# ግ ም ገ ማ ፡

# ምርጫ ፺፯ ፥- ሂደት፥ ክንዋኔና ውጤት፤ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) እይታ

## ክፍል አንድ፤

### መግቢያ፤

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የተጠናወተውን የአምባ-ገነኖች የአገዛዝ አዙሪት ለመበጠስና የሥልጣን ምንጭና ባለቤትነቱን አረጋግጦ፥ በሰላምና እርቅ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመገንባት በረጅም ውጣ-ውረድ የበዛበት ታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የተረጋጋና ቀጣይነት ያለው አስተማማኝ ሰላም አግኝቶ፥ ከአሳፋሪ የነጣ ድህነት ተላቆ፥ የብልጽግናን ጎዳና ለመከተልና አንድነቱን ጠብቆ ለመኖር የሚያስችል ህልሙን መሰል በሌለው ትግሉና ክቡር መስዋዕትነቱ እውን የሚያደርግበት መልካም ሁኔታ ግንቦት ፺፯ እንዳረገዘች ግልጽ ነበር። ለመልካም ፍሬም እንደምንበቃ የብዙዎች ልባዊ ምኞት ነበር። የተጠበቀው ተስፋ እውን መሆን እንደሚቻል ከተጠበቀው በላይ ግንቦት ሰባት አረጋገጠች፤ ዓለምን ባስደነቀና ሁላችንንም ባኮራ መልክ ሕዝባችን ታሪክ ሰራ፥ በኢትዮጵያ ምድር ዳግም አድዋ  በኢትዮጵያውያን ተወለደች። ግን እያንዳንዱ የተመዘገበ ድል የመነጠቅ ዕድል አለውና ኋላ-ቀር የግፍ አገዛዝ ያንገፈገፈውና ለውጥ የጠማው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎቱን በቁርጠኛነት እውን ለማድረግ ብዙ ጫናዎችን ተቋቁሞ ያስገኘውን ድል ለማስጠበቅና ለማስከበር ከለየለት አሸባሪ አምባ-ገነን አገዛዝ ጋር ግብ ግብ ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫ በሰፊው እንዲሳተፍ አድርገን ኢሕአዴግ ማቸነፍ ከፈለገ የሚኖረው አማራጭ በገፍ ማጭበርበር ብቻ ስለሚሆን ሕዝባችንን ቀስቅሰንና አደራጅተን የተጎናፀፈውን ድል እናስመልሳለን የሚል ቁርጠኛ አቋማችንን አሳውቀን፥ ሕዝባችንም ይኽንን አምኖና ተቀብሎ በአኩሪ መስዋዕትነቱ ድሉን ተጎናፀፈ። ሳይውል ሳያድር ድሉን ሲቀማ ገዥዎች ሸፍጣቸውን ለማረጋገጥ እስከምን ድረስ በግፍና በሽብር እንደሚሰማሩ በተቃዋሚው በኩል በቂ ኅሊናዊም ይሁን ድርጅታዊ ቅድመ-ዝግጅት ስላልነበር የሕዝባችን ድል ከተቀማ እነሆ ዓመት ተቆጠረ። ትግሉ ቀጥሏል። እስከ ድል ይቀጥላል።

በአንድ በኩል ተቸናፊው ሥልጣኑን አንቅሮ ለተፋውና በጥሎ ማለፍ ለአቸነፈው ሕዝብ ለማስረከብ ምንም ዓይነት ሥነ-ልቡናዊም ይሁን አካላዊ ዝግጅትና ፍላጎት አለመኖር፥ በሌላ በኩል የአሸናፊውን ሕዝብ ድል በፈታውራሪነት የመሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ምንም እንኳን መሪዎቹ በመልካም በጎ ፈቃድ፥ በችሎታ፥ በልምድ፥ በሚዛናዊ አስተሳሰብ፥ በተለይ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በማስቀደምና በሕዝብ ዘንድ የተሻለ ተዓማኒነት በማግኘት ረገድ የገዥው ፓርቲ መሪዎች አጠገባቸው ባይደርሱም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለለውጥ ያለውን ከፍተኛ ፍላጎትና ቁርጠኝነት በመመልከትና በማጤን በሕዝብ ላይ ካለ

ሙሉ እምነት ውጭ የሕዝቡን ድል በአስተማማኝ ለማስከበር የሚያስችል አስፈላጊው ድርጅታዊ መዋቅርና ዝግጅት በቂና መጣኝ አልነበረም፡፡ በተለይም የገዥውን ፓርቲ ጠባይ፥ የመሪዎቹን መሠረታዊ ባህሪ፥ አስተሳሰብና ሥነ-ልቦናዊ ይዞታ ተቃዋሚው ክፍል በተገቢ አልተረዳም ወይም አላገናዘበም ማለት ይቻላል፡፡ ለአንድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑት የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፥ ነፃና ገለልተኛ መዋቅሮች፥ ወዘተ... አለመኖር ሌላው የድል ዋስትና እጦት ማረጋገጫ እክል ነበር፡፡ በተጨማሪም ተቃዋሚው ክፍል የኢሕአዴግንና የአንዳንድ የውጭ ኃይሎችን ትስስር ምንነትና ይዘት በተገቢ አላጤነውም ማለት ይቻላል፡፡ እነኝህ ኃይሎች ስለ ዴሞክራሲና ስለ ሰው ልጅ መብት ስለሰበኩ ብቻ ከግል ጥቅማቸው ይበልጥ ለሁሉም የሰው ዘር እኩል እንደሚቆረቆሩ ወይም እንደሚቆሙና ቅድሚያ እንደሚሰጡ አድርገው የተረዱና በሌጣው የጠበቁ ብዙዎች ነበሩ፡፡ ከተቃዋሚው ወገን አብዛኛው እነኝህ የውጭ ኃይሎች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ ጥቂት አምባ-ገነኖችን ይመርጣሉ ብሎ አላሰበም፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚው ክፍል የዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ የኢሕአዴግን የግፍ እርምጃ በቸልታ አያይም፥ ከተራ ወገዛም የዘለለ እርምጃ ይወስዳል በሚል ከሚገባው በላይ ቅጥ ያጣ ሊያሰኝ በሚያስችል ልክ (መጠን) አመኔታ ጥሎ ነበር፡፡ በውጭ ኃይሎች ላይ የተጣለ ይኸ የተዛባ አመለካከት ያኔም ልክ አልነበረም ምን ጊዜም ልክ አይሆንም፡፡

መቸም አምባ ገነኖች እይታቸው በአንድ አቅጣጫ ብቻ ነው፡፡ እነሱ ሲደላቸው ሁሉም የደላው፥ በነሱ ላይ ካልተተኮሰ እነሱ እየገደሉም ቢሆን ሁሉም ሰላም እንደሆነ፥ የነሱ ቃል ሁሉ ሕግ እንደሆነና እነሱ የፃፉትን ሕግ ሳይቀር ሌላው እንጂ እነሱ ማክበር እንደሌለባቸው፥ ከነሱ የተለየ አሳብ ማቅረብና በነሱ ላይ ነቀፌታ ማሰማት ማለት በአገርና በሕገ-መንግሥት ላይ ጦርነት ማወጅ እንደሆነ፥ እነሱ በሥልጣን ቁንጮ ላይ ከሌሉ አገር እንደሚበተን፥ እነሱ የሰላም ጠር ሆነው እነሱ ካልመሩ ሰላም እንደማይኖር፥ ወዘተ... አድርው ነው ሁኔታዎችን የሚያዩት፥ እምነታቸውም ይኸው ነው፡፡ በእምነት ላይ የተሰነዘረና የተነጣጠረ ጥቃት ኅልውና ላይ እንደተሰነዘረ አንዳንዴም በበለጠ ሊሰማና ሊያስበረግግ ስለሚችል ነው እነሱም የተለየ አስተሳሰብን በእምነታቸው ላይ የተሰነዘረና ይኸም በኅልውናቸው ላይ የተቃጣ አደጋ አድርገው የሚቆጥሩትና መታገስና ተቻችሎ መኖርን ከአባባል አልፈው በተግባር መፈጸም የማይችሉት፡፡ ሥልጣንን በጊዜኣዊ የፖለቲካ የበላይነት ወይም በሃላፊነት ደረጃ ሳይሆን የሁለንተናዊ ኅልውናቸው (አካላዊ ጭምር) ብቸኛ ዋስትና አድርገው ስለሚቆጥሩት ሥልጣን ለነሱ ብቻ የተገባች እንደሆነና ከሥልጣን መውረድን የኅልውናቸው ማክተም አድርገው በማየት ሥልጣንን በከፍተኛ ቀናኢነት፥ ስግብግብነትና ጉጉት የሙጥኝ ይላሉ፡፡ በዚህ አስተሳሰብም ሥልጣን ላለመልቀቅ ባላቸው ግትር አቋም በየጊዜው በሚወስዱት ሕገ-ወጥና ጭፍን ፀረ-ሕዝብ እርምጃ ዋኝተው መውጣት ወደሚያቅታቸው የወንጀል ባሕር የባሰ እየሰጠሙ ይሄዳሉ፡፡ አደጋው እዚህ ላይ ነው፡- በሥልጣን መቆየት የሚችሉት በጉልበት ብቻ ነው፥ ይኸንም እውን ለማድረግ የዜጎች በግፍና በገፍ መሰቃየት፥ መንገላታት፥ መታሰር፥ መሳደድ፥ መብቶቻቸው መረን በለቀቀ መልኩ መረገጥ፥ መገደል፥ ወዘተ... የግድ ይሆናል፡፡ ይኸ አካሄድ ደግሞ የግድ ሕጋዊና ሰላማዊ ተብለው የሚጠሩ የቅሬታና የብሶት ማስተጋቢያና የአሳብ ማስተናገጃ መንገዶችን ሁሉ እንዲከስሙ ስለሚያደርግ ግፍና ጭቆና የበዛበት ሕዝብ መብቱን ለማስከበር ሌሎች መንገዶችን እንዲወስድ ይገደዳል፡፡ ይኸም በተራው ለማንም ሕዝብ የማይበጀውን ሰላሙም የአቸናፊዎች ሰላም ይሆንና አቸናፊ ወደ ቤተ-መንግሥት ተቸናፊው ወደ እስር ቤት፥ ስደትና መፍረናቀል የሚደረገው የአባገነኖች መቀያየር የአመፅ አዙሪት እንዲቀጥልና ሰፊው ሕዝብ ለተለመደው ሰቆቃና ችጋር እንዲዳረግ ይደረጋል፡፡

የአምባ-ገነኖች ትልቁ ችሎታቸው የማይወጡት ተቃውሞ ሲገጥማቸውና ሁኔታው ቀውጢ ሲሆንባቸው እንደየሁኔታው ጠባይ ጊዜ መግዛት መቻላቸው ነው፡፡ ሲወጠሩ አንገት ቀልበስ፥ ለስለስ በማለት ጊዜ መግዛት፥ ውስጥ ውስጡን ሁኔታው ለነሱ እንዲያመች ካደረጉ በኋላ ለተቃዋሚው ፋታ ሳይሰጡ ከማድቀቅና ጭራሹን ለማጥፋት አለበለዚያም ለነሱ በሚያመች መልክ ጠፍጥፎ ከመሥራት ወደኋላ አይሉም፡፡ አብዛኞዎቹ የአምባ-ገነን

ቁንጮዎች በተፈጥሮ ባህሪያቸው ፈሪዎች ስለሆኑ በጣም ጨካኞች ናቸው:: ስለሆነም በነሱ ዘንድ አቁስሎ መተው የሚባል ነገር የለም:: ለዚህም ነው ከአምባ-ገነኖች በተለይም አሸባሪ አምባ-ገነኖች ጋር የሚታገሉ ሁሉ እንደ ነብር አዳኝ ጠንቃቃ መሆን የሚኖርባቸው:: ነብር አዳኝ የመጀመሪያ መመሪያው ነብርን አቁስሎ መተው እንደሌለበት ጠንቅቆ ማወቅ ነው:: (የቆሰለ ነብር በምንም መንገድ አቁሳዩን ለማጥፋት ወደ ኋላ እንደማይል የታወቀ ነውና::) አምባ-ገነኖች ለማንሰራራት በአጭሩ በሦስት ደረጃ ተግባራቸውን ያከናውናሉ::

ደረጃ አንድ:- ጊዜ መግዛት፥ ደረጃ ሁለት:- መከፋፈል፥ ደረጃ ሦስት:- ፋታ ሳይሰጡ ተቃዋሚውን ማጥፋት፤

በአንድ በኩል ተቃዋሚውን በመሸንገል ለዘብ በማለትም ይሁን ለሁኔታው መፍትሄ ለመሻት ቀና መስሎ በመቅረብ ተቃዋሚው ያነሳውን የለውጥ አሳብ ሳይቀር በሙሉ ወይም በከፊል እንደሚስማሙበት ወይም ለመመርመር እንደተዘጋጁ እየለፈፉ ሕዝብን ለማነሁለል መሞከርና ተቃዋሚያቸው ክፍል እንዲዘናጋ እየጣሩ በሌላ በኩል ግን በተግባር ፈጽሞ ተቃራኒውን እየሠሩ ተቃዋሚውን በመከፋፈልና እርስ በርስ በማናከስ እነሱ የአፈና መረባቸውን በማጠናከር ተቃዋሚውን ተከላካይ እንዲሆንና አልፎም በጎልውናው ላይ በመዝመት ጥያቄው የተገላቢጦሽ ይሆንና ተቃዋሚው የተነሳበት የለውጥ አሳብ (አጀንዳ) እንዲረሳና እነሱ ለለውጥ በቆመው ክፍልና ሕዝብ ላይ የሚያስከትሉትንና የሚያደርሱትን እንደ እስራት፥ እንግልት፥ ግድያ፥ ወዘተ... የመሳሰሉ የግፍ ተግባሮችን በመቃወምና ለመከላከል በሚደረግ ጥረት ላይ ብቻ እንዲያተኮር በማድረግ ተቃውሞው ፈጽሞ ተከላካይ እንዲሆንና ተውሸልሽሎ እስከማይቀረው የመጨረሻ ሽንፈታቸው ድረስ አረመኔዓዊ አገዛዛቸውን በማስፈን ተቃውሞው እንዲከስም ይጥራሉ:: በአሁኑ ጊዜ ተቃዋሚው በዚህ የገኘው ወጥመድ ውስጥ ገብቶ ቀደም ሲል ከሥር መሠረቱ የተነሱ "የሕዝብ ድምፅ ይከበር" እና ከመሳሰሉ አውራ ጉዳዮች ወርዶ የኢሕአዴግ የግፍ እርምጃ ውጤት ወደሆነው "እስረኞች ይፈቱ" በሚለው ቀጭን መፈክር እንዲተካ እየተደረገ፥ ሌላው ቀርቶ መሪዎች ከመታሰራቸው በፊት ስለ ሰኔው ግፍ ሲነሳ የነበረው ጥያቄ እንኳን እየተረሳ አደገኛና አሳፋሪ የተከላካይነት ባህሪያት ቁራኛ በመሆን በስሊትም ባይሆን ኢሕአዴግ ለሚያደርገው ቅልበሳ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ አስተዋጽዖ በመደረግ ላይ ነው:: እዚህ ላይ ግልጽ መሆን የሚገባው እንደ የአቶ መለስ ኢሕአዴግ ዓይነቱ አረመኔዓዊ የግፍና የሽብር  አገዛዝ ዘለቄታዊነት የሌለው መሆኑን ነው:: ይሁንናም ያ እስከሚሆን ድረስ ግን መድረስ ያልነበረበት ግፍና ስቃይ በሕዝባችን ላይ መድረሱና ይኸም በሕዝቡ ትግል ላይ ከፍተኛ ሥነ-ልቦናዊ ጫና ማሳደሩ፥ በዚህም ምክንያት የሕዝባችን ተስፋ እንዲላላ መደረጉና በመሆኑም የመልካም ሥርዓት ግንባታው ወደ ኋላ መጎተቱ ሁላችንንም ሊያሳስበን የሚገባ ጉዳይ ነው::

እንደሚታወቀው አምባ-ገነን አገዛዝን በሕዝብ ላይ ለመጫን ሚሊዮኖች አያስፈልጉም፥ አምባ-ገነን ሥርዓትን ለማስወገድ ግን የሚሊዮኖችን/የብዙዎችን አንድጋ መቆምና መረባረብን ይጠይቃል:: ይኽ የሚሊዮኖች አንድጋ መቆምና መረባረብ ደግሞ እውን የሚሆነውና ውጤት የሚሰጠው አርቆ ማየት የሚችሉና ስትራቴጂአዊ የበሰለ ቆራጥ አመራር የሚሰጡ ድርጅቶች መሠረተ ሰፊ እንቅስቃሴ ጥራት ባለው መንገድ ማድረግ ሲችሉ ብቻ ነው::

የአቶ መለስ አገዛዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎት እረግጦና አፍኖ በጠብ-መንጃ ኃይል ሥልጣን ላይ ለመቆየት እየሞከረ ነው:: ሆኖም ለለውጥ ቆርጦ የተነሳውን ሕዝባችንን ድምፅ በጉልበት ቀምቶ በሰላም መግዛት እንደማይችል ሳይታለም የተፈታ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብና ኢሕአዴግ በተለይ ከግንቦት ስምንት ፲፯ ወዲህ ግልጽ በሆነ መንገድ ሆድና ጀርባ ሆነዋል:: ኀብረቱ የአገራችን ድኅረ-ምርጫ ሁኔታ የበለጠ አሳሳቢ እንደሚሆን አስቀድሞ በአግባቡ የሰጋውም ይኽ የአቶ መለስ ጠባብ ቡድን በመሣሪያ ኃይልና በሽብር ሥልጣን ላይ ለመቆየት በሚያደርገው መፍጨርጨር በሕዝቡና በገኘው ቡድን መኻል ያለው ቅራኔ የባሰውን እየሰፋና ጥላቻው የረጅም ጊዜ መፍትሔዎች ላይ ደንቃራ የሚፈጥር አስቸጋሪና

አጉል አቅጣጫ እየያዘ ሊሄድ እንደሚችል ከመረዳት ነው፡፡ በዚህ የገዥው ፓርቲ መሪዎች የእልህ ጉዞ ሕጋዊና ሰላማዊ እንቅስቃሴዎች እየከሰሙ የእርቅና የሰላሙን ሂደት ከመቸውም ጊዜና ከማንኛውም ሁኔታ የበለጠ እንደሚያወሳስበው ግልጽ ነበር፡፡ ኢሕአዴግ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ በኢትዮጵያ ምድር አገራዊ ሰላም ሊታይ ቀርቶ በርከት ያሉ ሰዎች የሚካፈሉባቸው መደበኛ የሐይማኖት በዓላትና የእስፖርት እንቅስቃሴዎች በሰላም ሊከናወኑባት የማትችል አገር እየሆነች ነው፡፡ ትምሕርት ቤቶችም ከዓመት ዓመት ተከፍተው ለመቀጠል መቻላቸው አጠራጣሪ ነው፡፡ ለመሆኑስ እስከ መቸ ተማሪ በወታደር ታጅቦ ሊማር ይችላል ብለው የኢሕአዴግ ቁንጮዎች እንዳሰቡ የሚገርም ነው፡፡

በአጭሩ የኢትዮጵያ ሁኔታ ካለፈው ግንቦት ወዲህ በአንድ በኩል ሕዝባችን ያስመዘገባቸውን ድሎች ለመቀማት ቆርጦ ከተነሳ ፍጹም አምባ-ገነን አገዛዝ ጋር እየተናነቀ ያለበትና ቅድመ-ምርጫ የነበሩ አንዳንድ መሠረታዊ መብቶች ሳይቀሩ ጨርሰው ደብዛቸው እየጠፋ፥ የዴሞክራሲ ሂደት ግንባታው በብዙ ዓመታት ወደ ኋላ እንዲጎተት ተደርጎ፥ ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉ ሕዝብ እንደ ሕዝብ በሰላም መኖር እንዳይችል አገርም እንደ አገር የመቀጠል ዕድል እንዲመናመን እየተደረገ ነው፡፡

ኢዴኃን ከተመሠረተበት ከነሐሴ ፮ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ማግስት ጀምሮ ለአንድ ዓመት ያህል ጊዜ ከሁለት መሥራች አባል ድርጅቶቹ ጋር በተፈጠረው ውዝግብ ምክንያት ድርጅታዊ ይዞታውን አጠናክሮ በተመሠረተበት መንፈስና ሕዝቡ የጣለበትን ተስፋ በሚመዝን ሁኔታና መጠን እንዳሰበውና ሊያደርግ የሚችለውንና የሚገባውን ያኽል የሚያረካ እንቅስቃሴ ማድረግ አልተቻለውም፡፡ በሁለቱ መሥራች አባል ድርጅቶችና በኀብረቱ መኻል የተከሰተውን ልዩነት ለመፍታት በተደረገው ጥረት የኀብረቱ አማካሪ ሸንጎ የተቻለውን ሞክሯል፡፡ ይሁንናም ከኀብረቱ መውጣት ብቻ ሳይሆን በውስጥ ሆኖ በልዩነት መታገል እንኳ ባይቻል ከውጭም ሆኖ ቢያንስ ጎን ለጎን ቆሞና ተደጋግፎ መታገል ሲገባ ተፃራሪ ሆኖ መቅረብና ኀብረቱን እንደጠላት ማየት ባልተገባ ነበር፡፡ ስለሆነም ኀብረቱ እንደአለመው ሁሉ በምሥረታው ላይ የመሳተፍ ዕድል ያልገጠማቸውን (ያልቻሉትን) ድርጅቶች ማሰባሰብ ቀርቶ በዚህ በውስጡ በተፈጠረ ያልታሰበ ልዩነት ምክንያት ወርቃማ የትግል ጊዜ ባክኗል፡፡ በጊዜው አሉ የተባሉ ልዩነቶች እንዲወገዱና ኀብረቱ ተጠናክሮ የሕዝባችን ትግል መልክ እንዲይዝ ብዙ ጥረት ቢደረግም አንዳንድ የአገሪቱ ችግር በተወሰነ ክፍል ብቻ የሚፈታ የመሰላቸው ወገኖች የዕብድ ገላጋይ ከመሆን ያልዘለለ ተግባር ላይ በመሰማራታቸው በመኻል የተከሰተው ልዩነት እንዲሰፋና ተቃዋሚው በሁለት እንዲካለል ተደርጓል፡፡ እነኝህ ወገኖች አሁንም ካለፈው ስህተት አልማር ብለው የኃይል አሰላለፉን ሲያንቦጫርቁት እየታየ ነው፡፡

ማንኛውም ድርጅት በተለይም ለሕዝብ ብሶትና መነሳሳት ምላሽ እሰጣለሁ ብሎ የተነሳ ድርጅት እክል ሲገጥመው ቆም ብሎ እራሱን መመርመርና ለገጠመው እክል የራሱን ድርሻ በቅንነትና በሃቀኝነት ገምግሞ፥ የእክሉን መንስዔ ጠንቅቆና አበጥሮ በመለየት ሳይውል ሳያድር መፍትሔ ሰጥቶ ትግሉን በአዲስ መንፈስ የመቀጠል ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ መሠረታዊ እምነት በመነሳት ኢዴኃን ባለፉት ወደ ሦስት ዓመት የሚጠጋ ኀልውናው በየጊዜው በውስጡ የገጠሙትን ችግሮችና እክሎች በተቻለ መጠን በቀናነት ለመመርመርና መፍትኄ ለመስጠት ሙከራዎች አድርጓል፡፡ በተቃዋሚው ክፍል በተለይ የጋራ ሥራ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶች መኻል እስከአሁን የሚታየው አባዜ የጋራ ሃላፊነትን በጋራ ከመወጣት ይልቅ ቶሎ ተስፋ ቆርጦ ኩምሽሽ የማለትና በተሰሩ ስህተቶች ወይም ግድፈቶች ላይ መብሰልሰል፥ የጋራ ሃላፊነትን ለመቀበል ዝግጁ አለመሆንና የጋራውን ተልእኮ እርግፍ አድርጎ በመተው እንደ አኩራፊ ልጅ ወደየተናጠል ሥራ ማተኮር ላይ መሰማራት ነው፡፡

ኀብረቱ ድኅረ ግንቦት ሰባት ፲፱፻፺፱ ዓ/ም ያለውን የውስጡንና በአጠቃላይ የአገሪቱን ሁኔታ እዚህ ላይ በአጭሩ የሚዳስሰውም በጋራ የተገኙ ድሎችን ለማስጠበቅ ከሚደረገው ሕዝባዊ ትንንቅ አኳያ በተናጠልና በወል የተሰሩ ግድፈቶችን በቀና መርምሮ ስህተቶች

እንዳይደገሙና መጠናከር አለባቸው የሚላቸውን በጎ ጎኖች ማጠናከር ስለሚቻልባቸው ጥቆማ በማድረግ የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግና በተለይም ኅብረቱ እንደ ኅብረት ድክመቶቹን አርሞ ለተሻለ ውጤት አስመዝጋቢ ትግል እራሱን ለማዘጋጀት ይረዳል ከሚል ቀና እምነት ነው።

## ክፍል ሁለት፤

## ቅድመ-ምርጫ ሁኔታ፥

በ፲፱፻፹፫ ዓ/ም የደርግ ሥርዓት ሲወድቅ ለማያባራ እንግልት፥ ለአሳፋሪ ችጋርና ለአመፅ አዙሪት የተዳረገ ሕዝባችንን በእርቅና ሰላም ላይ ወደተመሠረተ ሽግግር ሊወስድ የሚያስችል መልካም አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር። ሆኖም ግን አርቆ ማየት ያልቻሉት የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነን ገዥዎች ያን የመሰለ ዕድል በከንቱ እንዲከስም ማድረጋቸው በቁጭት የሚታወስና የብዙዎችን ተስፋ አደብዝዞ እንዳለፈ ግልጽ ነው።

እንደሚታወቀው በአገራችን በኢትዮጵያ በእርቅና በመግባባት ላይ የተመሠረተ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ምናልባት ከስምንት መቶ ዓመታት ወዲህ ተደርጎ አያውቅም። ያም ቢሆን ሕዝቡን ያልተመለከተ በገዥዎች መኻል ብቻ የተደረገ የሥልጣን ዝውውር ነበር። የሥልጣን ምንጭና የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድም ጊዜ በማንና እንዴት መተዳደር እንዳለበት ሊወስን ቀርቶ ቃሉ የመደመጥ ዕድል አግኝቶ አያውቅም። በመሆኑም ገዥዎች በመሰላቸውና እንደየአቅማቸው ሕዝብን ሲያምሱ፥ ሲያተራምሱና ሲጨቁኑ ቆይተዋል። ይኽ ሕዝብን ያገለለና በገዥዎች መኻከል የሚደረግ በአመፅ ላይ የተመሠረተ የሥልጣን ቅብብል አዙሪት በመቀጠሉም አገራችን ለእድገትና ብልጽግና እጅግ አስፈላጊ የሆኑት አስተማማኝና ዘለቄታዊነት ያለው ሰላምና መረጋጋት ማግኘት አልተቻላትም። ይኽም በተራው ሕዝባችንን ለአሳፋሪ የነጣ ድህነት ዳርጓል።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ጥቅም በልዩ ልዩ መልክና መንገድ ለረዥም ጊዜ የታገሉ ድርጅቶች የተናጠል የትግል ጉዞአቸውን ከልብ መርምረውና ፈትሸው ከተናጠል ይልቅ የጋራ አገራዊና ብሔራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ ቅድሚያ በመስጠት የጋራ ኃይላቸውን አስተባብረው በአንድ ብሔራዊ አጀንዳ ሥር ለመታገል በመወሰን ከሰባት ቀናት የሰከነ ዝግ ውይይትና ምክክር በኋላ በነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም ፲፭ ለመሳተፍ ፈቃደኛና ዝግጁ ከነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ፲፫ቱ ተገኝተው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን (ኢዴኃኅን) መመሥረታቸውና አንድ ወጥ የጋራ አመራር መፍጠራቸው ትብብር በገደደበት የአገራችን የፖለቲካ መስክ አንድ ታላቅ እመርታና ከፍተኛ ግኝት ነበር።
ኅብረቱ በመፈጠሩም፤

1. በገዥው ፓርቲ ላይ ከማተኮር ይልቅና በበለጠ እርስ በርስ በመሻኮት ሕዝብ ተሰላችቶ "ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ" በማለት ብሶቱንና ብስጭቱን ሲያስተጋ ያዳመጡት በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ የፖለቲካ ድርጅቶች ያለፉ የተናጠልና የጋራ ትግል ተመክሮዎቻቸውን በጥሞና መርምረውና የአገሪቱን ሁኔታ በሚገባ አጢነው "የውስጥ-የውጭ"፥ "ኅብረ-ብሔራዊ/አገር-አቀፍ- የአካባቢ/ጎሰኛ"፥ ወዘተ... የሚል ክፍፍል ሳይኖር ድርጅቶች በሚስማሙባቸው የጋራ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመታገልና "አሳፋሪ፥ አስቃቂና ዘግናኝ" ብለው የፈረጁትን የአገሪቱን ሁኔታ በሰላማዊ መንገድና በሰለጠነ ፖለቲካ ለመቀየር በመስማማታቸውና የጋራ መታገያ መድረክ እንዲሆናቸው ኢዴኃኅን በማቋቋማቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ሥነ-ልቦናዊ እርካታንና አዲስ ተስፋን፥ በተቃዋሚውም ላይ የተሻለ አመኔታን፥ ለተቃዋሚውም አክብሮት ማትረፍና ለአገር-አቀፍ ትግሉም የተሻለ አለኝታ ማስገኘት ችሏል።

2. በአንድ በኩል የተቃዋሚው ክፍል አገራዊ የትግል አንድነት እንዳይፈጥር ከፍተኛ ጥረት እያደረገና እየከፋፈለ በሌላ በኩል ጠንካራ ተቃዋሚ አጣሁ፥ የተቃዋሚ ያለህ እያለ ሲያሾፍና ሲማለል የነበረውን ኢሕአዴግና መሪውን አቶ መለስ ዜናዊን ከፓሪስ አንድ የተቃዋሚዎች መሰባሰብ ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ አደናግጧል፥ በተቃዋሚው ጎራ አንፃራዊ የአጥቂነት አዝማሚያ፥ በገዥው ፓርቲና መንግሥት የተከላካይነት ጠባይ እንዲንፀባረቅ አድጓል።

3. ከተቃዋሚው ክፍል ጋር ሰላማዊ ድርድር እንዲያደርግ ግፊት ሲያደርጉ ለነበር የውጭ ደጋፊዎችና በጎ አሳቢዎች ሁሉ 'ከማንና ከስንቱ ጋር' መነጋገር ይቻላል እያሉ ዚዛበቱ የነበሩት የኢሕአዴግ መሪዎች ኅብረቱ በተቋቋመ ጥቂት ወራት ውስጥ ከተቃዋሚው ጋር ለመነጋገር ፈቃደኝነታቸውና ዝግጁነታቸውን እንዲገልፁ አስገድዷል፥ አስችሏል።

4. ተቃዋሚው ክፍል በውጭ መንግሥታት ዘንድ የተሻለ ተደማጭነትንና ከበሬታን አስገኝቶለታል። በአገዛዙ ላይ የሚያቀርበው ቅሬታ የተሻለ እንዲደመጥና በአገዛዙ ላይም የተወሰነ ጫና እንዲያደርጉ አስችሏል።

5. ኅብረቱ በመመሥረቱ በአገራችን ልዩነትን አቻችሎ በሰላማዊ መንገድ የጋራ ትግል ማድረግ እንደሚቻል አረጋግጧል፥ በተናጠል ለመታገል የፈለጉ ድርጅቶችንም እንዲሰባሰቡ አደፋፍሯል፥ ምሳሌ ሆኗል። በመሆኑም ቀደም ሲል ከኅብረቱ ለመውጣት የወሰኑ ድርጅቶች ከሌሎች ጋር ሆነው ቅንጅትን እንዲፈጥሩ አስችሏል፤ በአወቃቀርና አሠራር ሳይቀር በመጀመሪያ አያስፈልግም ብለው የተከራከሩባቸውን የአወቃቀርና የአሠራር አካሄዶች የኅብረቱን ፈለግ እንዲከተሉ ሆኗል። *1

6. ከሁሉም በላይ የኅብረቱ መፈጠር ድርጅቶች ምርጫ ፺፯ን በተናጠል በየግል ድርጅት በተበታተነ መልክ ሳይሆን አገር-አቀፋዊ ይዘት ባለውና በአድነት/በስብስብ ደረጃ/ መካፈል እንደሚቻል ባደረገው ምሳሌአዊ ጥረት ቀደም ሲል ፈጽሞ የማይታሰብና የድርጅት ነፃነትን የሚጋፋ ነው የሚል እምነት የነበራቸውንና ከኅብረቱ ለመለየት እንደ አንድ ምክንያት ያቀረቡ ድርጅቶች በመጨረሻ ኅብረቱ በቀደደው ፈር በመሠማራት ቅንጅትን መሥርተው በአንድ ድርጅት ስም በምርጫው መሳተፍ በመቻላቸው የተገኘው አስደናቂ ውጤት እንዲገኝ አስችሏል።

7. በነአቶ መለስ የታየውን የመደራደር “በጎ-ፈቃድ” ኅብረቱ ተቀብሎ አደራዳሪ ቡድን በመሰየም በተለይም የግንቦት ፺፯ን ምርጫ ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር ከአንድ ዓመት በላይ የፈጀ ድርድር በማድረግ በሰለጠነ ፖለቲካ ድርድር እንደሚቻል አሳይቷል፥ ውጤቶችም ማስመዝገብ ችሏል።

በዚህም ድርድር ገዥው ፓርቲና መሪዎቹ ካላቸው ግትርና ጠባብ አመለካከት የተነሳ ኅብረቱ የፈለገውንና የጣረውን ያህል ባይሆንም ካቀረብናቸው ፲8 የማሻሻያ የሃሳብ ነጥቦች ውስጥ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጠቀሜታ ያላቸው ውጤቶች በማስገኘት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለግንቦት ድሉ እንዲበቃ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል።

ሀ) የሕዝብ ንብረት የሆኑ መገናኛ ብዙኃንን መጠቀም በተመለከተ፥- የመንግሥት መገናኛ

---

**1 መኢአድና ኢዴፓ ከኅብረቱ ጋር አብሮ ለመሥራት እንዳይችሉ ምክንያት ሆነዋል ብለው ካቀረቧቸው ነጥቦች ውስጥ አወቃቀርን በተመለከተ ኅብረቱ ሸንጎና ሥራ አስፈጻሚ እርከኖች ሊኖረው አይገባም፥ አሠራርን በተመለከተ በውጭ በተናጠል ድርጅት እንጂ በኅብረት ደረጃ የጋራ የሆነ የድጋፍ ኮሚቴ ማቋቋም አያስፈልግም፥ ወዘተ... የሚሉ ነበር። በእርግጥ ቅንጅቱ ሲቋቋም ግን ኅብረቱ የተነቀፈበት በተግባር ተሸሯል።*

ብዙኃንን በመጠቀም ሕዝብ ሊከታተል በሚችልበት መልክ ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚው ክፍል ቀጥተኛና የፊት-ለፊት ክርክር ማደግ በመቻሉ፣ ምርጫውን በተመለከተ በጣም ለተወሰነ የጊዜ መጠንም ቢሆን የተቃዋሚው ወገን መልእክቶቹን ለሕዝብ ማስተላለፍ በመቻሉ በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚው መካከል ያለውን ልዩነት ሕዝቡ ጠንቅቆ እንዲረዳና ሕዝቡ በገዥው ፓርቲና መንግሥት ላይ ያለውን ፍራቻና "የማይነካና የማይደፈር ኃይል" አለመሆኑን በገሃድ ለማወቅና መደፋፈር እንዲያገኝ፣ ለገዥው ፓርቲ ግልጽ ንቀትና በአማራጩም (በተቃዋሚው) ላይ የተሻለ ተስፋ እንዲኖረው አስችሏል።

ለ) በኢሕአዴግ የምርጫ ሕግ አንቀጽ 38/ሠ መሠረት በፓርቲ የሚቀርብ እያንዳንዱ የምርጫ ተወዳዳሪ አምስት መቶ የደጋፊዎች ፊርማ (በግል የሚቀርብ ተወዳዳሪ ከሆነ አንድ ሺህ) እንዲያቀርብ የሚጠይቀው እንዲሰረዝ ማድረግ ተችሏል። ቀደም ሲል በተደረጉ ምርጫዎች እንደታየውና እንደተረጋገጠው ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ ይኸ አንቀጽ በሚጠይቀው መሠረት የፓርቲ ተወዳዳሪዎች የሰጧቸውን የደጋፊዎች ዝርዝር በመጠቀም ገዥው ፓርቲ አስቀድሞ ማን የማን ደጋፊ እንደሆነ በመለየት በፈራሚዎቹ ላይ ልዩ ልዩ ጫና ማድረግና መራጮች በነፃነትና በምስጢር ምርጫውን እንደፈለጉ እንዳይሳተፉ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደርግ ስለነበር ይኸ እንዲቀር መደረጉ ጠቀሜታው ምን ያኸል እንደሆነ መገመት አያዳግትም።

ሐ) የውጭ ታዛቢዎች ምርጫውን እንዲታዘቡ ማድረግ ተችሏል። የኅብረቱ ተወካዮች ከአቶ መለስ ጋር መጀመሪያ በተገናኙበት ጊዜ ምርጫውን ነፃና ርቱዓዊ ለማድረግ እንዲቻል ካቀረቧቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች ውስጥ አገር-በቀልና የውጭ ታዛቢዎች ምርጫውን

እንዲታዘቡ እንዲደረግ የሚለው አንዱ ሲሆን የተገኘው መልስ ግን ፈጽሞ አሉታዊ ነበር። ይሁንናም እንዲገፋበት በመደረጉ ተቀባይነት አግኝቶ እነሆ የውጭ ታዛቢዎች ምርጫውን እንዲታዘቡ ማድረግ ተችሏል። ይኸም በመሆኑ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጋድሎና ድል በሌላ በኩል የገዥው ፓርቲ የማጭበርበር ሙከራ ይፋ እንዲሆንና በዓለም-አቀፍ ደረጃ እንዲታወቅ አስችሏል። አሁን ላለው ድኅረ-ምርጫ ትግል አግዟል።

ሠ) ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ማድረግ በተመለከተ፦- እንደሚታወቀው ተቃዋሚው ክፍል በአንድ አካባቢ ሕዝባዊ ስብሰባ ለማድረግ ከልዩ ልዩ ተደራራቢ እርከኖች ፈቃድ መጠየቅ ስለነበረበት ከፍተኛ መጉላላትና መደናቀፍ የተለመደ ችግር ነበር። በመሆኑም ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በታሰበው ቀን ማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑ ይኸ እንዲቀርና ለአካባቢው ባለሥልጣኖች ማሳወቅ ብቻ እንደሚበቃ ማድረግ ተችሏል። ይኸም በመሆኑ ተቃዋሚዎች አቅማቸው እንደፈቀደ ከአዳራሽ እስከ አደባባይ የዘለቀ ደማቅ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ማድረግና ገዥው ፓርቲ ላይ የነበረው ፍራቻ እንዲወገድና በምርጫው ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል። የኃይል አሰላለፉም በጠራ መልኩ ተቃዋሚውና ሕዝብ በአንድ ጎን ገዥው ፓርቲ በሌላ በኩል ነጥሮ በገሃድ እንዲታይ አስችሏል። ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግም ከንቀት አዚም ባንኖ የሕዝቡ ምኞት እንዲከስምና ድርጅቶች ውጤት አልባ እንዲሆኑ በደም ፍላት ያለ የሌለ ኃይሉን አሰልፎ ተንቀሳቅሷል። ይኸ በግልጽ የታየ ሕዝባዊ ማዕበል የሕዝቡን ቁርጠኝነትና ተስፋ አጉልቶ በማሳየቱ የዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡ፣ በተለይ እርዳታ "ለጋሹ" ክፍል በዝምታ ሊያልፈው የማይችል በመሆኑ፣ በአንድ በኩል ገዥው ፓርቲ የሚያደርገውን የሰብአዊ መብት ረገጣ ይዞታውን እንዲያሻሽልና ከተቃዋሚው ጋር በመደራደር ምርጫውን ተአማኒነትና ተቀባይነት ሊያስገኝ በሚችል መልክ ሁሉን ያሳተፈ እንዲሆን ጫና-ቀመስ ሙከራ እንዲያደርጉ ሲያስችል፣ በሌላ በኩል ገዥው ፓርቲ ሥልጣን በሰላም ይለቃል የሚል ሙሉ እምነት ስላልነበራቸው ሊሆን ይችላል ፊት ለፊት መላተምንና ውጥረትን ለማስወገድ በሚል ተቃዋሚው ወገን ከመንግሥት ጋር በመቀራረብ የተወሰኑ መሻሻሎች ከተደረጉ በሂደቱ ገብቶ እንዲሳተፍ ትኩረት እንዲሰጡ አስገድዷል፣ ውትወታቸውም እንዲጨምር ሆኗል።

ኅብረቱ በአንድ በኩል ምርጫው ነፃ፥ ርቱዓዊና ሁሉን-አቀፍ እንዲሆን ያቀረባቸውን የማሻሻያ ነጥቦች ገዥው ፓርቲ እንዲቀበል ሌሎችም፥ በተለይ ቅንጅቱ የድርድሩ ተካፋይ እንዲሆኑና ኢሕአዴግና የሱ መንግሥት እንደ ተመጣጣኝ ውክልናና፥ ምርጫ ቦርድና የምርጫ አስፈፃሚ አካላትን ገለተኛ/ሁሉን-አቀፍ እንዲሆኑ ማድረግን በተመለከተ፥ ወዘተ፥ .... ሳለመቀበል እያንገራገረ ያለባቸውን ነጥቦች በጋራ ገፍተን የተሻለ ውጤት ማስገኘት እንዲቻል ተደጋጋሚ ሙከራዎች ቢደረጉም በመጀመሪያ "ከመንግሥት እንጂ ከገዥው ፓርቲ ጋር አንደራደርም" በሚል ፈሊጥ የተቃዋሚውን አንድጋ ቆሞ የመደራደር አቅሙን ሰብሯል፡፡ ቀጥሎም በተለይ ድርድሩ ወሳኝ ደረጃ ላይ በነበረበትና ገዥው ፓርቲ ምርጫ ቦርድን በተመለከተ ኅብረቱ ላቀረባቸው አማራጮች የራሱን ተለዋጭ አማራጭ በማስተናገድ ላይ በነበረበት ደረጃ ሊረሳ የማይችልና ድርድሩ ዋጋ-ቢስ እንዲሆን ሆን ተብሎ በሚመስል መልክ በቅንጅቱ የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ በአቶ ልደቱ አያሌው "ቅንጅቱ ሁኔታ ተሟላ አልተሟላ በምርጫ ይሳተፋል" ተብሎ መነገሩ ገዥው ፓርቲ እንኳን ለመቀበል ተቸገርኩበት ያላቸውን ነጥቦች ቀርቶ ቀደም ሲል ለማስተናገድ እችላለሁ፥ አጠናዋለሁ ሲል ቃል የሰጠባቸውን ሳይቀር መልሶ ለማየትም አልፈለገም፡፡ ከነአካቴው ገዥው ፓርቲ "ብትገቡ ግቡ፥ ለምነውን መግባት የሚፈልጉ ሞልተዋል" የሚል የትዕቢትና የመዝናናት መልስ ሰጠ፡፡ ኅብረቱ ምርጫውን በተመለከተ ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር የሞከረው ድርድርም በዚያው ከሰመ፡፡

ኅብረቱ በዚህ መልክ የሚችለውን ያህል በድርድሩ ከገፋ በኋላ የምርጫ ምዝገባ ቀን እስከ መጋቢት ፲፭ ቀን እንዲራዘም ቀደም ሲል ለምርጫ ቦርድ ጥያቄ አቅርቦ በነገ ዛሬ መልሱን ካዘገዩ በኋላ በመጨረሻ ለስድስት ቀናት ብቻ እንደሚራዘም ነው ቁርጡ የተነገረን፡፡ ኅብረቱ በምርጫ ፺፯ መሳተፍን በተመለከተ የሥራ-አፈጻሚ ኮሚቴው ከኅብረቱ አባል ድርጅቶች ጋር ምክክር በማድረግ ተደጋጋሚ ውይይትና ግምገማ በሰፊው ካደረገ በኋላ በጥር ፲፭ ቀን ፺፯ ዓ/ም ባደረገው ቀጣይ ስብሰባ በምርጫው እንዲሳተፍ በወሰነው መሠረት ኅብረቱ በምርጫው ተሳትፏል፡፡*2

ኅብረቱ (ኢዴኃኅ) ከነሐሴ ፳፩ ቀን እስከ ነሐሴ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ/ም ባካሄደው ብሔራዊ ሸንጎ ላይ ምርጫ ዙሪያ ነፃና ፍትኃዊ ምርጫና በምርጫ ተሳትፎን በተመለከተ ኅብረቱ ለኢሕአዴግ መንግሥት ያቀረበውንና የተሰጠውን መልስ ገምግሞ በምርጫ ተሳትፎን በተመለከተ በመለስተኛ የፖለቲካ ፕሮግራሙ የተቀመጠውን በማጎልበትና ኅብረቱ ካለበት ደረጃና ሁኔታ ጋር በማጣጣም ነፃና ፍትኃዊ ምርጫ ለማካሄድ ኢዴኃኅ ባስቀመጣቸው ዓለም-አቀፋዊ መሥፈርቶች መሠረት አስፈላጊው የምርጫ ዝግጅት ሁሉ እየተደረገ፥ ከመንግሥት ጋር የሚደረገው ድርድርም ለሕዝብ ይፋ እየሆነ ሲሳካ ብቻ ኅብረቱ በምርጫው ውስጥ ገብቶ የጋራ እጩዎች በማሰማራት እንደሚወዳደር፥ ወደ ምርጫው የሚገባውና በምርጫው የሚሳተፈው በኅብረቱ ስምና በአንድ የጋራ ፕሮግራም እንዲሆን፥ ምርጫው በኢዴኃኅ አቸናፊነት ቢጠናቀቅ ያለውን ኋላ-ቀር አምባ-ገነን አገዛዝ በማስወገድ ለአገራችን ውስብስብ ችግሮች መፍትኄ ለማስገኘትና የሰከነ ሽግግር ለማድረግ እንዲቻል ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ብሔራዊ የአንድነት መንግሥት መቋቋም እንደሚኖርበት ግንዛቤ ወስዷል፥ ወስኗል፡፡ በውሳኔው መሠረት በምርጫው ዙሪያ ያሉትን የኅብረቱ ተግባራት ለማከናወን የሚከተሉትን የተግባር አካላት (ኮሚሽኖች) አቋቁሞ ተንቀሳቅሷል፡፡

ሀ)- የዴሞክርሲ ሂደቶች (ዴሞክራታይዜሽን)ና የነፃ ምርጫ ኮሚሽን፥

ለ)- የሽግግር መንግሥት አማራጭ ፕሮግራም አርቃቂ ኮሚሽን፥

ሐ)- የእጩዎች አሰባሳቢ፥ እንቂና አሰማሪ ኮሚሽን፥

በአገራችን ፖለቲካ እንደተለመደው የድርጅቶች መርኃ-ግብር (ፕሮግራም) ሰነድ በነሱና እንቀይረው በሚሉት ሥርዓት መካከል ያለውን ልዩነት አበጥሮ በሚያሳይ መንገድ

---

*2 በዚህ የኅብረቱ በምርጫ የመሳተፍ ውሳኔ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ የቀረበው ከኅብረቱ የቀድሞ ሊቀ መንበርና ምክትል ሊቀ-መንበር- ዶ/ር መረራ ጉዲናና ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ነበር፡፡

የተቀየሰ ሳይሆን በአብዛኛው ድርጅቶቹ ምኞታቸውን የሚገጹበት ዓይነት ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ የኅብረቱ ብሔራዊ አማራጭ የፖለቲካ መርኃ-ግብር (ፕሮግራም) ግን በአንድ በኩል ኢሕአዴግ ከሚከተላቸው መርኃ-እቅዶችና መርኃ-መመሪያ (ፖሊሲዎች) ጋር ያለንን ልዩነት የሚያነጻጽር ሆኖ በሌላ በኩል ኅብረቱ በተግባር ሊፈፅማቸው የፈለገውን እንዴት ተፈፃሚ እንደሚሆኑ መንገዱንና ዘዴውን የሚያስረዳ ነው፡፡ ለምሳሌ የመሬት ፖሊሲን በተመለከተ፥ ሕገ-መንግሥትን በተመለከተ፥ አንዳንድ እንዲቀየሩ የምንፈልጋቸውን መቀየር አለባቸው በሚል ደፈናዊ አቀራረብ ሳይሆን እንዴት መሆን እንዳለበትና እንደሚቻል ያሳያል፡፡
በመሆኑም የኅብረቱ ብሔራዊ አማራጭ የፖለቲካም ይሁን የኤኮኖሚ መርኃ-እቅዶች ለአንድ ምርጫ የተዘጋጁ ሳይሆን ለአሉብን መሠረታዊና ውስብስብ ችግሮች ዘለቄታዊ መፍትሔ ማስገኘት በሚችል መልክ ነው የተቀረጹት፡፡ ሆኖም ግን በአቅምና በአመራር እጥረት ምክንያት የኅብረቱን አማራጭ ሰነዶች የኢትዮጵያ ሕዝብ በበቂና በሰፊው እንዲያውቃቸውና እንዲወያይባቸው አልተደረገም፡፡

እንደሚታወቀው የአገሪቱ ቅድመ-ምርጫ የፖለቲካ ሁኔታ በተንጠለጠለ ተስፋ የተሞላ፥ ሕዝቡ ለመጀመሪያ ጊዜ በመንግሥት ላይ ያለውን ፍራቻ አሽቀንጥሮ የጣለበትና ፍላጎቱን ለማሟላት በፍጹም ቁርጠኛነት የተዘጋጀበት ነበር፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች በአላቸው አቅም ሁሉ ሕዝብን በማደራጀት በውስጡ ያለውን ልባዊ የለውጥ ፍላጎት በተግባር እንዲፈጽም ከፍተኛ መረባረብ አድርገዋል፡፡ ብዙ ወገኖች፥ በተለይም በውስጥም በውጭም ያሉ የኢሕአዴግ ደጋፊዎች፥ የግንቦት ፲፱፻፺፯ ምርጫን በኢሕአዴግ በጎ ፈቃድና ችሮታ ብቻ እንዲያውም በአንዳንድ ጠንካራ ደጋፊዎቹ ዘንድ ገዥው ፓርቲ ለሕዝብ ጥሩ ሥራ እየሠራ ስለሆነ ያለምንም ችግር ተወዳድሮ እንደሚያሸንፍ ሙሉ እምነት ስለነበረውና በራሱ ስለተማመነ ነው ምርጫውን አዘጋጅቶ “የፈቀደው” እና ምርጫው ሊከናወን የቻለው ስለዚህም ኢሕአዴግ ምስጋና ይገባዋል፥ ባለውለታም ነው፥ እሱን መንቀፍ ትክክል አይደለም ሲሉ ተደምጧል፡፡ ምርጫ ፺፯ ካለፉት ምርጫዎች ሁሉ በዓይነትም በመጠኑ በይዘትም የተሻለና እውነተኛ ለለውጥ የቆሙ ተቃዋሚ ድርጅቶችም እንዲሳተፉ ያደረገ፥ ሕዝባችንም ለውጥ ማምጣት እንደሚችል ከልቡ አምኖ በሙሉ ኃይሉ የተሳተፈበት፥ ወዘተ… መሆን የቻለው በአብዛኛው በውጭው ዓለም ጫናና በተለይም በውስጥ የሕዝብ ግፊት መሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡ ጥያቄው ግን ኢሕአዴግ ይኸንን በአቶ መለስ አነጋገር 'የተሰላ አደገኛ እርምጃ' ባይወስድ ኖሮ እንዳለፉት ምርጫዎች ብቻውን ሮጦ ብቻውን ቀደምኩ ቢል የሚቀበለው ስንት ነበር? ድጋፍስ ያገኝ ነበር ወይ? እንደ እውነቱ ከሆነ በሰበብ አስባቡ ጥቅማችንን የተሻለ ያስከብራል በሚል እርዳታቸውን ለሚለግሱት ክፍሎች ሳይቀር ድጋፋቸውን ለመስጠት አሳማኝ ሁኔታ ሊኖራቸው አይችልም፥ እርዳታቸውንና ድጋፋቸውን ለመቀጠልም ችግር ይሆንባቸው ነበር፡፡ አገዛዙም አምባ-ገነናዊ ይዞታውን ለመቀጠል አሁን እንደሚያደርገው ጉልበት ከመጠቀም ወደኋላ ባይልም ከአሁኑ የባሰ የተወገዘና ጨርሶ እራቁቱን እንዲቀር ያደርገው ነበር፡፡ በነአቶ መለስ 'የተሰላ ፈታኝ እርምጃ' ለአምባ-ገነን አገዛዛቸው መቀጠል ምርጫውን ቀደም ሲል እንደተደረጉ ምርጫዎች ሁሉ እንደለመዱት አጭበርብረው “ለዴሞክራሲያዊነታቸው” ሽፋን ማድረግ ይቻላል የሚል እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡ ያም ሆኖ ግን ተገዶም ቢሆን በተለይ በርጫው ሂደት ላይ የተወሰነ በር እንዲከፈት በማድረጉ ኢሕአዴግ መጠነኛ መሻሻል ማድረጉ ሊታመን ይገባል፡፡ ይኸ ሂደት ተቃዋሚ ድርጅቶች በስፋት እንዲሳተፉ በማስቻሉ ገዥው ፓርቲም እነሱም የሰለጠነ ፖለቲካን እንዲለማመዱ አድርጓል፡፡ በዚህ ረገድ የአገራችንን ፖለቲካ አሳድጓል፥ የሕዝባችንን ዝግጁነትና ብስለት በአደባባይ እንዲያረጋግጥ ዕድል ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ግን የኢሕአዴግ አምባ-ገነን መሪዎች በተለይ ከምርጫው ወዲህ በሕዝባችን ላይ የፈጸሙትና እየፈጸሙት ባለው ሕገ-ወጥ አረመኔአዊ ተግባር የኢትዮጵያን ሕዝብ ተስፋ በአጭር የሚቀጭ ሙከራ በመሆኑ ያደረጉትንም መጠነኛ የመሻሻል አስተዋጽዖ ሳይቀር እያጣፉት ብቻ ሳይሆን ገደል እየከተቱትና ኪሳራ ውስጥ እያስገባቸው ነው፡፡ ኢሕአዴግ በአገሪቷ የፖለቲካ ሕይዎት በሥልጣን ላይ በቆየባቸው ቅድመ-ምርጫ አሥራ-አራት የአገዛዝ

ዓመታት ውስጥ ተቀነጫጭበውም ይሁን ተንጠባጥበው ትንሽ በበጎ ጎን የሚፈረጅ አስተዋጽዖ ኖሮት ከነበር በዚህ ድኅረ-ምርጫ አረመኔአዊ የአፈና እርምጃው አውድሟቸዋል፡፡ በመሆኑም የኢሕአዴግ አውራዎች በምርጫው ሂደት የተከሰቱ አንዳንድ በጎ ነገሮችን በባለቤትነት ሊኩራሩባቸው፥ በባለውለታነት ሊፎክሩም ሆነ መመካት የሚያስችላቸው ምንም ዓይነት ኅሊናዊም ሆነ የሞራል ብቃት የላቸውም፡፡

ኅብረቱ የምዝገባ ቀን ስድስት ቀናት ብቻ ሲቀሩ ለምንና እንዴት ለመሳተፍ ወሰነ? ሁኔታዎች ሳይሟሉስ ውጤቱ ይኸ አሁን የተከሰተው መሆኑ እየታወቀና በተለይ የኅብረቱ መሥራች ጉባዔ ኅብረቱ በምርጫ የሚሳተፈው ምርጫው ዓለም-አቀፍ የነፃና ርቱዓዊ ምርጫ መስፈርቶች ሲሟሉ ብቻ ነው ለሚለው ውሳኔ ክብደት ሳይሰጥ ለምን በምርጫው ለመሳተፍ ወሰነ? ለሚሉት አግባብ ያላቸው ጥያቄዎች አጭር መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ከላይ ሲታይ በእርግጥ ኅብረቱ በምርጫ ለመሳተፍ መወሰኑ የኅብረቱን የሁኔታዎች የመሟላት ቅድመ-ሁኔታን የጣሰ ይመስላል፡፡ በእርግጥም የጠየቅናቸው ሁኔታዎች በተለይ እንደ ምርጫ ቦርድና ምርጫ አስፈጻሚ አካላትን የመሳሰሉ ዋና ዋና አካሎች ገለልተኛ እንዲሆኑ የቀረቡ ጥያቄዎች አለመሟላታቸው ግልጽ ነው፡፡ ለነገሩ ለጥያቄው ጥያቄ አለው፤ ኅብረቱ አልሳተፍም ብሎ ቢቀር ኖሮስ ውጤቱ ምን ይሆን ነበር? በልዩ ልዩ መግለጫዎቻችን እንደተገለጸው ሁሉ ሕዝብን ባላቀፈና ባላሳተፈ መልኩ በድርጅቶች ብቻ የሚወሰድ የአልሳተፍም (ቦይኮት የማድረግ) ውሳኔ እጅጉን መስመር የሳተና ውጤት አልባ አካሄድ ነው፡፡ ይኸ አስተሳሰብ የሚመነጨው ደግሞ ሕዝብን በባይተዋርነትና በተከታይነት እንጂ የትግሉ ዋነኛ ኃይል እንደሆነ ካለመገንዘብ ነው፡፡ በድርጅቶች የሚወሰድ የእምቢየው አልሳተፍም የፖለቲካ እርምጃ የሚሰራው ማንኛውንም የፖለቲካ ውሳኔና ለሕዝብ የሚቀርብ የእንቅስቃሴ ጥሪ ሕዝቡ በተግባር ለመተርጎም ድልድይ የሚሆኑ በልዩ ልዩ ዘርፍ የኅብረተሰቡን ጥቅም ለማስከበር የተደራጁ የሙያና የሲቪክ ማኅበሮችና ስብስቦች በጠነከሩበት፥ የፖለቲካ ድርጅቶች መዋቅራዊ ጥንካሬ ሲኖራቸውና አንድ ላይ ማሰብና መሥራት በሚችሉበት ሁኔታ ነው፡፡ ከዚያ ውጭ ሕዝብን ባላቀፈ መልክ የሚወሰድ የእምቢ አልሳተፍም እርምጃ ተቃውሞን ከመተክላዊ አቋም አንፃር ብቻ ከመግለጽ ውጭ የሚሄድና ትግሉን ወደፊት የሚገፋ አይሆንም፡፡ ለዚህም ነው አንደኛ በምርጫ ሂደቱ በመሳተፍ ሕዝብን ለማደራጀትና የሕዝቡን ትግል አንድ እርምጃ ወደፊት ለመውሰድ በማሰብ ነው ኅብረቱ ምርጫን በትግል ስልትነት ተቀብሎ የተንቀሳቀሰው፤ ሁለተኛ ተቃዋሚው በምርጫ ተሳትፎን በሚመለከት ያለው አመለካከትና ዝግጅት ተመሳሳይ ባለመሆኑና አንድ ላይ መቆም ስላልቻለ ገዥው ፓርቲ በተቃዋሚው ስም የሚወዳደርለት እስካገኘ ድረስ የሌላው ሳይሳተፍ መቅረት የሕዝቡን ትግል ወደፊት ለመግፋት ስለማያግዝ እንዲያውም በድርጅቶች መኻል ተጨማሪ ልዩነትን ከማስፋት የተለየ አስተዋጽዖ ስለማይኖረውና በኅብረቱም ውስጥ ክፍፍልን ሊፈጥር ስለሚችል በምርጫ መሳተፉ ትክክለኛ ስትራቴጂካዊ ውሳኔ ነበር፡፡

በዚህ የምርጫ ሂደት እስከ ምርጫ ክንውን ባለው ተሳትፎ የኅብረቱ አስተዋጽዖ ቀደም ሲል ለመጠቋቆም እንደተሞከረው በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ በእርግጥ በውስጥ ችግር በተለይ ሁለት መሥራች አባል ድርጅቶች ባነሷቸው ጥያቄዎች ምክንያት ያላስፈላጊ የውስጥ ውዝግብ ላይ ጊዜ ባይጠፋና የጋራ ውሳኔዎችን በተከተለና ባከበረ መልክ በሳል አመራር ቢሰጥ ኖሮ ብዙ መሥራት ይቻል እንደነበር ግልጽ ነው፡፡

ገዥውን ፓርቲና የአመራሩን አካሄድ፥ የፖለቲካ ባህሪና የነበረውን የኃይል አሰላለፍ በተመለከተ ኅብረቱ ከማንም የተሻለ ግንዛቤ ነበረው፡፡ የኅብረቱ መሥራች ጉባዔ በአገራችን የሰፈነውን አሳፋሪና ዘግናኝ ሁኔታ ለመቀየር በሥልጣን ላይ ያለው የኢሕአዴግ ፓርቲም ከሥልጣን መወገድ እንደሚኖርበት፥ ለዚህም እውን መሆን ኅብረቱ የሚከተለው የትግል ሥልት ሰላማዊ እንዲሆንና የሰላማዊ ትግል አካል የሆነውን ምርጫን በትግል ስልትነቱ እንደሚጠቀምበት መወሰኑ ይታወቃል፡፡ ምርጫውም ነፃ፥ ፍሃዊና ሁሉን-አቀፍ እንዲሆን ሁኔታዎች እንዲሟሉ ገዥውን ፓርቲ ወደ ድርድር አስገድዶ ለማቅረብ አስፈላጊው ሁሉ

እንዲደረግ መወሰኑ ግልጽ ነው። ለዚህም ኅብረቱ ድርጅታዊ ይዞታውን እንዲያጠናክርና በኅብረቱ ያልታቀፉ ተቃዋሚ ክፍሎች እንዲታቀፉ፥ ገዥው ፓርቲ እንዲደራደር ደብዳቤ እንዲፃፍ፥ የገዥው ፓርቲ እረዳቶችና ለጋሽ አገሮችም በዚህ ረገድ እንዲያግዙ ዘመቻ እንዲደረግ ወስኖ ተንቀሳቅሷል። ከላይ በተጠቀሱት የተግባር አካላት አማካይነት ባለው አቅም ሁሉ ተንቀሳቅሷል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ኅብረቱ ይበልጥ ትኩረት የሰጠውና አምኖ የተንቀሳቀሰው ከራሱ ከምርጫው ይበልጥና ከመንግሥት ለውጥ በላይ የሥርዓት ለውጥ ሊወልድ በሚችል የምርጫ ሂደት ላይ ነበር። ይኸም የሆነው የኅብረቱ እይታ ከአንድ ምርጫ የዘለለና ለማኅበራዊ፥ ኤኮኖሚአዊና ፖለቲካዊ ውስብስብ ችግሮቻችን ዘለቄታዊ መፍትሔን ማስገኛ ሁኔታዎችን በማመቻቸቱ ላይ ያማከለ ስለሆነ ነው።

በእርግጥ ምርጫ ፺፯ ነፃና ፍትኃዊ እንዲሆን ገዥው ፓርቲ ሁኔታዎች እንዲሟሉ አላደረገም። የግንቦት ፺፯ ምርጫ በብዙ ረገድ ከሌሎቹ ሁሉ የተሻለ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይኸ ሁኔታ የተፈጠረው ደግሞ የኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነን ገዥዎች ልባቸው እራርቶና ለመልካም ሥርዓት ግንባታ ተጨንቀውና ተጠበው ሳይሆን በዓለም-አቀፉና በአገር ውስጥ ባሉ ሁኔታዎች አስገዳጅነት መሆኑ ይታወቃል። በአገር ውስጥና በዓለም-አቀፍ ሁኔታዎች አስገዳጅነት ምክንያት በአንድ በኩል ቀደም ሲል ተደረጉ ከተባሉ የኢሕአዴግ ምርጫዎች ሻል ብሎ የሚታይና በተለይ እርዳታ ለጋሽ ደጋፊዎቹን መሸንገያ ሊሆኑ የሚችሉ ለእይታ የሚሆኑ እጅ መንሻ ለውጦችን በማሳየት በሌላ በኩል በሥልጣን ላይ ከማቆየት የማያግድ አካሄድን በመከተል የአቶ መለስ አገዛዝ የታሰበበት ስሊታዊ እርምጃ ወስዷል። በእርግጥም በብዙ መልኩ ምርጫ ፺፯ ቀደም ሲል ተደረጉ ከተባሉ የይስሙላ ምርጫዎች የዓይነትና የይዘት ለውጥ ነበረው።

ኢዴኃኅ በግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም አጠቃላይ ምርጫ የተሳተፈው ቀደም ሲል ያቀረባቸው የነፃና ርቱዓዊ ምርጫ መመዘኛ ስለተሟላ አለመሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ይኸ ምርጫ ሊጭበረበር የሚችልበት ዕድል አጠያያቂ አልነበረም። በእኛ አመለካከት ኅብረቱ በዚህ ምርጫ ከሂደቱ ጀምሮ መሳተፉ ትክክልና የሰከነ ዴሞክራሲ በአገራችን ላይ ሥር እንዲሰድ አስተዋጽዖ አድርጓል። ጥያቄው ኅብረቱ ከመሠረቱ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ያደረገው ትግል ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሚሆነው ወይም የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ ይችል የነበረው በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉም ተቃዋሚ አንድ ጋ መቆም ሲችል እንደነበር አጠያያቂ አይመስለንም። ኅብረቱ ምርጫን እንደ ትግል ስልት ነው የወሰደው ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ በአጭሩ ጠቀስ ማድረጉ አግባብ ያለው ይመስለናል። በአንድ አገር ምርጫ ስለተካሄደ ዴሞክራሲ አለ ማለት እንዳልሆነ ከራሳችን አገር ታሪክ የምንረዳው ነው። በአገራችን ውስጥ በአፄ ኃይለ-ሥላሴም፥ በኮሎኔል መንግሥቱ ደርግም አሁን ባለው የኢሕአዴግ አገዛዝም ሥር በልዩ ልዩ መልክ ምርጫዎች ተካሂደዋል። የተካሄዱት ምርጫዎች ግን ሕዝቡን የሥልጣኑ ባለቤት ማድረግ አልተቻላቸውም። ይኸም የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱ እንዲከበርለትና የሥልጣኑ ባለቤት መሆን ሳይፈልግ ቀርቶ ወይም ተፈጥሮአዊ ችሎታ አንሶት አይደለም። ሁሉም ምርጫዎች የተዘጋጁት፥ የተቀናበሩት፥ የተመሩትና የተከናወኑት በገዥዎቹ ብቻ ሲሆን ዓላማውም የአገዛዝ ሥርዓቶቹን ለማስቀጠልና የገዥዎቹን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ስለሆነ ነው። ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት መሆን የማይችልበት ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተብሎ ሊጠራ ከቶውንም አይችልም።

በምርጫው ሂደት እንቅስቃሴ ሕዝቡ የጠራ ግንዛቤ እንዲያገኝና መሠረታዊ የሆኑ መዋቅራዊ ጥንካሬዎች እንዲኖሩ የኅብረቱ ዓላማ ነበር። የጠራ ግንዛቤ ጨብጦ ከማስጨበጡ ሂደት ጋር በምርጫ ዙሪያ አንዱ ኅብረቱን ያሳሰበው ትልቅ ነገርና ትኩረቱን ሰጥቶ ጥረት ያደረገበት ተቃዋሚው ክፍል ተነጣጥሎ እንዳይቀርብ የማድረጉ ጉዳይ ነበር። ምክንያቱም ምንም እንኳ ሕዝቡ ገዥውን ፓርቲ ፈልጎ እንደማይመርጥ የታወቀ ቢሆንም ተቃዋሚው ቢያንስ ከሁለት ተከፋሎ እስከቀረበ ድረስ ገዥው ፓርቲ የሚፈልገው ከ33 ከመቶ እጅ ያነሰ ውጤት ማምጣት ብቻ ይሆናል። ይኸ ደግሞ ከአሥራ አራት ዓመታት በሥልጣን መቆየት

በኋላ ከልዩ ልዩ የማጭበርበር አይቀሬ ተግባሩ በተጨማሪ በምርጫ አስፈፃሚነት ያስቀመጣቸው ቀጥታ ደመወዝ ተከፋይ ተቀጣሪዎችና ከገዥው ፓርቲ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሆኑ ክፍሎችን ጨማምሮ ያንን ያኽል ውጤት የማምጣት ዕድሉ ሰፊ ነበርና ተቃዋሚው ተከፋፍሎ እስከቀረበ ድረስ ገዥው ፓርቲ ከአብዛኛው ሕዝብ ፍላጎት ውጭ አሸናፊ እንዲሆን ስለሚያስችለው ነው። ቅድመ-ምርጫ እንቅስቃሴውና ዝግጅቱ በጋራ እንዲደረግ በኅብረቱ በኩል ብዙ ጥረት ተደርጓል። በዚህ ረገድ ቢያንስ ተቃዋሚው ክፍል በምርጫው የሚያደርገው ተሳትፎ በጋራ በየምርጫ ጣቢያው ለየአንድ አንዱ የገዥው ፓርቲ ተወዳዳሪ አንድ የተቃዋሚው የጋራ ተወዳዳሪ ብቻ እንዲቀብ ለማድረግ ሙከራ ተደርጓል። በቅንጅቱ በኩል አሳቡ ተቀባይነት አላገኘም። በተጨማሪም ሁኔታዎች ወደ ምርጫ መግባት የሚወስዱ ከሆነ ሁለት ታላላቅ ጉባዔዎች፤ አንድ ቅድመ-ምርጫ አንድ ሌላ ድኅረ-ምርጫ የምርጫ ተወዳዳሪዎች ጉባዔዎች ማካሄድ እንዲቻል ዝግጅቶች እንዲደረጉ ወጥኖ ነበር።

*የመጀመሪያው* ማለት ቅድመ-ምርጫ ጉባዔ ዓላማው የምርጫ ጉዳይ ተከታታይ አካልና ተወዳዳሪዎቻችን አጠቃላዩ አገር-አቀፍና በየአካባቢው ያለው ሁኔታ ላይ ዝርዝር ዘገባ ቀርቦ ግምገማ እንዲደረግና ወደ ምርጫ በመግባት የሕዝቡን ትግል ማጠናከር የሚያስችል ሁኔታ መኖር አለመኖሩን ለመመርመርና ለመወሰን፥ በምርጫው ለመሳተፍ አበረታች ሁኔታ ከሌለም አማራጭ የትግል ስልቶችና መንገዶችን ለመምከር እንዲያስችል ሲሆን፤ ወደ ምርጫ መግባት የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሮ መሳተፉ ተመራጭ ከሆነና ኅብረቱ ለመሳተፍ ከወሰነ የተሻለ ውጤት ማምጣት ስለሚቻልባቸው ዘዴዎችና ስልቶች ለመምከር ነው። በተጨማሪም በዚህ ጉባዔ የሚጠናቀረው የምርጫ ሂደት ግምገማ ላይ ያተኮረ ዘገባ በገዥው ፓርቲና መንግሥት በኩል እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮችን በመረጃ በተደገፈ በማቅረብ ችግሮቹ እንዲወገዱ ለሚደረገው ትግል ከፍተኛ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። ይኸ አካሄድ በተወዳዳሪዎች ዘንድ የተሻለ በራስ መተማመንንና ድርጅታዊ ቅርርብን ሲያስገኝ በሕዝቡም ዘንድ ሥነ-ልቦናዊ ዝግጅትን አጠንካሪ እንደሚሆን ይገመታል።

*ሁለተኛው* ማለት ድኅረ-ምርጫ የተወዳዳሪዎች ጉባዔ የሚጠራው ምርጫው እንደተከናወነ ይሆናል። ዓላማው ምርጫው እንዴት እንደተከናወነና የተከሰቱ ችግሮችን በተለይ የምርጫ አሰጣጡ፥ ታዛቢዎች ተግባራቸውን ማከናወን መቻል/አለመቻላቸውን፥ የድምፅ ቆጠራው፥ ወዘተ... የሚጠናቀርበትና የሚገመገምበት ሲሆን ውጤቱ የምርጫ ቦርድ ከሚያውጀው ውጤት ጋር ተመሳክሮ በእኛ (በተቃዋሚው) በኩል ያለው ውጤትና በቦርዱ የሚሰጠው ውጤት የማይጣጣም ከሆነ፥ ያለው የመስክ (የየምርጫ ጣቢያና ወረዳ) መረጃ ተቃዋሚው እንዳሸነፈ የሚያሳይ ከሆነና በምርጫ ቦርዱ የታወጀው ያንን የማያንፀባርቅ ወይም ተቃራኒው ከሆነ የሕዝብ ድምፅ ተጭበርብሯል፥ ተሰርቋል ማለት ስለሆነ፥ የተባለውን የተሳሳተና የተጭበረበረ ውጤት እንደማንቀበለው በመወሰን ተወዳዳሪዎቻችን (ተመራጮቻችን) ወደየመጡበት ሳይበተኑና ለገዥው ፓርቲ ፋታ ሳይሰጥ የተቃዋሚው አማራጭ ሸንጎ እንደተመሠረተ ለሕዝብ ይገለጻል። ይኸ ሸንጎም የራሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ሰይሞ፥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካቢኔውን በማቋቋም ሕዝቡ ከጎኑ እንዲሰለፍ ጥሪ ያቀርባል። ይኸ እርምጃ በተቃዋሚውና በገዥው መኻል የመፋጠጥ ሁኔታን መፍጠሩ አይቀርም። ሆኖም በሕዝብ የታጀበ ሚዛናዊ ድርድር እንዲጀመርና ብሔራዊ የጋራ (የአንድነት) የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም የተሻለ ሁኔታን ይጋብዛል። ቢያንስ የሕዝቡ ትግል ባልተበተነና ባልተሟዘዘ መልኩ ተጋግሎ እንዲቀጥል ያስችላል። በዚህ መንገድ ለሕዝብ ድምፅ መከበር የሚደረገውን ትግል በተቀናበረ መልክ የተሻለ ማእከላዊ አመራር መስጠት ይቻላል።

በአብዛኛው በንድፈ-ሃሳብ የቀረና በፈለግነው መልክና ልክ ተግባራዊ ሳይሆን የቀረ ሌላ ዓቢይ ጉዳይ ኅብረቱ በዚህ ሂደት ውስጥ የሲቪክና የሙያ ድርጅቶች ሚና ጎልቶ እንዲወጣ የነበረው ውሳኔ ነው። ከመሥራች ጉባዔው ጀምሮ ኅብረቱ በአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሂደቱ ትግል እንዲጠናከር የሲቪክና የሙያ ድርጅቶችን ማለት የመምሕራን፥ የሴቶች፥ የገበሬዎች፥ የሰራተኞች፥ የወጣቶች፥ የነፃው ኅትመት (ፕረስ)፥ ወዘተ... መኖርና መጠናከር

እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አምኖ ካሉት ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዲደረግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሞክሯል:: ሆኖም በሚያሳፍር መልኩ ጎላ ብለው ከሚታዩትና ረዥም ልምድ ካላቸው ጋር እንኳ ሳይቀር የሚያጠግብ ውጤት ያለው ሥራ አልተሠራም:: ይኽ ድክመት በሥራ አመራሩና በሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ብቻ ሳይሆን በተግባር ኮሚቴዎችና በድጋፍ አካሎች ሳይቀር በየጊዜው የተነሳ ጉዳይ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ በሙሉና ያለጥርጥር ገዥውን ፓርቲ እንዳልፈለገ ኀብረቱና ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች በምርጫው ሂደት ወቅት በከተማና በገጠር በአዳራሽ ውስጥና በአደባባይ ባደረጓቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ ከመንግሥት የሚደርስበትን ማስፈራራትና ግልምጫ ከመጤፍ ሳይቆጥር ግልብጥ ብሎ በመውጣት ያሳየው ቆራጥነት ለለውጥ ዝግጁነቱን ያረጋገጠበት እጅግ አደፋፋሪና አኩሪ ተግባር ነበር::

ኀብረቱ ሁሉም ወይም ቢያንስ አብዛኛውን ተቃዋሚ ክፍል አንድ ጋ ማሰለፍ ይቻላል ከሚል እምነት በመነሳት ነው ምርጫን በትግል ስልትነት በአራት መንገድ ጠቀሜታ እንዳለው በመገንዘብ የተንቀሳቀሰው::

አንደኛ፡- ተቃዋሚው በሕዝብ ወሳኝነት አምኖ በቁርጠኝነት በምርጫ መሳተፉ በአገራችን ከአመፅ ውጭ በሰለጠነ ሰላማዊ ፖለቲካ የሥልጣን ሽግግር እንደሚቻል በተግባር በማሳየት ሕዝብ ለሥልጣኑ ባለቤትነት የሚያደርገው እንቅስቃሴ የፍርሃትን ሥነ-ልቦናዊ ጫና ያስወገደና የፖለቲካ ድርጅቶችም የሕዝብን ድጋፍና ተቀባይነት ተፈርቶ ሳይሆን በፍላጎት ተወድዶ ማግኘት የሚያስችል አዲስ ባህል እንዲያዳብሩ ይረዳል::

ሁለተኛ፡- ሕዝባችን የሥልጣኑ ባለቤት መሆን እንዲችል ምርጫው ዓለም-አቀፍ የነፃና ፍትኃዊ ምርጫ መስፈርቶችን ባሟላ መልኩ እንዲካሄድ ለሁኔታዎች መሟላት ገዥውን ፓርቲ አስገድዶ ወደ ጠረጴዛ በማምጣት ውጤት ያለው መደራደር እንዲያደርግ ያስችላል::

ሦስተኛ፡- ገዥው ፓርቲ ጤናማ አስተሳሰብ ዋጅቶ ነፃና ፍትኃዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የማሟላት ፍላጎት ከሌለው ሕዝብ ያለውን ሁኔታ እንዲረዳ በማድረግ <u>ሕዝብን በመያዝ</u> በምርጫው ማንም እንደማይሳተፍ በማድረግ ለገዥው ፓርቲ ተወዳዳሪ መንሳትና ብቻውን እንዲቀር ማድረግ:: ያለ እውነተኛ ተቃዋሚ ብቻውን ምርጫ ደግሶ ከራሱ ጋር ተወዳድሮ የራሱን ድግስ እራሱ አሞካሽቶ አቸነፍኩ ቢል በአለው ዓለም-አቀፍ የፖለቲካ ይዞታ ተቀባይነት ስለማያገኝ ተቃዋሚው ከሕዝቡ ጋር በመሆን በምርጫ ጨዋታ እንደማይገባ በመወሰን ለገዥው ክፍል ሕጋዊነትን ለመንፈግ ይችላል::

አራተኛ፡- በምርጫ መሳተፍም ሆነ አለመሳተፍ መብት የመሆኑን ያህል የምርጫው ውጤት ትክክለኛ ካልሆነና የሕዝቡን ፍላጎት ካላንፀባረቀ ውጤቱን አለመቀበልም እኩል መብት ነውና ሕዝብና ተቃዋሚው አንድ ጋ በመቆም የተጭበረበረ ውጤትን ባለመቀበል አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ወይም ውጤቱ እንዲስተካከል ገዥውን ፓርቲ ማስገደድ ያስችላል::

ወደ ምርጫ ፺፯ በተደረገው እንቅስቃሴ ገዥው ፓርቲ በእርግጥ ሕዝቡን ንቆና ተቃዋሚው ክፍልም በመሃሉ ያለው የማያባራ የእርስ በርስ መፏከትና በውሃ ቀጠነ አለመግባባት፥ አንፃራዊ በሆነ መልክ ደከም ያለ ድርጅታዊ ይዞታና ብቃት፥ በተለይም ኮሳሳ የገንዘብ አቅም ምክንያት እርባና ያለው መቋቋም ያደርጋል ብሎ አልጠበቀም::

ምርጫው ከመጠናቀቁ በፊት ሊደረጉ የሚገባቸውን ዝግጅቶችና ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች መመካከር እንዲቻል የተቃዋሚው የጋራ አካል መቋቋምን አስፈላጊነት በመረዳት በዚህ ረገድ ትብብር እንዲኖር ኀብረቱ ወትዉቷል፥ ጥረትም አድርጓል::

በማንኛውም አምባ-ገነን ሥርዓት ሥር ያሉ ምርጫ ቦርድ፥ የምርጫ አስፈጻሚ ክፍሎችና የምርጫ ሕግ ሁሉ ዋና ዓላማና ተግባር ያው በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ/ድርጅት መልሶ ሥልጣን ላይ መቆየትን ማረጋገጥ ብቻ ስለሆነ ባለፈው ግንቦት ምርጫም ቀደም ሲል በኢሕአዴግ ለኢሕአዴግ ተዘጋጅተው እንደተካሄዱ ምርጫዎች ሁሉ ውጤቱ ይኸ እንዲሆን መደረጉ ግልጽ ነው።

በግንቦቱ ምርጫ በተለይ አዲስ አበባና አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ኅብረቱ ውጤት ማምጣት አለመቻሉ በኅብረቱ ውስጥ ያነጋገረ ጉዳይ ነው። በእርግጥም በተለይ ኢዴኅና መላው አማራ ድርጅቶች በስፋት በሚንቀሳቀሱባቸው ቀጠናዎች ውጤቱ ፈጽሞ ያልተጠበቀ ነበር። በዚህ ረገድ ግምገማ ተደርጓል።
በኢዴኅ በኩል ከትግራይ የተወከሉ የኅብረቱ የምርጫ ተወዳዳሪዎች በገዥው ፓርቲ ከፍተኛ ተጽዕኖና ዛቻ በምክክር ከምርጫው እራሳቸውን እንዲያገልሉ ተደርጓል። ይኸ ባይሆን ኖሮ ኅብረቱ በትግራይ ካሰለፋቸው ታጋዮች ውስጥ ቢያንስ ግማሹ ሊመረጡ ይችሉ እንደነበር ኅብረቱ ሙሉ እምነት ነበረው። የኅብረቱ አብዛኛው ትኩረት በኦሮሞና በደቡብ ክልሎች እንደነበር ግልጽ ነው። ከምርጫው ቀደም ሲል በቅንጅቱና በኅብረቱ መኻል የተደረገው ስምምነት በአንዳንድ አካባቢዎች በተዛባ መልክ ኅብረቱ የውድድር ቦታውን ለቅንጅቱ እንደለቀቀ ተደርጎ እንደተወራና ይኸም ድምፅ ላለማግኘት አስተዋጽዖ እንዳደረገ ተነግሯል። ያም ሆነ ይኸ ኅብረቱ ከኦረሞና ከደቡብ ክልል ውጭ በምርጫ ቦርዱ ስሊት ውጤት አላስመዘገበም።

## <u>ክፍል ሦስት፡-</u>

## <u>ድኅረ-ምርጫ</u>

እንደሚታወቀው ኢዴኃኅ ምርጫው ነፃና እርቱዖዊ እንዲሆን ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር ድርድር ላይ ስለነበርና ይልቅም የምዝገባ ቀን ቢያንስ በአንድ ወር እንዲራዘም ያቀረበው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ያገኛል በሚል ተስፋ ላይ እያለ ገዥው ፓርቲ ለስድስት ቀናት ብቻ እንደሚራዘም ብያኔ ስለሰጠ የምዝገባ ቀን ገደብ ሊጠናቀቅ ጥቂት ቀናት ሲቀረው ብቻ ነበር ወደዚህ ምርጫ በሙሉ ልብ የገባው። ስለሆነም ኅብረቱ ከ1350 በላይ ብቁ እጩ ተወዳዳሪዎችን በአገር-አቀፍ ደረጃ መመልመልና ማሰማራት የቻለው በነኝህ ጥቂት ቀናትና በባዶ እጁ ነበር። ይኸ በእውነት የሚደነቅ ውጤት ነው። የሚያሳየውም ከኅብረቱ ጥንካሬ ይበልጥ ሕዝባችን ለለውጥ ያለውን ጥማት፥ ዝግጁነትና ብስለት ነው።

ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ የለውጥ ውሳኔ በፀጋ እንደማይቀበል ኅብረቱ የጠነከረ ግንዛቤ ነበረው። በሥልጣን መቆየትን እንደብቸኛ የኅልውና ዋስትና አድርገው የሚቆጥሩት የኢሕአዴግ መሪዎች ማንኛውንም መንገድ ተጠቅመው ሥልጣንን የሙጥኝ ማለታቸውና ቢያንስ አጥብቀው ማንገራገራቸው የታወቀ ነበር። ስለሆነም በአንድ በኩል ለለውጥ ቆርጦ የተነሳው ሕዝብና ተቃዋሚው ክፍል፥ በሌላ በኩል ደግሞ የመጣ ይምጣ ሥልጣን አልለቅም የሚለው የሌባ ዓይነ-ደረቁና እንቢተኝነት የተጠናወተው ገዥ ፓርቲ መኻል የተከሰተው ፍጥጫ አይቀሬ ነበር። እንደሰጋነውም ይኸ የልዩነት አቋም አገራችንን እጅግ ወደ ተወሳሰበ አስቸጋሪ አቅጣጫ የሚያመራ ፈታኝ ድኅረ-ምርጫ የውጥረት ሁኔታ ውስጥ እንድትገኝ አድርጓል። ኅብረቱ ይኸ ጉዳይ እንደሚከሰትና ስለሆነም አላፊነት የሚሰማው ሁሉ በጥብቅ እንዲያስብበትና በአዲስ አስተሳሰብ በጋራና በተቀናበረ መልክ እንዲረባረብበት፥ ከማሳሰብና ከማስጠንቀቅ አልቦዘነም። ሁኔታው ሊያስከትል የሚችለውን የሕዝብ ድል የመቀማት አደጋና የአቶ መለስ አረመኔአዊ የግፍ አገዛዝ በአዲስ መልክና በለየለት ጭካኔ ባገጠጠና ባፈጠጠ መልክ ድምፁን በነፈገው ሕዝብ ላይ የበቀል እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል ግልጽ

*ስለነበር የተቃዋሚው ክፍል በጋራ መቆምና ሕዝብን በማስተባበር ይኸንን የተጋረጠ አደጋ በጋራ መቋቋም አስፈላጊና አንገብጋቢ መሆኑ በኅብረቱ በኩል ገና ከጠዋቱ የታመነበት ጉዳይ ነበር።*

*እንደሚታወቀው በቅድመ-ምርጫው ሂደት ተቃዋሚው ተቀራርቦ እንዲሠራና በተለይም ወደ ምርጫው በጋራ እንዲቀርብ፥ ከምርጫውም ክንውን በኋላ ስለሚኖረው የመንግሥት ዓይነትና አቋቋም ላይ በተለይ በኅብረቱና በቅንጅቱ መኻል ውይይቶች ተካሂደዋል። ኅብረቱና ቅንጅቱ ከምርጫው በኋላ ከሁለት አንዳቸው በግልጽ ቢያሸንፍ ያቸነፈው ወገን መንግሥት እንዲመሠርት ሌላው እንደሚደግፍና እንደሚረዳ፥ ግልጽ የተናጠል ማቸነፍ ባይኖር ደግሞ የጋራ ጥምር መንግሥት ለማቋቋም ስምምነት እንዳደረጉ የሚታወስ ነው። እዚህ ላይ ግልጽ መሆን የሚገባው ከምርጫ በኋላ በቅንጅትና በኅብረት የጋራ ጥምር መንግሥት ይቋቋማል የሚለውን አስተሳሰብ የኅብረቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አላፀደቀውም። ምክንያቱም ይኸ አስተሳሰብ ኅብረቱ ካለው የድኅረ-ሕወሓት/ኢሕአዴግ የመንግሥት ዓይነት መሠረታዊ እምነት ጋር የማይጣጣም ስለነበር ነው። የኅብረቱ እምነትና በብሔራዊ አማራጭ የፖለቲካ መርኃ-እቅዱ (ፖሊሲው) በክፍል ሁለት እንዳስቀመጠው የአገራችንን የተወሳሰቡ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል የሰከነ ሽግግር ማድረግ ስለሚያስፈልግ ወደዚህ የሚደረገውን ሂደት ለማገዝ ድኅረ-ኢሕአዴግ መቋቋም የሚኖርበት መንግሥት ሁሉን-አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግሥት ስለሆነ ነው። የፖለቲካ ሥልጣን ሽግግር ከአንድ ኃይል ወይም የኃይሎች ስብስብ ወደ ሌላ ድርጅት ወይም የድርጅቶች ስብስብ የሚደረግ ተራ የሥልጣን ዝውውር ሳይሆን በአጠቃላይ ኅብረተሰባችንን ተብትቦ ይዞ ከቆየው የአመፅ የሥልጣን ቅብብል አላቅቆ ከአንድ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የአገዛዝ ሥርዓት ሕዝቡን የሥልጣኑ ባለቤት ሊያደርግ ወደሚችል የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማብቃት እንዲቻል የሰከነ ሽግግር ማድረግን ኅብረቱ መሠረታዊ እምነት አድርጎ ነው የወሰደው። እዚህ ላይ ግልፅ መሆን የሚገባው ጉዳይ ይኸ ኅብረተሰባችንን እንዳለ ወደ ሰከነ ሽግግር የሚወስደው ሂደት የሚከናወነው በቀጥታ ሥልጣን በሚረከብ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አማካይነት አለመሆኑ ነው። ኅብረቱ መመሥረት ይኖርበታል የሚለው የሽግግር መንግሥት ለአንድ ዓመትና ለዓመት ተኩል ያኸል ጊዜ የሚቆይ፥ እጁን በቀጥታ በሽግግር ሂደቱ የማያስገባና ተግባሩም ጊዜኣዊ አስተዳደር ብቻ የሚሆን ይሆናል። በእኛ እምነት በፕሮግራማችን በሰፊው እንደተብራራው የሽግግሩ ጉዳይ ተግባራዊነት ለሚቋቋሙት ሁለት ኮሚሽኖች ማለትም ለብሔራዊ እርቅና ለዴሞክራሲያዊ ሂደት ኮሚሽኖች የሚተው ይሆናል።*

*የግንቦት ሰባት ምርጫ ውጤት ችግሮች እንዳሉበት ያኑ ዕለት ማታ ግልጽ ነበር። ኅብረቱ በድኅረ-ምርጫው ማን አቸነፈ ማን ተቸነፈ የሚለውን ውጤት ለማወቅ ከመቻል በላይና ይበልጥ ትኩረትና ክብደት የሰጠው ምርጫው በሃቅና በትክክል የመከናወኑ ሂደት ላይ ነበር። በኅብረቱ በኩል በትክክልና በሃቅ አካሄድ የሚደረስበትን ውጤት ለመቀበል፥ ለማክበርና በእሱም ለመገዛት ፈቃደኝነት ብቻ ሳይሆን እምነታችን እንደሆነ ተገልጿል። በአንፃሩ ገዥው ፓርቲ የኢትዮጵያን ሕዝብ ውሳኔ አክብሮና ውጤቱን በፀጋ ተቀብሎ ሥልጣን ለማስረከብ ኅሊናዊም ሆነ ቁሳዊ ዝግጅት እንደሌለውና እንደሚያንገራግር የነበረው ስጋት እውን እንደሚሆን እርግጠኛ በመሆን ችግሮች የባሰ ሳይወሳሰቡና ለገዥው ክፍል በምንም መንገድ ፋታ ሳይሰጥ የተቀናበረ የጋራ ሥራ እንዲሠራ የተቃዋሚው ክፍል በተለይ አብዛኛውን የሕዝብ ድምፅ ያገኘው ቅንጅት ከኅብረት ጋር (በሂደት ሌሎችንም ሊጨምር እንዲችል ተደርጎ) ከፍተኛ የአመራር አባላትን ያቀፈ አንድ የጋራ ወሳኝ አካል በአስቸኳይ እንዲቋቋም አሳብ አቅርቧል። ይኸ አካል በሥሩ የሚከተሉትን የተግባር ንኡስ አካሎች አቋቁሞ ተግባር ላይ እንዲሰማራ ፍላጎታችን ነበር።*

*ሀ) ለሕዝብም ሆነ ለውጭው ዓለም የሚሰጡ መግለጫዎችን በጋራ የሚሰጥና ከዲፕሎማቲክ ማኅበረ-ሰቡ ጋር የሚገናኝና ሁኔታውን የሚያስረዳ የሕዝብ ግንኙነትና የተቃዋሚው ክፍል ቃል-አቀባይ (ካስፈለገም ከሁለቱም አንዳንድ ሰው ተመድቦ በየተራ እንዲሠሩ ማድረግ)፥*

ለ) ከሲቪክና ከሙያ ማኅበራት ጀምሮ እስከ ቀበሌ ያሉ መዋቅሮችን የሚያስተባብርና የሚያደራጅ አንድ አደራጅና አስተባባሪ አካል፤

ሐ) ከፖሊስ፥ ከፀጥታና ከጦር ኃይል ክፍሎች ጋር የሚገናኝ አንድ የደኅንነትና የመረጋጋት ጉድይ አካል፤

መ) ከገዥው ፓርቲና መንግሥት እንዲሁም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚደራደር አንድ ተደራዳሪ አካል፤

በዚህ ሁኔታ መዘበራረቅን አስወግዶ አቅጣጫ ሳይሳትና ለገዥው ፓርቲ ፋታ ሳይሰጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስመዘገባቸውን ድሎች ማስከበር እንዲቻል ሙከራ ተደርጓል። ከዚህ ውስጥ ምን ያህሉን በተለይ የቅንጅቱ አመራር እንዳወቀና እንዳሰበባቸው ማወቅ አልቻልንም።

በኅብረቱ በኩል ድኅረ-ምርጫ የአገራችንን ሁኔታ በተመለከተ ከምርጫው በፊት ከሞከርነው ጥረት ሁሉ በበለጠ የተቃዋሚው ክፍል በጋራ በመቆም ገዥው ፓርቲ ትርጉም ወዳለው ድርድር እንዲመጣና ምስቅልቅል ሁኔታን በማስወገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጋድሎ በተረጋገጠ ድል እንዲቋጭ አቅማችን የፈቀደውን ያኸል ሞክረናል። ይኸ ሙከራ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም እንዲንፀባረቅ ጥረት ተደርጓል። ከምርጫው በኋላ ኢሕአዴግ በቅርብ ደጋፊዎቹ ሳይቀር ድጋፍ እያጣና እራቁቱን እየቀረ ስለነበር የባሰ እንዲነጠል ለማድረግና ቢያንስ እምቢ የማይለው ጫና እንዲደረግበትና ወደ ድርድር እንዲመጣ በውጭው ዓለም ያለውን የዲፕሎማሲ ሥራ እና ኢትዮጵያውያን በትግሉ የሚያደርጉት ተሳትፎ በተደራጀና መልክ ባለው ሁኔታ ጎልብቶ እንዲቀጥል ለማድረግ በተለይ ከቅንጅቱ ጋር ብዙ ለመሥራት ተሞክሯል። በምርጫ የተቸነፈ ቡድን ጊዜ እንዳይገዛና ሂደቱን እንዳይቀለብስ ለማድረግ የቅድሚያ ቅድሚያ ተቃዋሚው አንድ ጋ መቆም ተፈላጊ ብቻ ሳይሆን የግድ ነበር። ሆኖም በፈለግነው መልክ በተግባር የሚታይ ከልብ የታሰበበት ምክክር ማድረግ እንኳ በጣም አስቸጋሪ ነበር። በመሆኑም ለገዥው ፓርቲ ተዋናይነት መድረኩ ክፍት ሆነ። አገሪቱ አጣብቂኝ ውስጥ ወደቀች፤- ተቸንፎ ሥልጣን ላለመልቀቅ በቆረጠና ይኸንንም ተግባራዊ ለማድረግ ምንም ነገር ለማድረግ ደንታ በሌለውና ኃላፊነት በማይሰማው የአቶ መለስ ዜናዊ ገዥ ቡድን እና ሕዝቡ በመስዋዕትነቱ ያስገኛቸውን ድሎች ለማስጠበቅና ለማስከበርም ይሁን ሕዝቡ የሰጠውን ሥልጣን ለመረከብ ድርጅታዊ ዝግጅቱም ስልቱም በጎደለው አቸናፊ ተቃዋሚ ክፍል መኻል። በሌላ በኩል ዓለምን ባስደነቀ ጨዋነት፥ ሥነ-ሥርዓት፥ አስተዋይነት፥ ብልሃትና ትዕግሥት መብቱን ለማስከበርና ድሎቹን ላለማስነጠቅ በቁርጠኝነት የተሰለፈው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና በሌላ በኩል ጥቂት በኢትዮጵያ ሰላና መረጋጋት ሰፍኖ ዴሞክራሲ እንዲያብብ ከሚያስቡ ወገኖች ጀምሮ ምንም ይሁን ምን በአካባቢው ያለ ጊዜአዊ ጥቅማቸውን ከማስከበር አኳያ ብቻ ሁኔታውን ለማመቻቸት ደፋ ቀና የሚሉ የውጭ ዓለም ክፍሎች (ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰብ) ለሁኔታው እልባት ለመስጠት በየአቅጣጫው የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፥ አሁንም ቀጥሏል። ገዥው ፓርቲ ሥልጣን የሙጥኝ በማለት ሰላማዊ ዜጎችን ረሽኗል፥ በገፍና በግፍ አፍሶ አስሯል፥ በጉልበት ሥልጣን ላይ ለመቆየት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሽብር ጦርነት አውጇል። ተቃዋሚው በጋራ ስትራቴጂና ስልት መንቀሳቀስ አቅቶት፥ የተቀናበረ አመራር መስጠት ተስኖት በተለያየ አቅጣጫ እየተጓዘ የኅብረት አመራር ላይ ከነበሩት መኻል ሁለቱ የቀድሞ ሊቀ-መንበርና ተቀዳሚ ም/ሊቀ-መንበር ከኅብረቱ ውሳኔ ውጭና የሕዝብን ፍላጎት ተፃርረው ለኢሕአዴግ ዴሞክራሲያዊ ሽፋን ሰጭና ያለቀበትን ሕይዎት እስትንፋስ ሆነው ፓርላማ በመግባት የኢሕአዴግ ወንጀል ተባባሪ መሆንን ሲመርጡ፥ የቅንጅት መሪዎች የሕዝብን አደራ ጠብቀው ለእስከፊ እስር ተዳርገዋል። እንግልት እጣ ፋንታው የሆነ የሚመስለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአቶ መለስ ሽብር ዘመቻ እየወረደበት አሁንም ድሉን ላለማስነጠቅ በሚችለው ሁሉ እየታገለ ይገኛል።

ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰብ እንደተቃዋሚው በአንድ አፍ መናገር አቅቶት በአንድ በኩል ሕዝብ እንዳቸነፈ፥ ገዥው ምርጫውን እንደሰረቀና እንዳጭበረበረ፥ ከምርጫው ወዲህ ገዥው ክፍል የወሰደውን አረመኔአዊ እርምጃ ባልከረረ መልኩ እየኮነነ፥ በግፍና በሕገ-ወጥ መንገድ የታሰሩ ሁሉ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታና በአስቸኳይ እንዲፈቱና በተቃዋሚውና በገዥው ፓርቲ መኻል ሰላማዊ ድርድር እንዲካሄድ በመጠየቅ ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከሃቅ ጋር ሲቆም፥ በሌላ በኩል ይኽን አገዛዝ በሞግዚትነት ያሸበለበሉ ክፍሎች በዳይም ተበዳይም፥ አሳሪም ታሳሪም፥ በሰላማዊ መንገድ ሕጋዊ ጥያቄ ያቀረበም መሠረታዊ ሰብኣዊ መብቶችን የሚረግጠውም፥ ገዳይም ሟችም "ሁለቱም ከሚወስዱት እርምጃ እንዲቆጠቡ" ከሚጠይቅ ቅጥ ያጣ የዕብድ ገላጋይ አቋም ጀምሮ፥ ተደራዳሪ እነማን መሆን እንደሚኖርባቸው ከመምረጥ፥ እስከ ከተቃዋሚው መኻል ማን "አክራሪ" ማን "ሁኔታው የገባው ፖለቲከኛ" እንደሆነ የመፈርጀት፥ የገዥውን ፓርቲ ዕድሜ ለማራዘም በመወሰን ተቃዋሚን ከማባበልና ከመደለል እስከ ማስፈራራት የደረሰ አጉራ ዘለል መሯሯጥ ታይቷል፥ እየታየም ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡ ዞሮ ዞሮ የራሱን ጥቅም ማስጠበቅ ስለሆነ ተልዕኮው አሁንም የአገሪቱ ጉዳይ መፍትኄ ኢትዮጵያውያን ላይ በተለይ ተቃዋሚው ላይ ነው። በዚህ ረገድ ይኽ የዓለም-አቀፍ ማኅበረሰብ ብለን አጠቃለን ካቀረብነው ክፍል ውስጥ ሁለት የውጭ አገር ኤምባሲ ተወካዮች በተገኙበት ተቃዋሚውንንና ገዥውን ፓርቲ/መንግሥት በሚያደራድሩበት ወቅት ድርድሩ በኢትዮጵያውያን በኻል፥ ጉዳዩ የውስጥ፥ ድርድሩ በኢትዮጵያ ምድር ሆኖ ሳለ ለነሱ አስተርጓሚ ማስቀመጥ ሲገባ ድርድሩ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሆን ተደርጎ ነበር። ይኽ የሚያሳየው ለነዚህ ክፍሎች ምን ያኽል የወሳኝነት ሚና እንዲኖራቸው እንደተፈቀደ ነው። በመሆኑም ልክ እንደገዥው ፓርቲ እነሱም በበኩላቸው ፍላጎታቸውን ለማስተጋባትና በተቃዋሚው ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና ለማድረግ አደፋፍሮአቸዋል። ተቃዋሚው ወገን በገዥው ፓርቲ አሻፈረኝነት ምክንያት በተከሰተው ድኅረ-ምርጫ የውጥረት ሁኔታ ትግሉን መስመር ለማስያዝና የሕዝብን ድምፅ ለማስከበር በተደረገው ትግል ሙሉ አመኔታውን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በማድረግ ፋንታ በሚያስገምት ደረጃ በዚህ ሦስተኛ አካል ላይ እንዳደረገ ተንፀባርቋል። ይኸው ሦስተኛ አካል ተገቢውን የሦስተኛ አካል ሚና ሳይሆን ለገዥው ፓርቲ ዓይን ያወጣ አድልዖ ባለው መልኩ ዋነኛ ተዋናይ እንዲሆኑም አደፋፍሯል። ያም የተዛባ አመለካከት ተቃዋሚው ያለ እነሱ መንቀሳቀስ እንደማይችል ወይም እነሱ ያሉትን እንደሚቀበል ስላረጋገጠላቸው የገዥው ፓርቲ ቁንጮዎችም ተቃዋሚው እንዲቀበልና እንዲፈጽም የሚፈልጉትን ሁሉ በቀጥታ ሳይሆንላቸው በነዚሁ የውጭ ሰዎች አማካይነት ተግባራዊ ለማድረግ ቀላል ሆኖላቸዋል። ለምሳሌ የታቀደው የመስከረም ፳ እና ፳፩ ቀኖች አገር-አቀፍ ስብሰባ እንዳልሆነ ሆኖ፥ ለመስከረም ፳፪ ቀን የተጠራው አገር-አቀፍ የድጋፍ ሰልፍ ፈቃድ በመከልከሉ ቅንጅቱና ኅብረቱ በጋራ የሦስት ቀን የቤት ውስጥ የክተት አድማ በመጥራታቸው እጅግ ተደናግጠው የነበሩት የኢሕአዴግ መሪዎች ይኽ እርምጃ እንዲሰረዝላቸው ያደረጉት በነዚሁ ሦስተኛ ክፍል ደላላዎች ነው። አሁንም ግልጽ መሆን የሚኖርበት ጥፋቱ የነሱ ሳይሆን የየድርጅቶቻቸውን ውክልና ሳይዙና ይሁንታ ሳያገኙ በጓዳ የተደራደሩት ሁለቱ የኅብረቱና የቅንጅቱ ተወካዮች ብቻ ነው። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ያም እርምጃ ልክ እንደ ሰኔ ሦስቱ የሦስትዮሽ ድርድር ተብዬ የሕዝቡ የጋለ ትግል ላይ ዳግም ቀዝቃዛ ውሃ ቸልሶበታል። ተቃዋሚውም ቅድሚያ መውሰድን ከእጁ አሳልፎ በመስጠት የኢሕአዴግ የቅልበሳ እርምጃ እንዲፋጠን አበረታታ፥ አስቻለም።

እንግዲህ ድኅረ-ምርጫ የተከሰተውን ውጥረት ለማስወገድ በጊዜው የነበረው ምርጫ ከላይ ሲታይ አንድም ከዚያ በፊት ያልታየ ዓለም-አቀፍ ጫና ተጨምሮበት ተቃዋሚውና ሕዝቡ አንድነቱን ብቻ ሳይሆን ቁርጠኝነቱንም አጽንቶ የመጣው ይምጣ በማለት መብቴን አሳልፌ አልሰጥም ብሎ ወሳኝ ፍልሚያ ማድረግና አይከፍሉ መስዋዕትነት ከፍሎ ገዥውን ፓርቲ ሥልጣን እንዲያስረክብ ማስገደድ፥ ወይም አስገድዶ አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ማስቻል፥ ወይም በአቅመ-ቢስነትም ሆነ በስመ ሰላምና መረጋጋት ከተቃዋሚው ወገን የተወሰው ክፍል ከኢሕአዴግ ጋር ግንባር በመፍጠር ገዥው ፓርቲ በጉልበቱ የሕዝብን

ሥልጣን ከሕዝብ መንጋጋ አውጥቶ እንዲወስድና ዴሞክራሲ ደኀና ሰንብች፥ መብት እስከወዲያኛው ብሎ ተሰናብቶ ከመቸውም የባሰ የሽብር አገዛዝ በአገራችን እንዲሰፍንና የሕዝቡ ስቃይ እንዲቀጥል መፍቀድ ሆኖ የታየበት ነበር። ይኽ ከሆነ ደግሞ የዴሞክራሲ ሂደት፥ የመቻቻል ፖለቲካ፥ ዴሞክራሲያዊ፥ ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል እንደከሰሙ ቁርጡን አውቆ ሌሎች አማራጮችን ማየት የግድ እየሆነ እንደመጣ ግልጽ ነበር።

ይኽ ምርጫ በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ተፋላሚዎች ከሞላ ጎደል ሁሉም የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ክፍሎች በተወከሉበት ሁኔታና ግልጽ በሆነ መልክ በሦስት የድርጅት ስብስቦች ማለት በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ)፥ በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (በቅንጅት) እና በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) አሰላለፍ እንዲንፀባረቅ ሆኗል። ይኽ የኃይል አሰላለፍ በገዥው ፓርቲ አውራዎች ጠባብና የተዛባ አስተሳሰብ ምክንያት ባይደናቀፍ በአገራችን ለተከሰተው ድኅረ-ምርጫ የፖለቲካ ቀውስ መፍትሔ ለማስገኘት በጣም አመች መሆኑ ግልፅ ነበር። ይኽ አመች የኃይል አሰላለፍ በመኖሩም ድኅረ-ምርጫ ቀውሱን ለመፍታት አንዳንድ የመፍትሔ አሳቦችን ማቅረብ ተችሏል።

የገዥው ፓርቲ ቁንጮዎች በኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ በተቃዋሚው ላይ አመኔታ ስለሌላቸውና ከሥልጣን መልቀቅ ቀርቶ ከሌላ ድርጅት/ድርጅቶች ጋር ሥልጣን መጋራት ማለት በነሱ ላይ በቀጥታ የሞት ፍርድ እንደተሰጠ አድርገው ስለሚቆጥሩት፥ ጊዜ ገዝተው ተመልሰው የባሰ አምባ-ገነን ይዞታቸውን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንዳይጭኑ ለማድረግ፥ ስጋታቸው መሠረተ-ቢስ መሆኑን ሊያረጋግጥላቸውና ድርጅታቸው በድርጅትነት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ እንደሚቀጥል ዋስትና ሊሆናቸው እንዲችል፥ ሕዝባችንንም ከቀጣይ ሰቆቃ፥ አገራችንንም ከትርምስ ለማዳን፥ ለጋራ ብሔራዊ ጥቅምና ሁሉም አቸናፊ ሆኖ የሚታይበት፥ ማንም በተናጠል ወይም በቡድን ተቸናፊ ሆኖ የማይቆጠርበት መንገድ መቀየስ አለበት ከሚል እምነት፥ በሂደቱ የመሳተፍ ዕድል ያልነበራቸውን ክፍሎች በጨመረ መልኩ ይበልጥ በእርቅና በመግባባት ላይ የተመሠረተ የሰከነ ሽግግር ማድረግ የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር ይቻል ዘንድ ብሔራዊ የአንድነት የሽግግር መንግሥት ማቋቋሙ አስፈላጊ መሆኑን በማመን ኅብረቱ ይኽንን አሳብ በጋራ እንድንገፋበት ቅንጅቱን በማግባከር ከተከታታይ ውይይቶች በኋላ አሳቡን ለገዥው ፓርቲና መንግሥት በጋራ ማቅረብ ተችሏል።

ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ከዚህ የተሻለ ለጋስ አማራጭ በውነቱ አልነበረም። ይሁንናም አርቆ ማየት የተሳናቸው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ይኽንን ለተሻለ ለውጥ የቆመው ተቃዋሚ ክፍል በበጎ ፈቃድ ላይ በመመሥረት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ተካፋይ እንዲሆኑ ያቀረበላቸውን ግብዣ አልተቀበሉትም።

ተቃዋሚው ሊቀበለው የሚገባ እውነታ አለ። ይኸውም ኢሕአዴግ ምንም እንኳ ምርጫ ፺፯ ፈጽሞ ከጠበቀው በላይና ውጤቱም ያልገመተው እንደሆነ ባያጠራጥርም ልዩ ልዩ ምናልባታዊ ሁኔታዎችን በመገመት ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችሉ አማራጮችን እንዳሰላና ቅድመ-ዝግጅቶች እንዳደረገ፥ (ኃይልን ለመጠቀም የማያቅማማና ምላጭ የመሳብ ሙሉ ፈቃደኝነቱም ሆነ ለጊዜው ችሎታው እንዳለው በተደጋጋሚ በተግባር አሳይቷል፥ ጤናማ ያልሆነ አጥፍቶ የመጥፋት ሃላፊነት የጎደለው አስተሳሰብ እንዳለውና እንደሚከተልም ግልጽ ነው።)፤ በአንፃሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለለውጥ ዝግጁ መሆኑንና ለዚህም በቁርጠኝነት እንደቆመ ካለው እምነት ውጭ የተቃዋሚው ጎራ ያለው ድርጅታዊ ብቃትና በተለይ ተማምኖና ተባብሮ የመሥራትና ለጋራ ውጤጥ የመብቃት አቅም ገና አስተማማኝ ደረጃ ላይ እንዳልነበር ግልጽ ነው።

ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሽብር ጦርነት በሕዝባችን ላይ አውጆ ሲነሳ ሁለት ዓላማዎችን ለማከናወን አስልቶ ነው የተንቀሳቀሰው። እነሱም፤ በሚወስደው አረመኔአዊ የግፍ እርምጃ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጫንቃው እያወረዳቸው የነበሩ

ፍራቻ፥ የእርስ በርስ መጠራጠርና አለመተማመን ተመልሰው እንዲሰፍኑ ማድረግና ተቃዋሚውን ወገን መከፋፈል ናቸው። የሕዝቡ ቅስም ቀስ በቀስ እንዲሰበር የሚያደርጉ ሥነ-ልቦናዊ ጦርነቶችና ማቁሰሎች ሰምመው እንዲገቡና እንዲሰርጹ ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠራቸው የመገናኛ ብዙሃንና የሚፈኛ መዋቅሮች አማካይነት የሚቻለውን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ አላለም። ትግሉን ለማኮላሸት በማሰብ የተቃዋሚው ክፍል እርስ በርሱ እንዳይተማመንና እንዲጠራጠር የፈጠራ ውዥንብሮችን በማናፈስና ለማናከስ ከመሞከር ጀምሮ ተቃዋሚው መኻል ጠንካራና ሊቆጣጠረው የማይችለውን ድርጅት ሁሉ በተናጠልና በየተራ የማፍረስና አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ በሱ መልክ ለሱ ታማኝ አገልጋይ በሚሆኑበት መልክ ጠፍጥፎ የመሥራቱን ተግባር በስሊት እየሠራበት ይገኛል። ይኸም ቀደም ሲል የኅብረቱ አባል በሆኑት በኦብኮና በኢዴኅ እንደተፈጸመው ሁሉ ትእይንቱ አሁን ደግሞ በቅንጅት ላይ ሲፈጸም እያየነው ነው።

ኢዴኃኅ (ኅብረት) ድኅረ-ምርጫ እንቅስቃሴዎቹን በአራት አቅጣጫዎች ለማካሄድ ጥረት አድርጓል።

<u>አንደኛ፡- ድርጅታዊ አቅም ግንባታ፤</u>

የተሰበጣጠረውንና ውጥንቅጡ የወጣውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር የመብት ትግል መልክ ለማስያዝ የተቋቋመው ኢዴኃኅ የአመለካከት፥ የራእይና ከሱም የመነጨ የፕሮግራም ጥራት እያለው፥ በስሜታዊነትና በዕለታዊ ሞቅ ሞቅታ ግለት ሳይሆን በእምነት ላይ በተመሠረተ ከጎኑ ያልተለዩ ጠንካራ ደጋፊዎች ሳይገደው፥ የብዙ ጊዜ የካበተ የትግል ልምድ ያላቸው፥ መንፈሰ-ጠንካራና መሠረተ-ሰፊ ድርጅቶችን በአባልነት ያቀፈ ኅብረት በተለይ በአገር ውስጥ በቂና ጠንካራ ድርጅታዊ መረብ፥ ቆራጥ አመራርና ግልጽ አሠራር አጥቶ ሕዝባችን የተያያዘው ሰላማዊ ትግል ፈተና ውስጥ ሲገባና ለአረመኔዎች ጨካኝ ዱላ ተዳርጎ ተስፋው እንዲኮስስ ሲደረግ በሃዘኔታና በአቅመ-ቢስነት ተመልካች ሳይሆን እንደማንኛውም ሃላፊነት መውሰድ ያለበት የፖለቲካ ድርጅት ሃላፊነት ተቀብሎ አገሪቱንና ሕዝቧን ከዚህ አጣብቂኝ ለማውጣት አጥብቆ መሥራት ይጠበቅበታል። ግዴታም አለበት። ከዚህ ታሪካዊ ሃላፊነት እራሱን ሊያገል ፈጽሞ አይቻለውም። ይኸንን አገራዊና ብሔራዊ ሃላፊነት መወጣት አቅቶት፥ አንገቱን አሸዋ ውስጥ ቀብሮ ቀን መቁጠርም ሆነ በአቅመ-ቢስነትና እርባና-የለሽነት ሚሸሾ መጥፋትን መምረጥ ፈጽሞ የማይጠበቅበት ድርጅት ነው። ስህተቶቹን በድፍረትና የተንዛዛ ጊዜ ሳይሰጥ በማረምና የሚስተካከለውን በማስተካከል የበኩሉን ታሪካዊ ግዴታ ለመወጣት ችሎታው አለው። ስለሆነም በተለይ ከፍተኛ የሃላፊነት ቦታ ላይ አስቀምጧቸው የነበሩት ሁለት ግለ-ሰቦች የኅብረቱን ተመራጮች ይዘው የአቶ መለስን የፖለቲካ ሕይዎት ነፍስ ለመዝራት በወሰዱት ፓርላማ የመግባት እርምጃ የተናጋው የኅብረት ይዞታ ተስተካክሎ ትክክለኛ አቋሙን ሕዝብ በተሻለ መንገድ እንዲያውቀው እየተደረገ፥ ድርጅታዊ አቅሙን ማሳደግና መገንባት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። እዚህ ላይ ግልጽ መደረግ ያለበት ጉዳይ አለ። ምርጫ ቦርድ እንዳቸነፉ እውቅና የሰጣቸው 52 የኅብረቱ ተወዳዳሪዎቻችን ከኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ) እና ከደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ደቡብ ኅብረት) ሲሆኑ በተለይ ቀደም ሲል በተጠቀሰው በአገር-አቀፍ ደረጃ የኅብረቱ ተወዳዳሪ የነበሩ አባሎቻችን ጉባዔ ላይ እያንዳንዱ ተሳታፊ ከሞላው ቅጽ መንፈስ ውጭና ጭራሽ የተገላቢጦሽ ሁሉም ፓርላማ ለመግባት እንዲወስኑ ያስገደዳቸው ሁኔታ በትክክል መታወቅ ይኖርበታል። ከየድርጅቶቹ አመራር ደረሰ ተብሎ በአንዳንድ ግለሰቦች ከተነገረው ከፍተኛ ጫና ውጭ በዝርዝር መረጃ በትክክልና በግልጽ ማወቅ ያስፈልግ ይሆናል። ያም ሆነ ይኸ ኅብረቱ እንደ ኅብረት የፖለቲካ ሕይዎቱን ማቆየት የሚችሉ የማይናቁ እርምጃዎችን ወስዷል፥ ትግሉም መሥመር እንዳይስት የበኩሉን ጥረት አድርጓል። በቀድሞ መሪዎች ላይም ከኃላፊነት ማስወገድ እስከ አባልነት መሰረዝ ድረስ እርምጃ የወሰደው የኅብረቱን ደኅንነትና መተክላዊ አቋም ከማስጠበቅ አኳያ ነው። ይኸንን እርምጃ በተመለከተ ለምን የሚለው ብዙ የሚያወዛግብ ባይሆንም እንዴት ለሚለው በአጭሩ መግለጹ አስፈላጊ ይሆናል። ይኸንን

እርምጃ በተመለከተ በመጀመሪያ ሁለቱን የቀድሞ መሪዎች ከሃላፊነት እንዴትና ለምን እንደተወገዱ ኅብረቱ ለመላው የምርጫ ተወዳዳሪዎች (ፓርላማ ለገቡ ጭምር) ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም በጻፈው ግልጽ ደብዳቤ ላይ በኋላም በሁለተኛ አስቸኳይ ብሔራዊ ሸንጎ ጉባዔው ውሳኔ መሠረት ከአባልነት ለምንና እንዴት እንደተሰረዙ በተገቢ ተገልጿል። በተጠቀሰው ግልጽ ደብዳቤ ላይ ምክንያቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

“… ከአጠቃላዩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከግማሽ በላይ የሆነው ማለት 299 መቀመጫ ውዝግብ ባለበት ሁኔታ …. ኅብረታችን ከአሰለፋችሁ ብቁ ተወዳዳሪዎች አምሾ (አንድ አምስተኛው) ቁጥር ብቻ “አልፋችኋል” በተባለበትና የቀሩት ድላቸውን የተነጠቁና ድምፃቸው የታፈነ እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸው አባሎቻችንና ደጋፊ ወገኖቻችን ለማያባራ እንግልትና ስቃይ በተዳረጉበት፥ በውጭ ታዛቢዎች ምስክርነት ሳይቀር እንደተረጋገጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመስዋዕትነቱ ያገኘውን መሰል የሌለው ድል በገፍና በግፍ በተሰረቀበና በተነጠቀበት፤ ታዳጊ ወጣቶች ሳይቀሩ ለዚህ የተሰረቀ ድምፅ መመለስና መከበር ክቡር መስዋዕትነት በከፈሉበትና ሕዝቡ በአጠቃላይ ከዚህ ኋላ-ቀር የአመፅ ሥርዓት ጋር እየተናነቀ ባለበት፤ ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ በሥልጣን ላይ መቆየትን እንደ ኀልውና ዋስትና በማየት የሕዝብን ድምፅ በጠራራ ፀሐይና በአደባባይ በመዝረፍ ለሌላ አምስት ዓመታት ከመቸውም ጊዜ የባሰ ፍጹም አምባ-ገነን የአመፅና የሽብር አገዛዙን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለመጫን በሚውተረተርበት፤ የአቸናፊና ተቸናፊ ስሜት በሌለበት የጋራ ችግሮቻችንን በሰከነ መልክ በጋራ ማየት እንዲቻል ለአገር ሰላምና መረጋጋት ሲባል ለተሸነፈው ኢሕአዴግ “ብሔራዊ የአንድነት የሽግግር መንግሥት” ጥሪ በቀረበበት፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የግንቦት ድሎች መከበር አገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሰላማዊና ሕጋዊ ትግላቸውን በተያያዙበት፤ ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር የሚደረግ ማናቸውም ድርድር በግልጽና በሕዝብ ትግል የታጀበ እንዲሆን በተወሰነበት፤ የትግል አጋሮቻችን ከሆኑ ሌሎች ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በተነጠለ፤ ወዘተ… ሁኔታ ኅብረታችን ወደ ፓርላማ መግባት/አለመግባት በሚለው ጉዳይ ላይ የኅብረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰፊ ተከታታይ ውይይቶችን አድርጎ፤ የኅብረቱን የፖለቲካ ፕሮግራምና በአገራችን ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመመሥረት መተክላዊ እምነትን፥ የሸንጎ ጉባዔና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የጋራ ውሳኔዎችን፥ ወዘተ … ባከበረና በተከተለ መልክ ኅብረታችን ወደ ፓርላማ መግባት እንደሌለበት በአሥር ለሦስት ድምፅ መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም መወሰኑ ይታወቃል።

የኅብረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔ ይኼ ሆኖ እያለ ኅብረታችንን ከምሥረታው ጀምሮ በሊቀ-መንበርነትና በምክትል ሊቀ-መንበርነት በየተራ ሲመሩ የቆዩ ሁለት አባሎቻችን፥ ማለትም ዶ/ር በየነ ጴጥሮስና ዶ/ር መረራ ጉዲና፥ ቢያንስ ኅብረቱ ከጣለባቸው ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ በራሳቸው ፈቃድ ሳይለቁ የጋራ ውሳኔን በተግባር በመጣስ ወደ ፓርላማ ገብተዋል።

እንደ ኢዴኃን ያለ ለሕግ የበላይነት የሚታገል ድርጅት ለራሱ ሕግ ተገዥ አለመሆን የማይጠበቅ ብቻ ሳይሆን የማይታሰብም ጉዳይ ነው። በመሆኑም የጉዩን አሳሳቢነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሁሉም የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ባሉበት ጉዳዩን ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት መተዳደሪያ ደንባችን በሚያዘው መሠረት አባል ድርጅቶች ስብሰባ እንዲጠራላቸው ጠይቀው አራት ጊዜ ሙከራ ተደርጎ በ“አልተመቸኝም” ና በ“የለሁም” ምክንያት ሁሉም የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የተገኙበት ስብሰባ ማድረግ አልተቻለም። ይሁንናም በመተዳደሪያ ደንባችን መሠረት ከምልአተ-ጉባዔው ቁጥር በላይ በተገኙበት ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ ልዩ ስብሰባ በማካሄድ በጥሞናና በጥልቀት ተወያይቶ በመተዳደሪያ ደንባችን አንቀፅ 7.4.1 እና አንቀፅ 7.4.2 መሠረት ሁለቱ አባላት ውሳኔው ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ ከሃላፊነት እንዲወርዱ ተወስኗል።..እንደ እውነቱ ከሆነ እራሳቸው ትተውት ከሄዱት የሃላፊነት ቦታ ነው ተነስተዋል የተባለው። … ውሳኔአቸው በምንም መልኩ የኅብረቱን ብሎም የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

ውሳኔው ለምን የተጠቀሱት ሁለት ግለሰቦች ባሉበት አልተወሰነም የሚለው ጥያቄ በብዙ የኅብረቱ አባላትና ደጋፊዎች ዘንድ ተነስቷል። አግባብ ያለውና ትክክለኛ ጥያቄ መሆኑን የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴው ያምናል። ሆኖም ሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔውን በወሰነበት ጊዜ እንዲወስን የተገደደበት ሁኔታ በደንብና በግልጽ ሊታወቅ ይገባል።

አንደኛ፡- ምንም እንኳ በማንኛውም ዴሞክራሲያዊ የጋራ አሠራር አብዛኛው በተገኘበት ውሳኔ ላይ መድረስ ያልተለመደ እንግዳ ነገር ባይሆንም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ክፍሎች በተገኙበት መወሰን የተሻለና የተመረጠ ይሆናል። ይኽን ልዩ ጉዳይ በተመለከተ ግን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁሉ ሥራ-አፈጻሚው ኮሚቴ ሁሉም በተገኘበት ስብሰባ ለማድረግ በተደጋጋሚ ቢሞክርም ከግለ-ሰቦቹ ፍላጎትና ትብብር አልታየም። በመሆኑም መቸ ሊመቻቸው እንደሚችልና እንደሚገኙ ምንም ዓይነት ማረጋገጫ በአለመገኘቱ፤

*ሁለተኛ፡- ሁለቱ ግለ-ሰቦች ኅብረቱ በጋራ ወስኖ ፓርላማ ገብቷል የሚል የተሳሳተ መረጃ መስጠት በመቀጠላቸውና ዜና ማሰራጨት በመጀመራቸው ኅብረቱ የቆመለት የተጭበረበረ የሕዝብ ድምፅ የማስከበር ሰላማዊ ትግል ላይ ከፍተኛ ብዥታ በመፍጠሩ፥ የኅብረቱ ዋና የትግል ትኩረት ላይ በጣም ያጠላና አባላት ላይ ከፍተኛ የስሜት መሰበር በማድረሱ ሥራው ላይ እንቅፋት በመሆኑና ለአባሎቻችን፥ ለደጋፊዎቻችንና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኽንን ግልጽ ማድረግና ትኩረቱን መልሶ ወደ ትግሉ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤*
*ሦስተኛ፡- ትላንት የተጭበረበረው የሕዝብ ድምፅ ይከበር ብለው የወደቁ ዜጎች ደም ሳይደርቅ፥ ለዚሁ የመብት ጥያቄ ብዙ አባሎቻችን ፍዳቸውን እያዩ ባሉበት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አታጋይ ድርጅቶቹ የተጭበረበረን የምርጫ ውጤት እንደማይቀበሉና በዚህ ሁኔታ የሚቋቋም ፓርላማም ሆነ በሱ የሚቋቋም መንግሥት ሕገ-ወጥ እንደሆነ በተነገረበት፥ ለዚህ መሠረታዊ የሕዝብ መብት መከበር እንደሚታገሉና ለዚህም ልዩ ልዩ የትግልና የትብብር ጥሪዎችን እንዲሁም የመፍትሔ አሳብ ባቀረቡበትና በዚህም ቃላቸው ሕዝብ በተስፋ አንጋጦ በሚያይበት ወቅት፥ በተለይ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ አዲስ የተቋቋመው የሽፍጥ ፓርላማ ተወካይ ቡድን አባል ሆነው በእንግሊዝ አገር መገኘታቸው የሰጠውና የፈጠረው ' አገር ሰላም ነው፥ ሁሉም ያለውን ሁኔታ ተቀብሏል፥ በመሆኑም ይኽ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ነው፥ ወዘተ... ' የሚል ስሜት የኅብረቱን አባላትና ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ሕዝቡን በእጅጉ ያሳዘነ፥ ያስቆጣና አንገት ያስደፋ፥ ለኅብረቱ አመራርም ሁኔታውን ለማስረዳት ያዳገተና ትግሉን በእጅጉ የተፈታተነ እርምጃ በመሆኑ፤ ነው የኅብረቱ የሥራ-አፈጻሚ ኮሚቴ ሁለቱን አባላት ከሃላፊነታቸው እንዲነሱ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም በስብሰባው በተገኙት የኮሚቴ አባላት ሙሉ ድምፅ ... በኅብረቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 7.4 መሠረት የወሰነው።....”*

ከጥር ፩ ቀን እስከ ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ለአራት ቀናት የተካሄደው የኅብረቱ ሁለተኛ አስቸኳይ የብሔራዊ ሸንጎ ጉባዔም ይኽንኑ በተመረኮዘ ሁለቱን የቀድሞ አባላት ከአባልነት መወገዳቸውን መወሰኑን ሲገልጽ፤ *“... የግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የምርጫ ውጤት በገዥው ፓርቲ በተጭበረበረበትና የሕዝባችን ድምፅ በተሰረቀበት ሁኔታ የኅብረቱ ተመራጮች በሕገ ወጥ መንገድ በተሰየመ ፓርላማ ውስጥ መቀመጫ መያዛቸው የሕዝብን መብት ማረጋገጥና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን የሚያካትተውን የኅብረቱን ዓላማ የሚጻረር መሆኑን በመገንዘብ የኅብረቱ ተመራጮች በፓርላማ መቀመጫ እንዳይዙ የኢዴኃን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በአብላጫ ድምፅ የወሰነውን ውሳኔ ሕጋዊነት፥ አግባብነት፥ ወቅታዊነትና ትክክለኛነት አጢኖ የኢዴኃን ብሔራዊ ሸንጎ በሙሉ ድምፅ አጽድቆታል።”....“.... የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ውሳኔ በመጻረር የፓርላማ መቀመጫቸውን በያዙና የጋራ አሠራርን በጣሱ የኅብረቱ የቀድሞ የወቅቱ ሊቀ መንበርና የቀድሞ የወቅቱ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ መንበር ላይ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በኅብረቱ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 7.4.1 እና 7.4.2 መሠረት ሁለቱ ተመራጮች ከኃላፊነት እንዲነሱ የወሰደውን ውሳኔ ጉባዔው በቋሚነት አጽድቆታል።...”*

ኢዴኃን የሕዝብ ድምፅ በተጭበረበረበትና ሕዝቡም ለድምፁ መከበር እየተዋደቀ ባለበት ሁኔታ በኅብረቱ ስም ተወዳድረው አቸንፉችኋል የተባሉ አባሎቻችን በኅብረቱም ውስጥ ከኅብረቱም ውጭ ካሉ ከሌሎች የትግልና የዓላማ አጋሮቻቸው ተነጥለው በአቶ መለስ ኢሕአዴግ ሙሉ ቁጥጥር ሥር በሆነ፥ የገዥውን ፓርቲ ቁንጮዎች በሥልጣን ላይ ማቆየት ብቻ ዋነኛ ዓላማውና ተግባሩ የሆነን አካል መቀላቀል ማለት ገዥው ፓርቲ ለሚያደርገውና ለሚወስደው እርምጃ ሁሉ የሕጋዊነት ሽፋን መስጠት መሆኑን፥ ሕዝቡም ለመብቱ መከበር ያደረገውን መስዋዕትነት የሚያራክስ፥ በሕዝቡና በገዥው ክፍል መኻል ያለውን የጠራ የኃይል አሰላለፍ በመቀየር ወይም በመበረዝ አንድ ወገን የቆመውን ተቃዋሚና ሕዝብ እየሰፋ በሚሄድ መልክ የሚገማምስ፥ ገዥው በጉልበትና በፍጹም አምባ-ገነንነት ብቻ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ባለው ፍላጎት የአፈና እርምጃዎችን የሚያደፋፍር፥ ሕዝባችን የሚያደርገውን የመብት ማስከበር ጥረት ሁሉ የሚያዳክም፥ በዚህም ምክንያት ገዥው ክፍል ጊዜ ገዝቶ በሕዝቡ ላይ የበቀል እርምጃ እንዲወስድ የሚያመቻች፥ በሕዝቡ ድካምና መስዋዕትነት ተቀነጫጭበውም ይሁን መገኘት የቻሉ መሠረታዊ መብቶችንም ጨርሶ እንዲወድሙ የሚፈቅድና ከሚገመተው በላይ ትግሉን መልክ ለሚያሳጣና ለሚያመሰቃቅል አደገኛ ሁኔታ እንደሚያስከትል አሳስቧል፥ አስጠንቅቋል። ገዥው አካል በዚህ መልክ በሕዝባችን ላይ ለሚያደርሰው ጥፋት፥ በደልና ስቃይ ሁሉ አቶ መለስና

ኢሕአዴግ ብቻ ሳይሆኑ እያንዳንዱ አጅቦ የገባ ተመራጭ ሁሉ ተጠያቂ እንደሚሆን ለማሳሰብ ተሞክሯል። በኅብረቱ እምነት የሕዝቡ ትግል ውጤት ማስመዝገብ የሚችለው የተወሰኑ ተመራጮች ምንም ነፃነት በሌለበትና ሊኖርበትም በማይችል በተጭበረበረ የውሸት ፓርላማ ውስጥ በአገልጋይነት ተቀምጠው በሚያደርጉት የጥቂት ደቂቃዎች የይስሙላ ተቃውሞን በማሰማት አይደለም። የአጠቃላይ ሕዝባችንን የሥርዓት ለውጥ ተጋድሎ በመቶ ሰባ አካቢ ቁጥር ባላቸው የተሸበቡ የፓርላማ አባላት መተካት ፈጽሞ አይቻለውም። በኅብረቱ ስም ወደ ፓርላማ የገቡ አባላት ፓርላማው እንደተከፈተ ገዥው ፓርቲ ፓርላማ ላለመግባት በወሰኑ የቅንጅት ተመራጮች ሕገ-ወጥ እንደሆኑ ወገዛ ሲደርስና የተመራጭ ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸውን ለመግፈፍ በገዥው ፓርቲ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ በመቃወም ከፓርላማ መውጣታቸውን ብዙ ወገኖች ተዓምር እንደተሠራና "ያው እዚያም ሆነው ተቃውሞ በማሰማት መታገል እንደሚቻል አሳይተዋል" በማለት አጉል የተሞኙ ነበሩ። ኅብረቱ ያኔም አሁንም የሚለው ግን ማንኛውም የፓርላማ አባል በፓርላማ ውስጥ የቀረበን አንድ ሃሳብ ተቃውሞ ከፓርላማ መውጣት የአፈጻጸሙ ደረጃ ይለያይ እንጅ በመሠረቱ ድምፅ እንደመስጠት፥ ድምፅ ከመስጠት እንደመቆጠብ ከወንበር ሳይነሱ ተቃውሞን እንደማሰማት የሚቆጠር የአገላለጽ ዘይቤ ብቻ እንጅ የተለየ ወይም አዲስ እርምጃ አይደለም። ምናልባት ያኔ ተቃውመው እንደወጡ የቀረበው ሃሳብም ይሁን ሌሎች ኅብረቱም ሕዝቡም ያነሷቸውና እየታገሉላቸው ያሉ ጉዳዮች እስከሚስተካከሉ ወይም መልስ እስከሚሰጥባቸው ድረስ አንመለስም የሚል አቋም ቢይዙ ኖሮ በእምነት ላይ የተሠራ ሕዝባዊ ዓላማን የተመረኮዘ አድራጎት ነፀብራቅ ሊሆን በቻለ ነበር። ያ አድራጎት ግን ለገዥው ክፍል የ"ዴሞክራሲያዊነት" አዲስ ቅብ ከመስጠት ውጭ የአቋም ለውጥ እንደተወሰደ ቆራጥ እርምጃም ሆነ ለተቃዋሚውና ለሕዝብ እንደተሠራ ውለታ ሊቆጠር ፈጽሞ አይችልም።

ኅብረቱ በአገር ውስጥ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ቅድመ-ምርጫ በነበረው ሁኔታ ማድረግ ይችል እንደነበረው ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዳያደርግ በገዥው ፓርቲ ሕገ-ወጥ እርምጃዎች ምክንያት ፈጽሞ የማይቻል እየሆነ በመምጣቱ ትግሉን በህቡዕ ማካሄድ የግድ ሆኗል። ይኸንን ተግባር በሃላፊነት የሚያስተባብሩ አንድ ም/ሊቀ-መንበርና አንድ እረዳት ፀሐፊ እንዲመደቡ የኅብረቱ ሁለተኛ አስቸኳይ የሸንጎ ጉባዔው በወሰነው መሠረት ለተግባራዊነቱ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ጽ/ቤቶቹን አጠናክሮ፥ ከጎረቤት አገሮች ጀምሮ በውጭው ዓለም ያለውን ትግል ለማስተባበር የተቻለውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። በተለይም የአውሮጳ ፓርላማ ውሳኔ እንዲተላለፍ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። በውጭው ዓለም በዲፕሎማሲው ረገድ በተለይ በአውሮጳ፥ በአሜሪካና በካናዳ የኢሕአዴግን የግፍ እርምጃዎች በማጋለጥ፥ በግፍ የታሰሩ ዜጎች ያለቅድመ ሁኔታና በአስቸኳይ እንዲፈቱ በመጠየቅ፥ ከምርጫው በተያያዘ በኢሕአዴግ መንግሥት የተፈጸሙ የግፍ እርምጃዎችን የሚያጣራ አንድ ዓለም-አቀፍ አጣሪ አካል እንዲቋቋምና ተጠያቂዎቹ ታውቀው ለፍርድ እንዲቀርቡ እንዲደረግ በመጠየቅ፥ የሕዝብ ድምፅ ስለሚከበርበት፥ ወዘተ.... በግሉም ሆነ ከሌሎች ጋር በመሆን እንቅስቃሴዎች አድርጓል። እያደረገም ይገኛል።

ሆኖም የደረሰበት መናጋት ጥረቶቹን አኮሰሰውበታልና እራስን ሳያጠናክሩ አመርቂ ሥራ መሥራት ስለማይቻል የበለጠ ድርጅታዊ አቅሙን ለመገንባት የሚያስችሉ እርምጃዎች መውሰድ ይኖርበታል።

<u>ሁለተኛ ፡- የጋራ ሥራዎች፤</u>

ኢዴኃኅ ከራሱ የውስጥ አሠራር ጀምሮ የተቃዋሚውን አንድነት ማጠንከር ቅድሚያ የሰጠው ጉዳይ ነው። ኅብረቱ የቆመላቸውን መተክላዊ አቋሞችና የሚከተላቸውን መሥመሮች በጠበቀ ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት ያስመዘገባቸውን ድሎች ለማስጠበቅ የበኩሉን ድርሻ በብቃት ለመወጣት ያላቋረጠ ጥረት አድርጓል። በአለው የአገሪቱ የተወሳሰበ ተጨባጭ ሁኔታ የተሻለና አስተማማኝ ውጤት ማስገኘት የሚቻለው

የተቃዋሚው ክፍል ከተናጠል ጉዞ ይልቅ ግልጽ ሕዝባዊ ዓላማ ላይ ያተኮረ ጠንካራ ትብብር ሲኖረውና ይኸም በተግባር ሲገለጽ ብቻ መሆኑን ኅብረቱ ያምናል። ከዚህም መተክላዊ አቋሙ በመነሳት ኅብረቱ በተለይም ከቅንጅቱ ጋር በመሆን የሕዝቡን ትግል ከመቀልበስ ለማዳንና የግንቦትን ድሎች ለማስከበር የተቀናበረ የጋራ ትልምና ስትራቴጂ መከተል እንዲቻል የቅርብ ምክክር በማድረግ ተጨባጭ ተግባራትን ለማከናወን ሞክሯል። በዚህ ረገድ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው ከላይ የጋራ ወሳኝ አካል ከመፍጠር ጀምሮ ልዩ ልዩ የተግባር ኮሚቴዎችን በማቋቋም የሕዝቡን ድምፅ ለማስከበር የሚደረጉ እንደ ሰላማዊ ሰልፍ፥ ቤት ውስጥ ከትቶ የመቀመጥ፥ ወዘተ... የመሳሰሉ ሰላማዊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችና ትግሉ የሚጠይቃቸውን ጠንካራ ወቅታዊ ሥራዎች በጋራ መሥራት እንዲቻል የተሻለ ቅንብርና ትብብር እንዲደረግ በተለያዩ ጊዜዎች ልዩ ልዩ አሳቦች ቀርበዋል። ገዥው ፓርቲ መልሶ እንዳይጠናከርና ምላሽ ሰጭ ለማድረግ እንዲቻል ተቀባይነት ሊኖራቸው የሚችል አዳዲስ የጋራ እቅዶችን (እንደ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት የማቋቋም፥ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ እንደመጥራት ዓይነት፥ ወዘተ...) በጋራ ለማድረግ ተሞክሯል። ከምርጫው በፊትም አንዳንድ የጋራ አቋሞችን የሚገልጹ የጋራ መግለጫዎችን ከማውጣት ጀምሮ ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር የሚደረጉ ድርድሮችን በጋራ ለማስተናገድ ተችሏል። በተለይ ምርጫው ከተከናወነ በኋላ የተከሰተውን ዝብርቅርቅ ሁኔታ መልክ ለማስያዝና የሕዝብ ድምፅ እንዲከበር የቅርብ ግንኙነት እየተደረገ አንዳንድ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ተችሏል። ሆኖም በአብዛኛው በተወካዮች መኻል የመተማመን ችግር ስለነበር የተሻለ ተቀራርቦ ብዙ ውጤት አስመዝጋቢ ተግባር ማከናወን አልተቻለም። እዚህ ላይ በተለይ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ አለ። ኅብረቱ በአለው ሁኔታ ወደ ፓርላማ የመግባትና ያለመግባትን ነጥብ በተመለከተ በልዩ ልቱ እርከኖች ጊዜ ወስዶ ከፍተኛ ውይይቶችንና የአሳብ ልውውጦችን በተደጋጋሚ አድርጓል። በመጨረሻ ላለመግባት ከመወሰኑ በፊት የቅንጅቱን ከፍተኛ አመራር ለማግኘት ብዙ ተሞክሯል፥ ይኸን ውሳኔም የጋራችን እንዲሆን በተናጠል ከመወሰናችን አስቀድመን ተመሳሳይ አቋም እንድንወስድ ለማድረግ ከፍተኛ ጥርቶች አድርገናል። ቢያንስ መልእክቶቻችን እንዲደርሱ ተደርጓል። በቅንጅቱም በኩል በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ከፍተኛ ውጥረትና የውስጥ ችግር ስለነበር የጠበቅነው ምላሽ በወቅቱ አልተገኘም። ኢሕአዴግ ፓርላማውን የሚከፍትበት ቀን እየተቃረበ በመምጣቱ ኅብረቱ የግድ መወሰን ስለነበረበት ከቅንጅቱ የጠበቀውን ምላሽ ሳያገኝ ላለመግባት መወሰን ነበረበት። ከተወሰነ በኋላም ቢሆን አብዛኛው የኅብረቱ ተመራጮች በኋላ ውሳኔ ጥሰው ከመግባታቸው በፊት ከቅንጅት ጋር ምክክር ለማድረግ ከፍተኛ ሙከራ ተደርጓል። እንደሚታወቀው ቅንጅቱ ፓርላማ ላለመግባት በእርግጠኝነት የመጨረሻ አቋም የወሰደው በፓርላማ መክፈቻ ዋዜማ ነበር።

ኢዴኃኅ በዚህ የጋራ ሥራ ጥረቱ ላይ ከቅንጅቱም በተጨማሪ ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችና በተለይም ከሲቪክና የሙያ ማኅበራት ጋር ግንኙነቶች አድርጓል። በተለይ ኢሕአዴግ በሕዝብ ላይ ያወጀውን የሽብር ጦርነት ለመቋቋምና በግፍ የታሰሩ ዜጎችን ለማስፈታት በሚደረገው ዲፕሎማሲያዊም ይሁን ሌሎች እንቅስቃሴዎች ኅብረተሰባችንን በስፋት ለማሳተፍ እንዲቻል ከሁሉም የፖለቲካ፥ የሲቪክና የሙያ ድርጅቶች እንዲሁም ስብስቦች ጋር የተባበረ ትግል ለማድረግ አንድ "አገር-አቀፍ የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል" እንዲቋቋም ደብዳቤ በመጻፍ፥ በልዩ ልዩ መንገድና በአካል በማግኘት ውጤት ያለው ሥራ ለመሥራት ሞክሯል። ይኸ የጋራ ጥረትም የፖለቲካ ድርጅቶች እየከፋ የመጣው የአገሪቱ ሁኔታ የሚጠይቀውን ሁሉንም ኃይሎች ያሰባሰበ የተባበረ ትግል ለማድረግና አልፎም ዘለቄታዊ መፍትኄ ለመሻት የሚያስችል የተቃዋሚው ክፍል "ሁሉን-አቀፍ አገራዊ ጉባዔ" እንዲጠራ ውይይቶችን በማድረግ ላይ ነው።

<u>ሦስተኛ፡- የሕዝብን ጠንካራ ተሳትፎ ማሳደግና ማረጋገጥ፤</u>

ትግሉን ለውጤት ለማብቃት ባለጉዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግሉ ዋና አንቀሳቃሽ ሆኖ መቀጠሉ ተገቢ በመሆኑ ተቃዋሚው ክፍል የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ግልጽና ሕዝቡ እያወቀውና ሙሉ ተሳታፊ እየሆነ እንዲቀጥል፥ ገዥው ፓርቲ ፋታ አግኝቶ ሕዝቡን

እንዳይከፋፍልና በድርጅቶች ላይ አመኔታው እንዳይመነምን በውስጥም በውጭም ሕዝቡን ማደራጀት፥ አዳዲስ የትግል ዘዴዎችና መንገዶች እየተቀየሱ ግልጽና የማያሻሙ መመሪያዎችና የትብብር ጥሪዎች በማቅረብ የትግሉን ግለት ለመጠበቅና ለውጤት ለማብቃት የሚያስችል በሳል አመራር መስጠት አስፈላጊም ወሳኝም መሆኑ ይታወቃል። ይኸንንም የሕዝብና የድርጅቶች አስፈላጊ የትግል ትስስር በተግባር ለመተርጎም በኅብረቱ በኩል፣

ሀ) ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ኅብረቱ ወደ ምርጫ ለመግባት የወሰነው ሕዝብን ለማደራጀትና ሕዝቡ የትግሉ ባለቤት እንዲሆን የሚያስችል እንቅስቃሴ ለማድረግ በመሆኑ ይኸንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ለምርጫ ተወዳዳሪነት በሚመለመሉና ኅብረቱን ወክለው በሚሳተፉ ታጋዮች አማካይነት ቀጣይነት ያለው ድርጅታዊ ሥራ ለመሥራት ነበር። በዚህ እረገድ ከአቅም ማነስና ከአሠራር ድክመቶች የተነሳ እንደታሰበው ሰፊ እንቅስቃሴ ባይደረግም ሙከራዎቹ ግን አጥጋቢ ነበሩ። ቀደም ሲል ኅብረቱ አውጥቶት በነበረው ስልት መሠረት የተቃዋሚው የምርጫ ተወዳዳሪዎች የጋራ ጉባዔ እንዲደረግና የምርጫው ሂደት፥ ክንዋኔና ቀጣይ ትግል ላይ ግምገማ እንዲደረግ ብዙ ጥረት ተደርጓል። ተቃዋሚው በአንድ መስመር ባለመቆሙና ኅብረቱም ወደ ምርጫው በሙሉ ልቡ የገባው በጣም ዘግይቶ ስለነበር በተጨማሪም ከነበረው አንዳንድ የአሠራር ድክመት ሌላ የገንዘብ አቅሙ እጅግ ደካማ ስለነበር ቅድመ-ምርጫ የእጩ ተወዳዳሪዎች ጉባዔ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም። ሆኖም ቀደም ሲል በታሰበው መሠረት ኅብረቱ ከምርጫው ሂደት እስከ ፍጻሜው ከዚያም የምርጫውን ውጤት ተከትሎ የተከሰተውን ሁኔታ በተገቢና በተጨባጭ በመገምገም፥ የዴሞክራሲ ሂደቱን በሚያጎለብትና የሕዝቡን ትግል በሚያጠናክር መልክ የወደፊት እንቅስቃሴውን ለመተለም እንዲያግዘው በሚል ኅብረቱን ወክለው በአገር-አቀፍ ደረጃ የተወዳደሩ ሕዝብ አመኔታ የጣለባቸውን ታጋዮች በአዲስ አበባ ላይ የሦስት ቀን ጉባዔ በማድረግ ሰፊና ጥልቅ ውይይት ተካሂዶ፥ ጉባዔው የምርጫውን ውጤት እንደማይቀበለው፥ የሕዝቡን ድምፅ ለማስከበር የሚደረገው ሰላማዊ ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል፥ ኅብረቱ የወሰዳቸውን እርምጃዎች በተለይም ከቅንጅቱ ጋር በመሆን ብሔራዊ የጋራ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥሪን እንደሚደግፍ፥ ወዘተ.. ውሳኔ አስተላልፎና የጋራ ትግል ጥሪ አቅርቦ፥ ለኅብረቱ አመራር አሳቦች አስተላልፎ፥ ለኅብረቱም ቀጣይ እርምጃ እንዲረዳ ታስቦ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ እያንዳንዱ ተወዳዳሪ በመሙላት እጅግ ጠቀሜታ ያለው ተግባር ተፈጽሟል። ይኸ የሕዝብ ተወካዮች ስብሰብ የሚያደርገው ግምገማ ተጨባጭ ውሳኔውም ሕዝባዊ እንደሚሆን ክብደት ያለውና የታመነ ጉዳይ ነው። ስለሆነም ይኸ ጉባዔ ያስተላለፋቸው ውሳኔዎችና እያንዳንዱ ተመራጭ የሞላው ቅጽ በተለይ ፓርላማ መግባት አለመግባት በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የኅብረቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በኋላ ለወሰዳቸው ውሳኔዎች በጣም ጠቅመዋል።* 3

በዚህ የተወዳዳሪዎች ቅጽ በግልፅ እንደተቀመጠው በአጠቃላይ ቅጹን ከሞሉት ተወዳዳሪዎቻችን መኻል አሥራ ሦስት ወይም ከሞላ ጎደል ከመቶ አምስት እጅ በታች (4.3%) ብቻ ፓርላማ መግባቱ ምናልባት ትግሉን ሊጠቅም ይችል ይሆናል ሲሉ የቀሩት ማለት ከመቶ ዘጠና አምስቱ በላይ ባለው ሁኔታ ፓርላ መግባቱ ጠቀሜታ እንደሌለው ነው የገለጹት። ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶች ሰላማዊ ትግሉ ውጤት እንደማያመጣና የሕዝቡን ድምፅ ለማስከበር ኅብረቱ አማራጭ የትግል ስልቶችን እንዲከተል የሚጠይቁ ይገኙበታል።
የሕዝብ ድምፅ በግልጽ በተጭበረበረበት ሁኔታ ኅብረቱ ወደ ፓርላማ ላለመግባት ሲወስንም ከሌሎች ሁኔታዎች በተጨማሪ ሕዝባችን እንዲወክሉት አመኔታውን ጥሎባቸው የመረጣቸውን ተወዳዳሪዎቻችን ፍላጎት በተከተለ መንፈስ ነው።

የኅብረቱን ውሳኔ በመፃረር የኢሕአዴግን ፓርላማ የተቀላቀሉት የኅብረቱ አባላት የጣሱት የራሳቸውን ውሳኔና የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎት ጭምር ነው።

---

** 3 ስለዚህ የተወዳዳሪዎች ጉባዔና የተላለፉ ውሳኔዎች ሙሉ ቃል በነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የወጣውን መግለጫ ይመለከቷል።*

በኀብረቱ በኩል ለምርጫ ተወዳዳሪነት ካሰለፍናቸው ታጋዮች ጋር የሚኖረው ግንኙነትና የትግል ትስስር በአንድ የምርጫ ወቅት ብቻ ተገናኝተን ምርጫው ሲያልቅ ውጤቱን ተቀበልንም አልተቀበልንም፥ በየመጡበት ተበታትነው ዘንቦ ተባርቆ በቀጣዩ ዙር እንገናኝ ይሆናል በሚል የሚሰነባበት የዘፈቀደና ወረታዊ አካሄድ ሳይሆን እንቅስቃሴው ቀጣይነት ያለው መሆን ስለሚኖርበት፥ እነኝህ ታጋዮች የኀብረቱ ፖለቲካ መስመረኞች (ካድሬዎች) በመሆን ሕዝቡን እያደራጁ፥ ሕዝቡና ትግሉ ተሳስረው በመቀጠል ትግሉ ህያው እንዲሆን የማስቻል አካሄድ ነው።

ለ) ትግሉ በድርጅቶች ብቻ ከአዲስ አበባ በሚሰጥ መግለጫ እንዲወሰን ማድረግ ሕዝቡና ድርጅቶቹ እየተራራቁ እንዲሄዱ የሚያደርግ አካሄድ ስለሆነና ትግሉ በሕዝብ መታጀቡ ለትግሉ መቀጠል ዋስትና በመሆኑ ቢያንስ ለሁለት ቀን የሚዘልቅ የአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶችን፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፥ የገበሬዎች፥ የወጣቶች፥ የሴቶች፥ የተማሪዎች፥ የሠራተኞች፥ የሐይማኖት ድርጅቶች፥ ወዘተ... እስከ አንድ ሽህ አምስት መቶ የኅብረተሰብ ተወካዮች የሚሳተፉበት አንድ " የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ አገር-አቀፍ ጉባዔ " ለመስከረም ፳ እና ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ እንዲደረግ የኅብረቱ ሁለተኛ መደበኛ የሸንጎ ጉባዔ ውሳኔ አስተልፏል። ሰላማዊ ትግሉ እንዲቀጥል ታስቦ የቀረበ ይኸ አሳብ ለሕዝባችን የሚቀርበው ጥሪም ይሁን ለጉባዔው የሚቀርበው የመወያያ ሰነድ ዝግጅት ከቅንጅት ጋር በመሆን በጋራ እንዲሆን ነው የተወሰነው። ከእንደዚህ ዓይነት አገር-አቀፍ አካል የሚወጣ ውሳኔና የሚቀርብ ጥሪ የሕዝብ ውክልና ያለውና ሕጋዊነቱም አጠራጣሪ ያልሆነ፥ ተቀባይነትም የሚኖረው እንደሆነ ግልጽ ነበር። በመቀጠልም ይኸ አገር-አቀፍና ሁሉን አቀፍ ጉባዔ በሚያቀርበው ጥሪ መሠረት ሰኞ መስከረም ፳፪ ቀን ከአዲስ አበባ ጀምሮ በአገሪቱ ታላላቅ ከተሞችና በዓለም-አቀፍ ደረጃ ታላቅና ደማቅ የድጋፍ ሰልፍ እንዲደረግ ተወስኖ እስከተቻለው ድረስ ተግባራዊ እንዲሆን ተሞክሯል።

የታቀደው " የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ አገር-አቀፍ ጉባዔ " እንደታሰበው ተግባራዊ ሳይሆን የቀረውና የተጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ ያልቻለው በመጀመሪያ ለዚህ ጉዳይ ቅድሚያ ወስዶ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል ብለን የጠበቅነው ቅንጅቱን ሲሆን በቅንጅቱ በኩል የነበረው የመተባበር ሁኔታ ከሙሉ እምነት የመነጨና የሚጠበቀውን ያህል አልነበረም። በቅንጅቱ በኩል ኅብረቱ ይኸንን ጉዳይ ከወሰነ በኋላ ነው የነገረን የሚል ቅሬታ እንደነበረው በኋላ ተሰምቷልና ምናልባት ተሳትፎአቸው ቀዝቀዝ ያለው በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ። ሌላው ምክንያት በኅብረቱ በኩል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ይኸ ተግባራዊ እንዲሆን ዝርዝር መመሪያ ከሰጠ በኋላ ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ክፍሎች በተለይ የቀድሞው ሊቀ-መንበር ዶ/ር በየነ ከልብ እንዲገፉበት በቂ ጥረት አላደረጉም። ለምሳሌ በጉባዔው እንሲሳተፉ መጋበዝ የነበረባቸው ክፍሎችና የራሱ የኅብረቱ የምርጫ ተወዳዳሪዎች በጊዜው አልተነገራቸውም። ይኸም በአብዛኛው ገዥው ፓርቲ በጉዳዩ ላይ መልካም አመለካከት አይኖረውም ከሚል ፍራቻ እንደነበር ታውቋል። በመጨረሻም በገዥው ፓርቲ/መንግሥት ማስፈራራት ምክንያት ጉባዔውን ለማካሄድ ሰፊ ቦታ ማግኘት ያለመቻል ችግር ነበር። በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በኩል ይኸ እንደታወቀ ስብሰባው በምንም መንገድ መቅረት እንደሌለበትና ሰፊ ቦታ ካልተገኘ የተቃዋሚውን ቁጥር እስከ ግማሽ በመቀነስ ሰባት መቶ የሚያኸሉ የጉባዔ ተሳታፊዎች ካስፈለገ በድንኳን ውስጥ ጉባዔውን እንዲያደርጉው፥ ይኸም ካልተቻ ለስብሰባው በአደባባይ ላይ እንዲደረግ ተወስኖ ነበር። ይኸ ሁሉ እንደማይሆን ሲታወቅ ግን ቢያንስ ለዚሁ ጉባዔ ከአገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች የመጡ ተወዳዳሪዎች ቢቻል የቅንጅቱንና የኅብረቱን ተወዳዳሪዎች በማዛነቅ፥ ቢያንስ ግን ኅብረቱ የራሱን ቅንጅቱም የራሱን ተወዳዳሪዎች በየቢሮዎቻቸው በሰላሳና በአምሳ በቡድን በቡድን ከፋፍለው በአጀንዳው ላይ ውይይት እንዲደረግ ተወስነ። የመጨረሻው አማራጭ በኅብረቱ በኩል ተወዳዳሪዎቹን በኅብረቱና በኅብረቱ አባል ድርጅቶች ጽ/ቤቶች ውስጥ እንደምንም ተጣበው ስብሰባው ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል።

የአዳራሽ ስብሰባን የነፈገ መንግሥት ሰላማዊ ሰልፍ እንዲደረግ ይፈቅዳል ማለት ስለማይቻል እንደሰጋነው ለመስከረም ፳፪ ቀን ፺፯ ዓ/ም የታሰበውን ሰላማዊ የድጋፍ ሰልፍ ለማድረግ በአቶ መለስ የሚመራው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ፈቃድ እንደከለከለ ከኅብረቱ ዋና ጽ/ቤት በወቅቱ ሊቀ-መንበር አማካይነት ለማእከላዊ አመራር ተገለጸ፡፡ የማእከላዊ አመራር ሁኔታውን መዝኖ ምንም እንኳ ሕዝባችን ለጥሪው በጎ ምላሽ ለመስጠት በቁርጠኝነትና በጉጉት እንደተሰለፈ ቢታወቅምና ዝግጅቶች ቢደረጉም፥ ሕዝብን የመጣ ይምጣ ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ ውጣ ማለቱ ከላይ ሲታይ ቀላል መስሎ ቢሰማም ሃላፊነት የጎደለው አካሄድ ስለሚሆን የኅብረቱ የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ አስቸኳይ ስብሰባ ተጠርቶ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ አንድ የትግል መስመርም ሆነ ስልት ተግባራዊ እንዲሆን ለሕዝብ ከቀረበ በኋላ የምንቃወመው መንግሥት አይሆንም ስላለ አማራጭ መታገያ ስልት ለሕዝብ አለማቅረብና እርግፍ አድርጎ መተው የሕዝብን የትግል ወኔ የሚፈታተንና አግባብነት የሌለው ብቻ ሳይሆን የድክመት ማንፀባረቂያም ስለሚሆን ሰላማዊ የድጋፍ ሰልፉ ሊደረግበት ከታሰበው ከሰኞ መስከረም ፳፪ ቀን ጀምሮ ከአርባ ስምንት ሰዓታት ሳልበለጠ ጊዜ የገኘሁውን ክፍል ሕገ-ወጥ ውሳኔ እንደምንቃወም ለማሳየት ዜጎች በየመኖሪያ ቤታቸው ከትተው እንዲቀመጡ ጥሪ እንዲተላለፍ፥ ይኸም በቅንጅቱ በኩል ተቀባይነት እንዲያገኝና ጥሪው ለሕዝባችን በሁለታችን ስም በጋራ እንዲቀርብ እንዲደረግ፥ ሌሎች አማራጭ ተከታታይ የትግል ስልቶች እንዲዘጋጁ ተወሰነ፡፡

በዚሁም መሠረት ከቅንጅቱ ጋር ምክክር ተደርጎ በቅንጅቱ በኩል እርምጃው ከአርባ ስምንት ሰዓት ወደ ሦስት ቀናት ከፍ እንዲል ስለጠየቀ በዚሁ ስምምነት መሠረት በኅብረቱ ዋና ፀሐፊ በአቶ ደረጀ ከበደ በሚመራ ልዑክና በቅንጅቱ ም/ሊቀ-መንበር በወ/ ብርቱካን መደቅሳ የሚመራ ልዑክ ቡድን አማካይነት ይኸ የቤት ውስጥ ክተት ጥሪ በጋራ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቀረበ፡፡ ይኸ በሆነ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ በእንግዚዙ ተወካይ አምባሳደር ቦብ ደዋር እና በአሜሪካዋ ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ቪኪ ኸድልስተን አስተናባሪነት ከኅብረቱ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስና ከቅንጅቱ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር በተደረገ የጓዳ ድርድር፥ ከገኘሁው ፓርቲ ምንም ዓይነት ቀጥታ ቃል ሳይገኝ በስማ በለው፥ ገኘሁው ፓርቲና መንግሥት በተቃዋሚው ተመራጮችና ደጋፊዎች ላይ የወሰዳቸውንና የሚወስዳቸውን ሕገ-ወጥ እርምጃዎችና አስገዳጅ ጫናዎች እንዲያቆም ሳይደረግ፥ ከነጮቹ ተሰጠን ባሉት ባዶ ተስፋ ብቻ ተማምነው የድርድርን መሠረታዊ ሕግ በጣሰ መልኩና ድርጅቶቻቸውን (ኅብረትና ቅንጅትን) ሳያማክሩና የጋራ ውሳኔን በገሃድ በጣሰ ሁኔታ ለሕዝብ የቀረበው የቤት ውስጥ ክተት ጥሪ እንደተሰረዘ በቴሌቪዥን መግለጫ ተሰጠ፡፡

በዚህ በኢሕአዴግ ብቻ የተጻፈ የሚመስል በዶ/ር በየነና በአሜሪካ ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ቪኪ ኸድልስተን የተሰጠ መግለጫ የጋራ ውሳኔአችን ብቻ ሳይሆን የተሻረው ኅብረቱን በአጠቃላይም ተቃዋሚውን ፓርላማ ለመግባት እንደተስማማ የሚያስመስል ፈጽሞ መረን የለቀቀና እጅ እግርን አስሮ የሚሰጥ የአድር ባይና አጎብዳጅ ተግባር ተፈጸመ፡፡ በተቃዋሚው ስም የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል የውስጥ ሽርሽራ ተፈጸመበት፡፡ ዳግም ሰኔ ሦስት ተግባራዊ ሆነ፡፡ ይኸ እጅግ አሳፋሪና የገዘፈ ስህተት በየድርጅቶቹ መኻል በውስጣቸው፥ በቅንጅትና በኅብረት መኻል፥ በሕዝቡና በተቃዋሚው መኻል አፍጥቶ የመጣ ችግርን ወለደ፡፡ የልዩነት መስመር መፈጠር ጀመረ፥ እየሰፋ የሚሄድ ክፍተት ተንፀባረቀ፡፡ ይኸ እንደተሰማም የኅብረቱ ሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ ሌላ አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ በጉዳዩ ላይ ከዶ/ር በየነ ማብራሪያ እንዲሰጥ በማድረግ አካሄዱ ፈጽሞ ስህተትና ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ተገልጾ ተጨማሪ ውሳኔዎችን አስተላልፏል፡፡* *4*

በዚህ የሥራ አስፈጻሚ ስብሰባ ከተወሰኑት ውስጥ:- ከአሁን በኋላ የጋራ ውሳኔዎችን መሻር የሚያስገድድ ሁኔታ ሲከሰት በመተዳደሪያ ደንባችን መሠረት በጋራ ብቻ እንዲሆን፥ ሆን ተብሎ ኅብረቱን ፓርላማ ለመግባት እንደተስማማ አድርጎ የተዛባ መልእክት የሚሰጠውን በኅብረቱና በቅንጅቱ በጋራ ስምምነት የተደረገበት ነው ተብሎ በዶ/ር በየነ የተነበበው መግለጫ ውዥንብር ስለፈጠረ ኅብረቱ የዚያ ዓይነት አስተሳሰብም ፍላጎትም ሆነ ውሳኔ እንደሌለውና እንደማንቀበለውም በመግለጫ ማብራሪያ እንዲሰጥ፥ በኅብረቱ

---

** 4 በዚህ ጉዳይ ላይ ኅብረቱ መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ያወጣውን መግለጫ ይመለከቷል፡፡*

ውሳኔ እንደሌለውና እንደማንቀበለውም በመግለጫ ማብራሪያ እንዲሰጥ፥ በኅብረቱ ተደራዳሪ ቡድን ላይ ቢያንስ ምክትል ሊቀ-መንበሩ አቶ ግርማ ሹምየና ዋና ፀሐፊው አቶ ደረጀ ከበደ እንዲጨመሩ፥ ወደፊት የሕግ ባለሙያዎችም በአማካሪነት እንዲታከሉ፥ ድርድሩም ሦስተኛ አካል ባለበት እንዲሆን፥ ከገዥው ፓርቲና መንግሥት በኩል አዎንታዊ ምላሽ እስከ ረቡዕ መስከረም ፳፬ ቀን ካልተሰጠ የትግል ትብብር ጥሪ ለሕዝብ እንዲቀርብ፥ ወዘተ.... የሚሉት ይገኙበታል።

## አራተኛ፡- በሕዝብ የታጀበና መተክል ያልለቀቀ ድርድር ማድረግ፤

ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር የሚደረገው ድርድር ከሕዝቡ ጀርባ ሳይሆን ሕዝብ እያወቀውና በሕዝብ ትግል የታጀበ እንዲሆን፥ የሕዝቡን ፍላጎት የሚያከብርና መተክላዊ፥ ግልጽና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆንና የዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡ በአደራዳሪነት የሚኖረው ሚና በወሳኝነት ሳይሆን በአጋዥነት ደረጃ ብቻ እንዲሆን ኅብረቱ የጠነከረ አቋም ስላልው በዚህ ጉዳይ የተመደቡ አባላት በዚሁ መንፈስ መሠረት እንዲሠሩ ጥረት አድርጓል።

ኅብረቱና ቅንጅቱ በተናጠልም በጋራም ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር ድርድሮችን ማድረጋቸው ይታወቃል። እንደሚታወቀው ማንኛውም ድርድር ሚዛናዊ ውጤት የሚያስገኘውና የተሻለ ተቀባይነት የሚኖረው ተደራዳሪዎቹ መኻል አቻነት ሲኖር ወይም በሁሉም ረገድ የተዛባ ሁኔታ ከሌለው ብቻ ነው። አለበለዚያ ድርድሩ አንፃራዊ ጥንካሬ ያለው ክፍል ፍላጎት ብቻ የሚንፀባረቅበትና የሱም ጥቅም የሚከበርበትን ውጤት ማስከተሉ የግድ ነው። በተጨማሪም ምንም ዓይነት ድርድር ተግባር ላይ መዋል የሚችለው ተደራዳሪዎቹ የተስማሙበትን ጉዳይ ሲያምኑበትና ሁሉም ወገን ኃላፊነቱን ለመወጣት በተግባር ሲገልጽ ብቻ ነው። በኢሕአዴግ በኩል የሚታየው ግን በመጀመሪያ ዴሞክራሲያዊ ሂደቱ እንዳይቀጥል ማጨናገፍ፥ ሁኔታውን አደፍራሽና ሰላም እንዳይሰፍን ሰበብ መሆን፥ ለውጭው ፍጆታ ብቻ ተስማማሁ ካለ በኋላ ስምምነቱ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ወከባውንና የግፍ እርምጃውን መቀጠል አዘቦታዊና የተለመደ አካሄድ እንደነበር በገሃግ ታይቷል። ኅብረቱ በምርጫው ለመሳተፍ ሲወስን የአገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንደሆነ እየታወቀ፥ ለዚህም ምርጫውን በሰላም ለማካሄድ የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ያካተተተ የምርጫ ሂደት ሥነ- ሥርዓት ደንብ ምርጫው ውስጥ በሚሳተፉ የፖለቲካ ድርጅቶች የተፈረመ መሆኑ እየታወቀ፥ የመንግሥት ኃይሎች ከፍተኛ ማዋከብ አፈናና ግድያ በተቃዋሚ ኃይሎች ላይ እያደረሱ ባሉበት ሁኔታ፥ የምርጫው ቀን እየቀረበ በሄደ ቁጥር በአገር-አቀፍ ደረጃ ያለውን የሕዝብ የለውጥ ፍላጎትና ቁርጠኝነት በመረዳት፥ ኢሕአዴግ ሁሉም ተፎካካሪ ክፍሎች የሰላም ውል እንዲፈርሙ ለማስገደድ ያደረገውን ግፊት፥ የራሱ የሆኑ ካድሬዎችና የፀጥታ ኃይሎች የሚያካሂዱትን የኃይል እርምጃ ለመሸፋፈንና ከተጠያቂነት ለማምለጥ፥ ከወዲሁ ሕዝቡ የተጭበረበረ ምርጫን ያለመቀበል መብቱንም ሆነ ብሶቱን ለመግልጽ እንዳይችል ሁለንተናዊ አፈና ለማድረግ ሆን ተብሎ የተቀመረ የተለመደ ኢሕአዴጋዊ መሰሪያዊ አካሄድ መሆኑን በማመን ቅንጅቱ ቢፈርምም ኅብረቱ ይኸንን ቧልት አልተቀበለም፥ አልፈረመም።

እንዲሁም የተጭበረበረው የሕዝብ ድምፅ በተለይም ሁሉም ክፍሎች የተስማሙባቸውን የ299 ድምፆች ውዝግብ ለማጣራት ገለልተኛና ተአማኒነት ያለው የጋራ አጣሪ አካል እንዲሰየም የተደረገው ሙከራ ውጤት ሊሰጥ ያልቻለው በኢሕአዴግና በአሳፋሪ መልክ የእሱ ትዕዛዝ ፈጻሚና ወገንተኛ የሆነው ምርጫ ቦርድ የተመሳጠረ መሰሪአዊ ተግባር ነው። በዚህ የተጭበረበረ የሕዝብ ድምፅ የማጣራት ሙከራ በኅብረቱ በኩል አቸንፌ ተጭበርብሬአለሁ ብሎ ባመንባቸው ከ ፩፻፺ በላይ የምርጫ ጣቢያዎችና ፸፱ ወረዳዎች ላይ በአግባቡ የማጣራት ምርመራ እንዲካሄድ ጥያቄ ቀርቦ ነበር። ይኸ አሐዝ በትግራይ ውስጥ ኅብረቱ አሰልፏቸው የነበሩና ማቸነፍ ሲችሉ በገዥው ፓርቲ ከፍተኛ ጫና ምክንያት ከምርጫው ውድድር እንዲወጡ የተደረጉትን አይጨምርም። ሆኖም በኋላ እንደታየው

የማጣራቱ ሂደት እንዳልሆነ ሆኗል፡፡ በኅብረቱ እምነት ትግራይ ውስጥ ምርጫ አልተካሄደም፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ይሁን በትግራይ ክልል ምክር ቤት ውስጥ የትግራይ ሕዝብ በፍላጎቱ በመረጣቸው ወገኖች የተወከለበት ሁኔታ የለም፡፡

ምርጫው ከተከናወነበት ግንቦት ሰባት ማታ ጀምሮ ምርጫ ቦርድ ተብየው የኢሕአዴግ አገልጋይ ዋና ተግባር ያን ዕለት ማታ ገዥው ፓርቲ አቸንፌአለሁ ብሎ የለፈፈውን ቁጥር ተሰባብሮ ለማሟላት የሚችልበትን ስሊት መቀመር ሆነ፡፡ ቆየት ብለን የመጨረሻ “ውጤት” የተባለውን አሓዝ ስንመለከት የሚያረጋግጥልን ይኸንኑ ሃቅ ነው፡፡

ቅድመ-ምርጫ በተለይ በጋራ በተደረጉ ድርድሮች ላይ በአዲስ አበባ የሚገኙ የውጭ አገር ኤምባሲ ተወካዮች እንደ ታዛቢም፥ እንደ አደራዳሪም በመሆን ሲያጋፍሩ እንደነበር ይታወቃል፡፡ እነኝህ ክፍሎች ገለልተኛነትን አጥብቆ ከሚጠይቀው የሦስተኛ አካል የድርድር ታዛቢም ይሁን አደራዳሪ ሚና በተለየ በአብዛኛው ዓይን ባወጣ መልክ ገዥውን ፓርቲ በመደገፍ ተቃዋሚው ላይ ከፍተኛ እስከ ማስፈራራት የደረሰ ጫና ሲያደርጉ ተስተውለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኅብረቱ በዚህ ተግባር ላይ ያሰማራቸው ግለሰብ ከኅብረቱ ውሳኔ ውጭ የሕዝብ ትግል ላይ አሉታዊ ጫና የሚያሳድሩና ድክመትን የሚያንፀባርቁ ስምምነቶችን በድርድር ስም በመፈጸም ትግሉን ክፉኛ ጎድተዋል፡፡ ድኅረ-ምርጫ ተቃዋሚው ክፍል ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር ያደረጋቸውን የድርድር ሙከራዎች በተመለከተ ሳንጠቅሰው ያማናልፍ ጉዳይ አለ፡፡ በዚህ ረገድ በምሳሌነት የምንጠቅሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ተማሪው የተሰረቀው የሕዝብ ድምፅ ይከበር በሚል የራሱ የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት በሚፈቅደው መሠረት በሰላማዊ መንገድ ለመጠየቅ ባደረጉት ሰላማዊ እንቅስቃሴ ገዥው ክፍል በግፍ በተጨፈጨፈበትና በሕዝብና በገዥው መኻል ያለው ውጥረት በገፋበት ወቅት በኢሕአዴግ፥ በቅንጅትና በኅብረት መኻል ሰኔ ሦስት ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የተፈጸመው የሦስትዮሽ ተብየው ድርድር በትግሉ ላይ ያስከተለውን አሉታዊ ውጤት ነው፡፡

ይኸ ድርድር ተብየ ትርኢት በአንድ በኩል በሦስተኛ ኃይልነት አደራዳሪ ሆኖ የተሰለፈውን የዓለም-አቀፍ ማኅበረሰብ ተወካዮች ሚና ያለቦታውና ያለአግባብ ለገዥው ክፍል ወገንተኛ እንዲሆኑ የፈቀደና በሌላ በኩል ተቃዋሚው ክፍል የሕዝቡን ፍላጎት የሚመጥንና ጥያቄውን የሚያስከብር ቆራጥ አመራር መስጠትና እርባና ያለው እንቅስቃሴ ማድረግ የማይችል፥ የተሰጠውን የሚቀበል ደካማ እንደሆነ በገሃድ አጋልጧል፡፡ የሰኔ ሦስት “ድርድር” ተቃዋሚው ክፍል ጫናን ተቋቁሞ፥ አጥጋቢ ውጤት ያለው የበሰለ አመራር የመስጠት ፈተናን ያላለፈበት ለኢሕአዴግ እጅ ያስሰጠና የሕዝብን ትግል የከዳ ተግባር በመሆኑ ዳግም የአልጀርስ ስምምነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አድራጎቱን ኅብረቱ አልተቀበለውም፥ ይኸንን ድርድር ተብዬም መሠረት በማድረግ ወደ ፍርድ ቤት የመሄድም ሆነ ሌላ እርምጃ እንዳይወሰድ ወስኗል፥ መመሪያ ሰጥቷል፡፡

ሕዝቡ ድምፄ ይከበር፥ የአሥራ አራት ዓመታት ኋላ-ቀር ከፋፋይ አገዛዝ በቃኝ፥ በፍላጎቴ አምኘ የመርጥኳቸው ያስተዳድሩኝ በማለት ወደሰበረው በመሣሪያ ኃይል የገዥዎች በሥልጣን የመቆየት አዙሪት ላለመመለስ በቁርጠኝነት ግብ ግብ ላይ እያለና አይከፍሉ መስዋዕትነት እየከፈለ እያለ የዚያ ዓይነት “ድርድር” ማድረጉ አላስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ስህተት ነበር፡፡ ይኸ “ድርድር” ተቃዋሚው ወገን ወድዶ እጁን ተጠምዝዞ እንዲታሰር አመቻችቷል፥ ገዥውን ፓርቲ ከገባበት አጣብቂኝ ለመውጣት እንዲችል አውላላ በር ከፍቶለታል፡፡

ይኸን አገዛዝ እንደምንም በሥልጣን ላይ እንዲቆይ ለማድረግ ወስነው በልዩ ልዩ መልክ ትግሉን እየተፈታተኑ ያሉ የውጭ ኃይሎችን በተገቢ መረዳቱ ጠቀሜታ አለው፡፡ የሥልጣን ባለቤትና ምንጭ መሆኑን ለማረጋገጥ በግንቦት ያስመዘገበውን ድልና መብቱን ለማስከበር የሚያደርገውን ትግል ለመበረዝና ለማኮላሸት አሁንም በአደራዳሪ ስም አንዳንድ የውጭ

ኃይሎች በሕዝባችን ላይ ደባ እየተፈጸመበት መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል። አሁንም ለነዚህ ክፍሎች ችግሩንና ውጥረቱን በሰላም ይፈታ ሲሉ ኢሕአዴግን ሳትነኩ "የሚሰጣችሁን" ተቀብላችሁ አገልግሉ ከሚል የዘለለ አይደለም። ለዚህም ሕዝብን የናቀ እኩይ ተግባር አንዳንድ ከኀብረቱ የተባረሩና በቅንጅቱም በኩል ያሉ ደካሞችና አድር-ባዮችን በተቃዋሚ ስም አሰልፈው አገር ሰላም ነው ሊሉን ይሞክራሉ። ይኸንን ትእዛዝ ለመፈጸም የሚሽሎከለኩ፥ የሚጠብቁና የተዘጋጁም እንዳሉ ግልጽ ነው። ተጧጧፈው የኀዳ ድርድርም ለዚሁ ዓላማ እንደሚሆን መገመት አዳጋች አይደለም። በኀብረቱ በኩል ገና ከጠዋቱ የሰባ ሰባት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በተወሰኑ ተመራጮች ሊተካ አይገባም ያለውም ለዚህ ነበር።

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደጠቀስነው ሕዝባችን ለለውጥ በቁርጠኝነት መቆሙን በግንቦቱ ምርጫ በማያወላዳ ሁኔታ አሳይቷል፥ አቸንፏል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ይልቅ ተቃዋሚውን የመረጠበት ምክንያት ግልጽ ነው። ኢሕአዴግ ወደዚህ ውድድር የገባው የአሥራ-አራት ዓመታት የመከፋፈል፥ የብሔራዊ ጥቅም አለመቆም፥ የናጠጠ ሁለንተናዊ የመብት ረገጣ፥ የአፈና፥ የበሽታ፥ የአለመተማመን፥ የሙስንና የንቅዘት፥ የረሃብና ችግር፥ ወዘተ.... ኢ-ዴሞክራሲያዊ ብልሹ የአገዛዝ መረጃ (ሬኮርድ) ይዞ ነው። በተቃዋሚው በኩል ብሩህ ተስፋን፥ አንድነትን፥ ፍቅርን፥ መቻቻልን፥ ብቃትን፥ ተአማኒነትን፥ ወዘተ.. ይዞ ነው ወደ ምርጫ ውድድሩ የገባው። መቸም ማንም ይሁን ማ፥ የትም ይሁን የት ከብርሃን ጨለማን፥ ከመልካም ተስፋ ተስፋ መቁረጥን፥ ከእድገት ውድቀትን የሚመርጥ የለምና ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢሕአዴግን ያልመረጠው። በዚህ ምርጫ ኢሕዴግ የደረሰበት ተራ ሽንፈት ብቻ ሳይሆን በሕዝብ ጨርሶ መተፋትን ነው። ምን ጊዜም ቢሆን ከአንድ ሕዝብ ከዚህ የበለጠ አይጠየቅም፥ አይጠበቅምም። አኩሪና ሊሰሰውለት የሚገባ ክቡር ሕዝብ ነው። የእሱን ድርሻ በሚገባ ተወጥቷል። የሕዝቡ ጥያቄ እዚህ ደረጃ ደርሰናል፥ የሰበርነው የአመፅና የአምባ-ገነን የግፍ አዙሪት ተመልሶ ሕይወት እንዳይዘራ አመራር ስጡን፥ ለማይቀለበስ ውጤት አብቁን ነው። ቁም ነገሩና ከባዱ ተቃዋሚው ክፍል ይኸንን የሕዝብ ፍላጎት ከኢሕአዴግ የድንቁርናና የትእቢት ጡንቻ በጥበብ አላቆ፥ ትርምስና አጉል ደም መፍሰስን በማስወገድ የሕዝቡን የግንቦት ድሎች ማስከበር የመቻልና ያለመቻል ጥያቄ ነው። በሚያሳዝን መልኩ ተቃዋሚው ይኸን ፈተና እየተወጣው አይደለም። የግንቦት ምርጫ ዱብዳነት ለኢሕአዴግ ብቻ ሳይሆን ለተቃዋሚውም እንደሆነ ግልጽ ነው። ዝግጁነት ሳይኖር በተለይ በተናጠል ለመጓዝ መሞከር ጤናማ አስተሳሰብ አይደለም። በኅብረቱ በኩል ወደ ምርጫም ሲገባ አቸንፎ ሥልጣን ለመያዝ አልነበረም። እንዲሁ በሁኔታዎች ያልታሰበ አጋጣሚ የመንግሥት ሥልጣን ማስጨበጥ የሚያስችል በቂ ድምፅ ቢያገኝም እንኳ ብቻውን መንግሥት አያቋቁምም ነበር። እምነቱ አይደለምና። በኀብረቱ እምነት ኢሕአዴግ ሥልጣን በ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ሲይዝ የተደናቀፈውና የጨነገፈው ወደ ሰከነ ሽግግር የሚያደርሰው ዴሞክራሲያዊ ሂደት በአዲስ መልክ እንዲቀጥል ማድረጉ ብቻ ነው አስፈላጊው የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ተግባራዊ ሊሆንና ለአገራችን ፈርጀ-ብዙ ውስብስብ ችግሮች ዘለቄታዊና አስተማማኝ መፍትሔ ማስገኘት የሚቻለው። ለዚህም ነው ቅድመም ሆነ ድኅረ-ምርጫ በእኛ እምነት ኀብረቱም ሆነ ቅንጅቱ በተናጠል መንግሥት ማቋቋም አይችሉም፤ ተፈላጊ አካሄድም አይሆንም የሚል አቋም የያዝነው። ገዥው ፓርቲ ሽንፈትን ተቀብሎ የመንግሥት ሃላፊነትን ለማስረከብ ፈቃደኝነት ቢኖረውና ትብብር ቢያደርግ ኖሮ ኀብረቱና ቅንጅቱ በጋራ መንግሥታዊ ኃላፊነትን ለመረከብ ቢችሉ ምናልባት ወደ ሽግግር የሚደረገውን ሂደት የተሻለ ሊረዳ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይኸን አስተሳሰብና አመለካከት ግን ቅንጅቱ የመጋራቱ ጉዳይ በጣም አጠራጣሪ ነው። የዘለቄታው ሳይታየን በድርጅት አጥር ውስጥ ታቅበን የድርጅት ጥቅም በማስቀደም ለጋራ ዘለቄታዊ ጥቅም በጋራ መቆም በአለመቻል የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ከእጁ እንዲነጠቅና እንደገና ተስፋው እንዲጨልም መደረጉ ምን ጊዜም ይቅርታ የሌለው በደል ይሆናል።

*ድኅረ-ምርጫ የተከሰተው ሁኔታ የሚያስተምረን ሕዝቡ የግንቦት ድሎቹን እንዳይ-ነጠቅና ትግሉ እንዳይቀለበስ ተቃዋሚው ወገን ለገዥው ፓርቲ ፋታ ሳይሰጥ፥ የጋራ መግለጫ ከመስጠት አልፎ መዋቅራዊና ድርጅታዊ ይዘቱን ባፋጣኝ አስተማማኝ ይዞታ ላይ ማምጣት ያስፈልገው እንደነበር ነው። በተለይ በፀጥታና በድርጅት ዙሪያ በሁሉም እርከን በጋራ ለመሥራት የሚያስችል መዋቅራዊ ግንኙነትና ትሥሥር መመሥረት፤ በውጭም በውስጥም ያለው ኃይል የተሻለ፥ ቀጣይና አስተማማኝ ትግል እንዲያደርግ የጋራ አካሎችን በማዋቀር ሕዝቡን በስፋት ማንቀሳቀስ ይገባ ነበር። ያ ባለመደረጉ በድርጅቶች መኻል ያላስፈላጊ ክፍተት እየተፈጠረ ይኸም ኅብረተሰባችንን እየከፈለ ለትግሉ እንቅፋት መሆኑና ይኸም በተራው የሕዝባችንን ሰቆቃ እንዲራዘም ማድረጉ በተገቢ ሊታወቅ በተገባ ነበር። የኅብረቱ የቀድሞ ሊቀ-መንበርና ተቀዳሚ ም/ሊ/መንበር ውሳኔ ጥሶ ፓርላማ መግባትና በኋላም የቅንጅት መሪዎች እስር ቤት መግባታቸው በአጠቃላይ በትግሉ ላይ ካሳደረው ከፍተኛ ጫና በተጨማሪ ኅብረቱም ሆነ በቅንጅቱ በኩል ለጋራ አገራዊ ችግር የጋራ መፍትኄ ለመፈለግ እንዲቻል ተቀራርቦ መሥራት ላይ ግልጽ እክል ፈጥሯል። በዚህ ረገድ በተለይ የቅንጅቱ የሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጭ አካል ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ለመሥራት ጊዜውም ውክልናውም የለንም በማለት የጋራ ሥራ መሥራት አልተቻለም። *5*

*የፖለቲካ ድርጅቶቹ ለሕዝቡ የሚቀርቡ ዜናዎች በመረጃ የተደገፉና ተአማኒነት ያላቸው እንዲሆኑ በየድርጅቱ በተለያየና በተዘበራረቀ መልክ ሳይሆን ጥራት ባለውና በተቀናበረ ሁኔታ እንዲሆን በአንድ የጋራ የዜና ስብስብና ስርጭት ማእከልነት ያም ባይሆን ተደጋጋፊና ተረዳጅ ሆኖ የሚሠራበት መንገድ መፈጠር ነበረበት።*

*በገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ሥር ላሉ የጦር፥ የፖሊስና የፀጥታ ክፍሎች የአገሪቱን ሁኔታና የሕዝብን ስቃይ ቁልጭ አድርጎ በሚያሳይና በጠራ መረጃ ላይ የተደገፈ አሳማኝ መልእክት ማስተላለፍና የኢሕአዴግ መሪዎች አገሪቱን ወደጥፋት አቅጣጫ እየወሰዷት እንደሆነ በማስረዳት የአረመኔ ተግባር ተባባሪና መሣሪያ እንዳይሆኑ አገራዊና ወገናዊ ጥሪ ማቅረብ አስፈላጊ ነበር፤ ነውም። ቀውደም ሲል ኅብረቱ አሳስቦ እንደነበረውም ከመጀመሪያው ይኸንን የኅብረተሰብ ክፍል መድረስ የሚያስፈልገው በራዲቅ ብቻ ሳይሆን ተጠሪዎች ተሰይመው የጎንዮሽ ግንኙነት ሊደረግና በአገሪቱ የፀጥታና ተዛማች ጉዳዮች ላይ በጋራ መምከር የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልግ ነበር፤ መደረግም አለበት።*

*በመሠረቱ አገራችንን ወደ ትርምስ እየወሰደ የሚገኘው የአቶ መለስ ዜናዊ ኢሕአዴግ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ የግንቦት ፺፯ን ድሎች ቀምቶ የሕዝቡን ሰላማዊ ትግል ለማክሰም ያለ የሌለ ኃይሉን አሰልፎ የሚፈጽመው ግፍ የሚያረጋግጠው ድክመቱን ቢሆንም ከዚህ ሂደት ለመውጣት እርብርብ እስካልተደረገና በሳል አመራር እስካተሰጠ ድረስ ማገገም ወደማንችልበት ሁኔታ ሊወስደን ይችላል። በአንዳንድ ወገኖች ይኸ ቡድን በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያደርገው አረመኔአዊ እርምጃ ቢበዛ አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት የሽብር አጋፋሪዎች ዕድሜአቸው እስከፈቀደላቸው ድረስ ብቻ የሚቀጥል ተደርጎ በነጠላው ሲቀርብ ይሰማል። አንዳንድ የዓለም-አቀፍ ማኅበረሰብ የዋሃን አባላትና የተወሰኑ የሥልጣን ደላሎች በተደጋጋሚ ለተቃዋሚው የሚገልጹት፥ ኢሕአዴግ የአሁኑን የአምስት ዓመት ዙር ይጨርስ ታገሱና በቀጣዩ ምርጫ ተራ እንዲደርሳችሁ "ታገሉ" እያሉ እንደሚወተውቱ ይታወቃል። ይኸን ሃሳብ የሚያቀነቅኑ ክፍሎች ያልተረዱት ቁም ነገር ግን በዚህ የሽብር ሂደት ውስጥ ለዴሞክራሲ ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት በቀላሉ ሊያገመግሙ በማይችሉበት ደረጃ ድምጥማጣቸው እየጠፋ የመምጣቱ ጉዳይ ነው። እያንዳንዱ የሽብር አገዛዝ ቀን*

---

**5 - ኅብረቱ ድኅረ-ምርጫ የተከሰተውን የአገራች ሁኔታ በተመለከተ በተለይ የታሰሩ ዜጎቻችንን ለማስፈታትና ኢሕአዴግ በሕዝባችን ላይ ያወጀውን የሽብር ጦርነት ለመቋቋም ባሉ አጣዳፊ ጉዳዮች ዙሪያ ኅብረተሰባችንን አስተባብረን እንድንሠራ ላቀረባቸው ተደጋጋሚ ጥያቄዎችና አሳቦች የቅንጅቱ የሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጭ አካል አለመቀበል ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር "ጊዜ የለንም" የሚል ሃላፊነት የጎደለው መልስ በጽሑፍ ተሰጥቶታል።*

የሚያደርሰው ጥፋት በአገራችን ረክሶ የሚገኘው ምትክ የሌለው የሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ብቻ ሳይሆን ይኽ ሁኔታ እንዳይቀጥልና ኅብረተሰባችን እንዲያገግም የሚያስፈልገው በጎ ሥነ-ልቦናዊ ሰብዓዊ ትስስር ላይ ጭምር በጊዜ ለመተመን በሚያስቸግር መልክ ቶሎ መጠገን የማይቻል ውድመትን ያስከትላልና ነው ይኽ ሂደት በአጭሩ ይቀጭ የምንለው። ማፍረስና መገንባት እኩል ጊዜ አይወስዱም፥ በተለይም የተሰበረ የሰው መንፈስ፥ በትርምስና በእርስ በርስ ቀውስ ውስጥ እንዲያልፍ የተገደደ ኅብረተሰብ በቀላሉ ማገገም ያስቸግረዋልና ነው ኅብረቱ ሕዝባችን በትግሉ ያስገኘው የአመፅ አዙሪት መሰበር መልሶ እንዳይገጥም፥ የጥፋት መሳከተኞችንና የሽብር ሥርዓትን ዕድሜ በጋራ ትግላችን እናሳጥር የሚለው።

እነሱ የማይቆጣጠሯቸውና እውነተኛ ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ ድርጅቶች እርም የሆኑባቸው የኢሕአዴግ አባወራዎች አቅማቸው እስከፈቀደ ድረስ እያንዳንዱን በየተራ ለማጥፋት ወደኋላ አይሉም። በኅብረቱ በኩል ሲመሠረት እንደዚህ ዓይነትን አይቀሬ ሕወሓት/ኢሕአዴጋዊ እርምጃ ለመከላከልና ትግሉን በቀጣይነት ለመምራት እንዲቻል ስለነበር የተዋቀረው በቅንጅቱ አመራር ላይ የደረሰው ጉዳት አልደረሰበትም።

በአሁኑ ጊዜ የተቃዋሚው ክፍል የተነሳሳውን የሕዝብ መንፈስ፥ ስሜትና ፍላጎት በሚመጥን ደረጃ አሟሟቱንና መስዋዕትነቱን የሚያካክስ በሳልና ወቅታዊ አመራር ሰጥቶ ወደ ተረጋገጠና አይቀሬ ድል ማብቃት እየተሳነው እንደሆነ በግልጽ የሚታይ ጉዳይ ነው። ቅንጅቱ ለጊዜው በእስር ቤት ከሚገኙት ከፍተኛ የአመራር አባላቱ ውጭ ካሉት መኻል መወሰንና አመራር መስጠት የሚችል አካል በአስቸኳይ ቢያቋቁም ሁኔታው የሚጠይቀውን ከሌሎች ኃይሎች ጭምር በጋራ ሰፊ መሠረት ያለው እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት በጣም ይረዳል የሚል የጠና እምነት አለን።

ተወደደም ተጠላ አሁን ባለው የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ቅንጅቱም ሆነ ኅብረቱ ወይም ሁለቱ በጋራ አሁን በሚገኙበት ደረጃ የሕዝቡን ትግል ለውጤት በሚያበቃ ሁኔታ እየመሩት አይደለም። ምክንያቱ ሊለያይ ቢችልም ሁለታችንም ብቃት ያለውና ሁኔታው የሚጠይቀውን አስተማማኝ አመራር እየሰጠን አለመሆኑ ግልጽ ነው።
ይኸን መራር ሃቅ መቀበል ያስፈልጋል። አመራር ያጣ ትግል፥ ተቀባይ ያጣ ድል ይሷል ይኸ ነው!

በመሆኑም ኅብረቱም ሆነ ቅንጅቱ ይኸንን መራር ሃቅ በቀና መንፈስ ተቀብለው ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችና ከሲቪክና የሙያ ማኅበራት ጋር በመሆን ሕዝቡን ሊታደጉት ይገባል። አሁንም ቢሆን ድርጅቶች ካለፉት ስህተቶች በጊዜው ለመማር የቻሉ አይመስልም። አቀራረቡ ይለያይ እንጅ አሁንም ከጋራውና ከአገራዊው ዓላማ ይበልጥ የተናጠል ድርጅት ዝናና ክብር ላይ ትኩረት ሲደረግ ይታያል። ይኸንን የተናጠል ጉዞ አባዜ፥ ለሁሉም ጥያቄ መልስ ያለው እኔጋ ብቻ ነው፥ እኔን ተከተሉ፥ ወዘተ... አጉራ ዘለል ጥንውት እስካልተወገደ ድረስ የጋራ ሥራንና ትብብርን አጥብቆ የሚጠይቀው የሕዝብ ትግል ሊሰምር አይችልም። የኢትዮጵያ ችግር ከእያንዳንዱ ድርጅት ብቻ ሳይሆን ከነሱም ድምር እጅጉን ይበልጣል።

አሁን በአንዳንድ ቦታ በተለይ በሰሜን አሜሪካ በአንዳንድ የቅንጅቱ ተወካዮች የሚደረገው "ለቅንጅቱ አመራር አባላት በኢሕአዴግ መታሰር ኅብረቱ ተጠያቂ ነው" የሚል መሠረተ-ቢስ ክስና አፍራሽ ሥራ ታሪክን ባልሆነና በተሳሳተ መልክ እንደገና ለመጻፍ የሚደረግ ሙከራ የሚጠቅመው ኢሕአዴግን ብቻ እንደሆነ በተገቢ መታወቅ አለበት። ይኸ አባባል እየተደጋገመ በመሰማት ላይ ያለና ጠቀሜታውም በድርጅቶቹ መኻል አመኔታ ያለው የትግል ትስስር እንዳይኖር የሚታገለንን ኢሕአዴግን ብቻ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ስለሆነም ነው በኅብረቱ በኩል እስካሁን ድረስ ለሚነዙ አሉባልታዎች ጆሮ ያልሰጠውና ንቆ

የተዋቸው። ይሁንናም ዝምታው ሲበዛ ሌላ የተሳሳተ ትርጉም ስለሚሰጥ ኅብረቱ እንደዚህ ዓይነቱን መረን የለቀቀ ዘመቻ በዝምታ ሊያየውም ሆነ ሊያልፈው አይገባም። * 6

በአገራችን በኢትዮጵያ የታየውን ይኸን የመሰለ አኩሪ የሕዝብ ንቁ ተሳትፎ እያለ ትግሉን ለውጤት አለማብቃት ምን ጊዜም ይቅር ታ የማይደረግለት ድክመት ነው። እቅድ ይወጣና ሕዝቡ የእኔ ነው ብሎ እንዲታገልበት ጥሪ ይቀርባል፥ ለተፈጻሚነቱ እስከ መጨረሻ አይገፋም፥ ተለዋጭ መሥመሮችና ስልቶች በተከታታይና በወቅት በቅወቅቱ አይቀርቡም፥ እንዲሁ በዝርግ ይተዋሉ። የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ጥሪ ለሕዝብ ተወርውሮ ዝም የሚባልበት ሳይሆን፥ ወይም የፍተሻ ተኩስ በሚመስል ሁኔታ አለ የተባለው ስልት (ዘዴ) ሁሉ እንዴ ዝርግፍ ተደርጎ "የፈለከውንና የምትችለውን መርጠህ አድርግ" በሚመስል መልክ መቀጠል የለበትም። ይኸም በመሆኑ ቅድሚያ መውሰድ ከተቃዋሚው እጅ እየወጣ ትግሉ ኅሉፋዊ ወይም የተሚዘዘና ሕይዎት አልባ እንዲሆን ይደረጋል። በአገራችን መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የተሰለፉ ኃይሎች ሁሉ እራሳቸውን ከዚህ የቆየ አባዜ ሊያላቅቁና ስትራቴጂካዊ አስተሳሰብ ሊኖራቸው ይገባል።

ኅብረቱ ለአገራችንና ለሕዝቧ ያለውን በጠራ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ራእይውን እውን ለማድረግ የጋራ ትግሉ እንዲጎለብት የማስተባበር ጥረቱን እስከተቻለ ድረስ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ሆኖ፥ ካልተቻለም እንደስከአሁኑ እያንዳንዱን ቀሞ ሳይጠብቅ ፈቃደኛ ከሆኑት ጋር በመሆን በቁርጠኝነት ሊገፋበት ይገባል።

## ክፍል አራት፤

## በኅብረቱ ውስጥ የተከሰቱ ዋና ዋና ችግሮች፤

### አንደኛ)- ከኅብረቱ አባል ድርጅቶች ጋር የተከሰተ ችግር፤

ከምሥረታው ማግስት ጀምሮ በተለይ መኢአድና ኢዴአፓ ልዩነት አለን በማለት ከኅብረቱ በመለየታቸው የጋራ ትግሉን በአንድነት ለመግፋት እንዲቻል በማሰብ የተባለውን ልዩነት ለማስወገድና ችግሩን ለመፍታት ጊዜና ጉልበት ባክኗል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁሉ ችግሩን ለመፍታት በኅብረቱ አማካሪ ሸንጎ አማካይነት፥ በማእከላዊ ሥራ አመራርና በሥራ አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም በልዩ ልዩ ተቆርቋሪ ወገኖች አማካይነት በርካታ ጥረት ተደርጓል።

ከነኝህ ሁለት መሥራች ድርጅቶች ውጭ በኢ/ር ቅጣው የሚመራው ኢብአግ መሪው ከኅብረቱ ጋር የአሠራር ችግር አለኝ በሚል ድርጅቱ በኅብረቱ ውስጥ ያለውን ሃላፊነት የሚጠበቀውን ያህል ሊወጣ አለመቻል ብቻ ሳይሆን የተወሰኑ የድርጅቱ አባላት በድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ ስም የድርጅቱን (የኢብአግን) መሪ (ሊቀ-መንበር) ከሃላፊነት አውርደናልና እኛን (ኢብአግን) በኅብረቱ ውስጥ አይወክሉም የሚል ውዝግብ በመነሳቱ ድርጅቱ በኅብረቱ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው ተሳትፎ ላይ ችግር አስከትሏል፥ በኅብረቱ አሠራር ላይም አንዳንድ ተጨማሪ እክሎችን ፈጥሯል።

---

* 6 ይኸንን መሠረተ-ቢስ ክስ በራዲዮ ያሰሙትና በቤይ ሰላጤ፥ በአትላንታ፥ በሲያትል፥ ወዘተ... በተደረጉ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የተናገሩት በሰሜን አሜሪካ የቅንጅቱ ድጋፍ ሰጭ አካል ዋና ፀሐፊ አቶ ብርሃነ መዋ ናቸው። ይኸንንም በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጠው ኅብረቱ ሚያዝያ 28 ቀን 1998 በተጻፈ ደብዳቤ ጠይቋል።

***<u>ሁለተኛ)- ቆራጥና ተአማኒነት ያለው አመራር የመስጠት ችግር፤</u>***

የኅብረቱ አወቃቀር የውስጥ/የውጭ፥ የብሔረ-ሰብ/ኅብረ-ብሔራዊ የሚል ልዩነትን በማስወገድ ተቃዋሚው ክፍል ጠንካራና አስተማማኝ ትግል ለማድረግ እንዲያስችል ብቻ ሆኖ ሳይሆን የዴሞክራሲ ፖለቲካ መሠረት የሆነውን መቻቻል በማዳበር አስፈላጊ ሁኔታ ከተከሰተ በመንግሥት ደረጃ ሊንቀሳቀስ በሚያስችለው መልክ እንዲሆን በታሰበበት መልክ ነበር። መሠረታዊ ለሆኑ የአገሪቱ ችግሮች በየድርጅቱ የፖለቲካ ፕሮግራም የሚሰፍር ደረቅና የተለመደ አስተሳሰብን ከማንፀባረቅ አልፎ በጥናት ላይ የተመሠረተ መፍትሔ ለማስገኘት ይቻል ዘንድ ነገ ማንም ይሁን ማን በሥልጣን ላይ ቢወጣ ጠቀሜታ እንዲሰጥ በየዘርፉ ብቃትና ችሎታ ያላቸው አገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሙያዊ አስተዋጽዖ የሚያደርጉባቸው የሕግና ሕገ-መንግሥት፥ የኤኮኖሚና ልማት፥ የትምሕርት፥ የሕዝብ ጤና፥ የአገር መከላከያ ጉዳይ ኮሚቴዎችን በሥሩ ያቀፈ የጥናትና ምርምር አካል አቋቁሞ ለመሥራት ሞክሯል።

ኅብረቱ ለኢትዮጵያ ያለውን ራእይና ከኢሕአዴግ ጋር የሚለይባቸውን አስተሳሰቦችና ከነሱም የሚመነጩ ፖሊሲዎችን በዝርዝር የሚያሳዩ ብሔራዊ የፖለቲካ አማራጭ መርኃ-እቅድ (ፕሮግራም) እና ብሔራዊ የኤኮኖሚ አማራጭ መርኃ-እቅድ ሰነዶችን አውጥቶ ለሕዝብ አሳውቋል። ይሁንናም በተተለሙ የጋራ ትልሞችና በጋራ ውሳኔዎች መሠረት ተግባራዊ የሚያደርግ ሙሉ በሙሉ አመኔታ የተጣለበት በሳል አመራር በአገር ውስጥ የመስጠት ችግር ነበረበት። ለምሳሌ ከሲቪክና የሙያ ማኅበራት ጋር የአሠራር ግንኙነት ማድረግ አለመቻል፥ በቅድመ-ምርጫ ክርክሮችና ውይይቶች በጊዜው ከነበሩት ሊቀ-መንበርና ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ-መንበር ውጭ የኅብረቱን ራእይ የሚያስረዱና በተከራካሪነት የሚቀርቡ ባለ ሙያዎች እንዲቀርቡ አለማድረግ፥ ለሕዝብ የሚሰጡ ቅስቀሳዎች በኅብረቱ የጋራ ፕሮግራም መሠረት ከመሆን ይልቅ በአብዛኛው እንዲያውም አንዳንድ ቦታ ሙሉ በሙሉ የየግል አባል ድርጅቶችን መሥመር የመግፋት፥ ከገዥው ፓርቲ ጋር የሚደረጉ ድርድሮች በተወሰነው መሠረት የኅብረቱን ሕዝባዊ ቅላማዎች የጠበቁ፥ ሌሎች የአመራር አባላትንና የሕግ ባለሙያዎችን እንዲጨምር አለማድረግ፥ በኅብረቱ ውሳኔዎች መሠረት እንደ የተመራጮች ጉባዔ፥ ሰላማዊ ሰልፍ፥ አገራዊ ጉባዔ፥ ወዘተ.. የመሳሰሉ ተግባራትን በሰበብ አስባቡ የገዥው ፓርቲ አይፈቅድም በሚልና እጅግ ለዘብተኛ በመሆን በአግባቡ ተፈጻሚ አለማድረግ፥ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት የተጠበቀውን ያህል ውጤት እንዲሰጥ በቂና ቀና ጥረት አለማድረግ፥ በመጨረሻም የጋራ ውሳኔ ጥሶ ፓርላማ በመግባት የሕዝባችን ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ መቸለስ፥ ወዘተ.... እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ምንም እንኳ በተለይ መጨረሻ ላይ የጋራ ውሳኔ በጣሰና ትግሉን በጎዳ መልክ ወደ ፓርላማ በመግባት ትግሉ ላይ ጉዳት ማድረሳቸው ቢታወቅም ሁለቱ የቀድሞ መሪዎች፥ ዶ/ር መረራ ጉዲናና ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ፥ በአጠቃላይ ለትግሉ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳደረጉ መታወቅ ይኖርበታል።

***<u>ሦስተኛ) ሁሉም የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ለኅብረቱ ጥንካሬ የሚጠበቅባቸውን ተገቢ አስተዋጽዖ አለማድረግ፤</u>***

የኅብረቱ አባል ድርጅቶች በቁጥር ብቻ ሳይሆን በስብጥር ደረጃ ሁሉንም የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ የሚወክሉና ከአምስት እስከ ሰላሳ አራት ዓመት የትግል ልምድና የካበተ ተመክሮ ያላቸው ናቸው። በእርግጥ ሁሉም ድርጅት በሁሉም ቦታዎች እኩል አባላትም አቅምም ላይኖራቸው ይችላል። ሆኖም ሁሉም የሚችሉትን፥ አቅማቸው የሚፈቅደውንና የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽዖ አድርገዋል ማለት አይቻልም። ይኸ ለአንፃራዊ ድክመታችን የተሻለ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳንችል አስተዋጽዖ እንዳደረገ መገመት አያዳግትም። ስለሆነም ወደፊት እያንዳንዱ አባል ድርጅት በኅብረቱ ውስጥ ያለውን ድርጅታዊ አስተዋጽዖ በተሻለ ደረጃ ቢያደርግ ኅብረቱ በሁሉም ዘርፍ ጠንካራ እንቅስቃሴ ማድረግ ያስችለዋል።

<u>አራተኛ) የአሠራር ድክመት፤</u>

ኅብረቱ የአስተሳሰብና የራእይ ጥራት ያለው፥ በአወቃቀሩ ውስጥም ውጭም ያሉትን ድርጅቶች ያስተሳሰረ፥ በስብጥር ደረጃም በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል መንቀሳቀስ የሚያስችለው ይዞታ ብቻ ሳይሆን አሩን ሞልቶ ከኢሕአዴግም ይሁን ከማንኛውም የድርጅቶች ስብስብ በተሻለ ኢትዮጵያን ሊወክል የሚችልና በነፃዋ ኢትዮጵያ መቻቻልና መግባባት እንዲሰፍን አርአያ የሚሆን ነው። ሆኖም ብዙ የአሠራር ድክመቶች አሉት። በተለይ በሕዝብ ግንኙነት እንቅስቃሴው እጅግ ደካማ ነው። በእርግጥ በተለይ "ዜና ኅብረት" እና "ዜና ኢዴኃኅ" በሚል ኅትመቶች በማውጣትና በማሰራጨት ጥሩ ጅማሮ ነበረው።

በኅብረተሰባችን ዘንድ መከፋፈልን ላለማስፋፋትና ምናልባትም በጎ የመቀራረብ መፍትኄ ይገኛል በሚል ባዶ ተስፋ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሁለት መሥራች አባል ድርጅቶች ጋር የነበረው ውዝግብ መንስዔና ሁኔታ በተገቢና ብዙ ጊዜ ሳይፈጅ በግልጽ አለመብራራቱ አንድም ሁለቱ ድርጅቶች በጣም በገፉ መልክ ኅብረቱን ጥፋተኛ አድርገው ለማሳየት በሚያደርጉት ዘመቻ ምክንያት ደጋፊዎች ከድጋፋቸው እንዲቆጠቡ አንዳንዶችም በተፈጠረው ልዩነት ተስፋቸው እንዲመነምንና ከተሳትፎ ገለል እንዲሉ አድርጓል፥ ድርጅቶቹም ከኅብረቱ አግባባዊ መልስ በጊዜው ባለመሰጠቱ የባሰ እየራቁ እንዲሄዱ አስተዋጽዖ አድርጓል።

የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴው ብቻ ሳይሆን ሌሎች የተግባር ኮሚቴዎችም ምናልባት ከፋይናንስ ኮሚቴው ውጭ አመርቂ እንቅስቃሴ አላደረጉም። ቢሮዎች በተገቢ አልተንቀሳቀሱም። ዋና ጽ/ቤቱን ለማደራጀት ረዥም ጊዜ ፈጅቷል፥ የጽ/ቤቱን ሥራም አስፈላጊው ብቃትና ታማኝነት ባላቸው ሰዎች እንዲካሄድ አልተደረገም።

መሠረታዊ ጥናቶች እንዲያደርግ በርካታ አገር-ወዳድ ምሁራንን እንዲያሳትፍ የተቋቋመው የጥናትና ምርምር አካል በመጠኑ በአማራጭ ፕሮግራማችን ነደፋ ላይ ካደረጉት ውጭ ሰፊ ተሳትፎ አላደረጉም። እንደታሰበው ወደ አገር ውስጥና በውጭም የሚተላለፍ የራድዮ ስርጭት ማካሄድ አልተቻለም። በአጭሩ ኅብረቱ ለትግሉ የሚጠቅሙና ተፈላጊ የሆኑ ብዙ እቅዶችና ትልሞች ቢኖሩትም ተግባራዊ እንቅስቃሴው ግን ኮሳሳ ነበር።

<u>አምስተኛ) የገንዘብ አቅም ችግር፤</u>

እንደሚታወቀው ኅብረቱን የመሠረተው ጉባዔ ተግባራዊ መሆን የቻለው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን ባደረጉት አስተዋጽዖ ብቻ ነው። ኅብረቱ ከተመሠረተም በኋላ የተለማቸውን የትግል እቅዶች ተግባራዊ ለማድረግ የተማመነው በወገን ኢትዮጵያውያን ላይ ነው።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከሁለት መሥራች አባል ድርጅቶች ጋር የተከሰተውን ችግር ተከትሎ በተለይም በነሱ በኩል የተደረገው ኅብረቱ ከሕዝብ እርዳታ መሰብሰብ የለበትም በሚለው ቅስቀሳ ምክንያት ኅብረቱ ጠንካራ ሥራዎችን ለመሥራትና እቅዶቹን ተግባራዊ ማድረግ እንዳይችል በከፍተኛ ደረጃ ጎድቶታል። በአገር ውስጥ ከዋና ጽ/ቤቱ ጀምሮ የየአካባቢ ቅርንጫፎችን ከፍቶ፥ ዓላማውን በሰፊው እያስረዳና ሕዝብን እያደራጀ በስፋት እንዳይንቀሳቀስ ደንቃራ ሆኖበታል። ይኸም በምርጫ ዙሪያ ኅብረቱ ሊያደርግ ይችል የነበረውን ሁሉ እንዳያደርግና ሊያስመዘግብ ይችል የነበረውን ውጤት እንዳያገኝ አድርጎታል፤ በጣም ጎድቶታል። በገንዘብ ችግር ምክንያት በውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭም በተለይ በጎረቤት አገሮች አካባቢ ሊሠሩ የሚችሉና የታቀዱ ሥራዎችን መሥራት አልተቻለም። የውጭ ጽ/ቤቶቻችን አሁንም በአባል ድርጅቶች መሥሪያ ቤቶች ውስጥ

ስለሆኑ ለቢሮ ኪራይም ሆነ የጽ/ቤት መገልገያዎችን ሁሉ ሳናስብ እስካሁን ቀጥለናል። በዚህ እረገድ ጽ/ቤቶቻችንን ለሚያስተናግዱ አባል ድርጅቶች ምስጋና ይገባል።

እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ከመጀመሪያ ጀምሮ በመንፈስ-ጠንካራነትና በኅብረቱ ዓላማዎች ላይ ባላቸው እምነት ብቻ በመነሳት በርካታ ኢትዮጵያውያን በድጋፍ ኮሚቴም፥ በቤተሰብም፥ በግልም ይኸ ነው ተብሎ ተመን ሊወጣለት የማይችል ያላቋረጠ እርዳታ ማድረጋቸው ነው። እነዚህ ውድና ክቡር ዜጎች ገንዘባቸውንም ጊዜአቸውንም መስዋዕት አድርገው በአጭር ጊዜ ውስጥ ባደረጉት እርብርብ ኅብረቱ በምርጫው ያገኘውን ውጤት እንዲያመጣ አስችለዋል። እስካሁንም፥ በተለይም በኅብረቱ ከፍተኛ የሃላፊነት ቦታ ተመድበው የነበሩት ሁለት የቀድሞ አባላት ባልተጠበቀ መልክ ያልጠበቅነውን ሕገ-ወጥና አንገት-አስደፊ እርምጃ ከወሰዱ በኋላ ብዙ ሰው ከኅብረቱ ጎን መሰለፍ ቀርቶ ስለኅብረቱ አንስማ ባለበት ጊዜ ኅብረቱንና ግለ-ሰቦቹን በመለየት፥ ኅብረቱ የቆመለትን እስትራቴጂካዊ ዓላማ በማክበር፥ "እምነት እስከ ሞት" እንዲሉ እነሆ በየድጋፍ ኮሚቴው ያሉ ወገኖቻችን በሚደንቅና በሚያኮራ ሁኔታ የኅብረቱን አርማ ከፍ አድረው ይዘው አቆይተዋል። ሰው በግብር እና በችግር ይፈተናል ነውና እነዚህ ወገኖቻችን በዚህ ክቡር ተግባራቸው ለኅብረቱ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያም ባለውለታዎች ናቸው። ኅብረቱ ወደፊት ዓላማውት ሳይለቅ በትግሉ እንዲቀጥል የነሱ ድጋፍ እንደማይለየው በሙሉ እምነት መናገር ይቻላል። ድጋፋቸው በገንዘብ ብቻ ሳይወሰን በልዩ ልዩ ወቅታዊ ጉዳዮችና በትግሉም ላይ የመሥመር ጥራት እንዲኖር በጣም ጠቃሚ ሃሳቦችን በማቅረብ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።

## ክፍል አምስት፤

### 5-1) ቀጣዩ እርምጃ፥ የመፍትሔ አሳቦች፤

እንደሚታወቀው ማንኛውም ድርጅት እክሎችና ችግሮች ይገጥሙታል። አንድን ድርጅት በተለይም የትግል ድርጅት ከሚገጥሙት ችግሮች ሁሉ የበለጠ ከባዱ የውስጥ ችግር ነው። ኅብረታችን በአንድ በኩል በውስጡ የተከሰቱ የተጠበቁም ያልተጠበቁም ድርጅታዊ ችግሮችን አስወግዶ ትኩረቱን ወደ ተመሠረተበት በአገራችን ላይ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን የማድረግ ብሔራዊና ሕዝባዊ ዓላማ ላይ ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ እየሞከረ ነው። ተወደደም ተጠላ ይኸ ኅብረት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ የጋራ ትግል ጠቀሜታን ብቻ አይደለም የበሰለና የጠራ የትግል መሥመር የማስያዝ ሚና ተጫውቷል።

በሰኔው ምርጫ ጉልህ ሚና የተጫወቱት ቅንጅቱም ኅብረቱም አሁን ባለው የአገሪቱ ሁኔታ የሕዝቡን ትግል ለውጤት በሚያበቃ ሁኔታ እየመሩት አይደለም። ምክንያቱ ሊለያይ ቢችልም ሁለታችንም ብቃት ያለውና አስተማማኝ አመራር እየሰጠን አይደለም። ይኸን መራር ሃቅ መቀበል ያስፈልጋል። አመራር ያጣ ትግል፥ ተቀባይ ያጣ ድል ይሏል ይኸ ነው! በመሆኑም ኅብረቱ ከቅንጅቱ፥ ከሌሎች ዴሞክራሲያዊና አገር-ወዳድ ኃይሎች፥ ከሲቪክና የሙያ ማኅበራት ጋር በመሆን አሁንም ይኸንን የሕዝብ ትግል አቅጣጫ የማስያዝና ሕዝባችን በአምናው ግንቦት ያስመዘገባቸውን ድሎች ያለማስነጠቅ ሃላፊነት ብቻ ሳይሆን ግዴታ አለበት። እዚህ ላይ በድጋሚ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ እንኳን ትግሉን መልካም ድምዳሜ ላይ ለማድረስ ይኸን ለትግሉ አዲስ እስትንፋስና ሕይዎት የመስጠት ከፍተኛ ብሔራዊ ሃላፊነትና ተግባር መከናወን የሚችለው በተባበረና ቀጣይነት ባለው የጋራ ትግል ብቻ መሆኑን ነው። ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሕዝባችንን ለማተራመስና እርስ በርሱ ለማናከስ የሚያደርገውን የመከፋፈል ከይሲ ጥረት ሁሉ በተግባር መቋቋም ያስፈልጋል። አሁን በአንዳንድ ክፍሎች የሚታየው በገዥው ፓርቲ ምክንያት የአንድን አካባቢ ሕዝብ በደፈናው እንደ ወንጀል ተባባሪ ማየትን መታገልና ፈጽሞ ማስወገድ ያስፈልጋል። በዚህ ጎዳና

የተሰለፉ ሁሉ አገርንና ወገንን ሳይሆን የሚጠቅሙት አምባ-ገነኑን አገዛዝ ብቻ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ባለውለታው ናቸው፡፡

ይኸን የመሰለ አኩሪ የሕዝብ ንቁ ተሳትፎ እያለ ትግሉን ለውጤት አለማብቃት ምን ጊዜም ይቅርታ የማይደረግለት ድክመት መሆኑን አዎንታዊ ለውጥ በአገራችን ላይ አመጣለሁ ብሎ የሚታገል ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት በተገቢ ሊያጤነው ይገባል፡፡ አሁንም ተቃዋሚው የገጠመው ችግር ላለፉት ከሰላሣ ዓመታት በላይ አብሮት የቆየና ያልተለየው ሁኔታን በተገቢና በወቅቱ መጠቀም ካለመቻል የተነሳ አጀንዳውን ለረጅም ጊዜ መቆጣጠር ብቁ ሆኖ ያለመገኘትና በተደጋጋሚ አንጻር ሆኖ ለሚታገለው ክፍል አሳልፎ ከመስጠትና ተከላካይ ሆኖ ከመቀጠል አባዜ መውጣት አለመቻል ነው፡፡ እቅድ ይወጣና ሕዝቡ የእኔ ነው ብሎ እንዲታገልበት ጥሪ ይቀርባል፥ ለተፈጻሚነቱ እስከ መጨረሻ አይገፋም፥ ተለዋጭ መሥመሮችና ስልቶች በተከታታይና በወቅት በወቅቱ አይቀርቡም፥ እንዲሁ በዝርግ ይተዋሉ፡፡

በአሁኑ ጊዜ ኢሕአዴግ በሚያደርጋቸው እንደ ማሰር በመሳሰሉ የሽብር እርምጃ ውጤቶች ላይ ድርጅቶች የሚያሳዩት የተቃወሰ የትኩረት አቅጣጫ (ያውም ባልተቀናጀ መልክ) በሕዝብ ዘንድ ሰርጾ እንዲገባ እየተደረገ መሆኑ ትግሉ እንዲድበሰበስና አምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓቱ ጊዜ እንዲገዛ ከመርዳና የሕዝቡ ሰቆቃ እንዲቀጥል ከመፍቀድ ውጭ የሚያመጣው አንድም አዎንታዊ አስተዋጽዖ የለም፡፡ ይኸ አዝማሚያ ትግሉን አዚም ውስጥ የሚጥል አደገኛ አመለካከት ነው፡፡ ስለሆነም የሕዝቡ ትግል በአዲስ መልክ አቅጣጫ እንዲይዝ ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው አጣዳፊ ጉዳይ በመሆኑ ይኸ አቅጣጫ እንዴት መስተካከልና እንዴት መቀጠል እንዳለበት በአጭሩና በማያሻማ መንገድ መገለጽ ይኖርበታል፡፡ በአገራችን ያለውን ቀውስ በግልጽ መረዳት፥ ማሳየትና ሁኔታውን ለመቀየር የምንከተለውን የትግል ስልትና ዘዴ ሁሉም ሊረዳው በሚችልበት መንገድ መሆን ይኖርበታል፡፡ የተቃዋሚው ዋነኛ የፖለቲካ ጥያቄ ምንድን ነው? እስረኛ ማስፈታት?፥ በኢሕአዴግ የሚደረግን ይኸንን ወይም ያንን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ማስቆም?፥ የሕዝብ ድምፅ እንዲከበር መጠየቅ?፥ አገዛዙ በሥልጣን ላይ የመቆየት የሞራልም ይሁን ሕጋዊ ብቃት ስለሌለው ይወገድ?፥ የዴሞክራሲ ተቋማት ይገንቡ?፥ አዲስ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም?፥ ወዘተ... ወይስ ሁሉም? ሁሉም ከሆነ በምን ቅደም ተከተልና እንዴት? ለሚሉት ጥያቄዎች አጥጋቢና ተግባራዊ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ መንገዱንም በግልጽ መተለምና ሕዝባችን ለነዚህ እውነንት እንዲታገል በጋራ የሚቀርቡለት የትብብር ጥሪዎች እንደዚሁ ግልጽና ተፈጻሚነት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

በእኛ እይታ በሁሉም መመዘኛ ኢሕአዴግ የመንግሥትነት ባህሪውን አጥቷል፡፡ ስለሆነም ኢሕአዴግ በምንምና በማናቸውም መንገድ በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሞት ሽረት ትግል እንደሚያደርግ፥ ድርጅቶቹ በተናጠል ተፈላጊውን ውጤት የሚያስገኝ አመራር መስጠት አለመቻል፥ ከማንምና ከምንም በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብቱ መከበር ብቸኛና አስተማማኝ ወገኑና አቅሙ እራሱ መሆኑን፥ ወዘተ ... ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡ ትግሉም በ'አይቸው ብመለስ' ዓይነት የገበጣ ጨዋታ ሳይሆን ጠመዝማዛ፥ መራርና ብርቱ መሆኑን ያጤኗል፡፡

## 5.1.1) ድርጅታዊ ጥንካሬ፤

ቀደም ሲል በክፍል ሦስት እንደተጠቀሰው ሁሉ ኅብረቱ የተለመውን ቅዱስ አገራዊ ዓላማ እውን እንዲሆን ሰፊ መሠረት ያለው እንቅስቃሴ ለማድረግ እቅዶች አሉት፡፡ ሆኖም ኅብረቱ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመሥራት ከማሰቡ በፊት በቅድሚያ እራሱን ማጠናከር ይኖርበታል፡፡ ይኸ ሲሆን ብቻ ነው በሕዝብ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ድርጅቶችም ዘንድ ከበሬታንና ተደማጭነትን ባገኘ መልኩ ውጤት ያለው ሥራ መሥራት የሚችለው፡፡

ድርጅታዊ ጥንካሬ የሚፈተነው በችግር ጊዜ የሚገጥሙ መሰናክሎችና እክሎችን ተቋቁሞ መገኘትን ብቻ አይደለም። ማንኛውም ድርጅት ካለፈው ወር በዚህ ወር፥ ካለፈው ዓመት በዚህ ዓመት የተሻለ የእድገት ደረጃ፥ የመሻሻል ሁኔታ ላይ መሆኑን ሆኖ ለመገኘት ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። እየሰለሉ ዕድሜ መቁጠሩ ብቻውን ግን ጥንካሬ አይሆንም። ስለዚህ ኅብረቱ እራሱን ለማጠናከር ልዩ ጥረት ማድረግ ያስፈልገዋል።

5.1.2) <u>አዲስ የኃይል ሽግሽግና ስብስብ፤</u>

በኅብረቱ በኩል አሁንም ቀደም ሲል በልዩ ልዩ ይፋ መግለጫዎቹና ለድርጅቶች ባቀረባቸው ሃሳቦች እንደተገለጸው ሁሉ በዚህ ትግል የኃይል አሰላለፉ በነጠረ መልኩ የተቃዋሚው ክፍል ከሕዝብ ጋር በአንድ በኩል፥ የኢሕአዴግ አምባ-ገነኖች በሌላ በኩል እንደሆነ የሚያሳይና በግልጽ የተሰመረበት መሆን ይኖርበታል። አሁን ባለው ኢሕአዴግ ከሕዝብ ጨርሶ በተነጠለበትና በአረመኔአዊ ተግባሩ ምክንያት አንቅሮ በተተፋበት የውጥረት ሁኔታ በተወሰኑ ድርጅቶች የጠበቀና የተቀናበረ ዘመቻ ገዥውን ፖርቲ ከሥልጣን ማስወገድ አይቻልም አይባልም። ይኸንን እውን የማድረጉ አጋጣሚ ሰፊ ነው። በኢሕአዴግ በአጠቃላም ይሁን በኢሕአዴግ አባላት በኻል በተለይ ሕወሓት ውስጥ ሊከሰት በሚችል ቅራኔ ገዥው ፓርቲ ጨርሶ መቆጣጠር ወደማይችልበት ደረጃ ሊደርስና ሊወድቅ የሚችልበትም ጠባብ አጋጣሚም ሊፈጠር አይችልም አይባልም። የኢዴኃኅ (የኅብረቱ) ትግል ግን የመንግሥት አቀያየሩ ሁኔታ በአቦ-ሰጡኝም ይሁን በሌላ አጋጣሚ አገዛዙን ማስወገድን በተናጠል ያነጣጠረ ሳይሆን ይኸ ሂደት የሰከነ ሽግግር ሊያስገኝ የሚችል ሁኔታን ለማመቻቸት ነው። የአገዛዙ ውድቀት አገርን አብሮ የሚጥልም ሆነ ሕዝብን የሚከፋፍልና አገራችንን አዲስ የቀውስ አውድማ የሚያደርግና ሕዝባችንን ለከፋና ለማያባራ ትርምስ የሚያጋልጥ መሆን አይኖርበትም። ስለሆነም ነው ኅብረቱ በተደጋጋሚና ያለመታከት የአገር-ወዳድና የዴሞክራት ኃይሎችን መሰባሰብ የሚወተውተው። ጥረታችንና ትኩረታችን ሕዝባችን በመራር ትግሉ በአለፈው ግንቦት ያስገኘው ተስፋ ጨርሶ ሳይጨልም በመረባረብ የሕዝባችን ስቃይ አክትሞ፥ የሚያንዣብበው የመከፋፈል አደጋ ተወግዶ፥ የአዲስ ሥርዓት በር ቀዳጅ መንገድን በመከተል የሰከነ ሽግግር ማድረግ ለማስቻል ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋና እየተወሳሰበ የሄደውን የአገራችን ሁኔታ አሁንም በአንድ ድርጅት ወይም በተወሰኑ ድርጅቶች አቅም መፍታት ፈጽሞ እንደማይቻል ግልጽ ነው። ኢሕአዴግ በሕዝባችን ላይ ያወጀውን የሽብር ጦርነት ከመቋቋምና የታሰሩ ዜጎቻችንን ለማስፈታት ካለው እንቅስቃሴ ጀምሮ፥ ለሕዝባችን የዝንት-ዓለም ሰቆቃና መብት መነፈግ ችግሮች ዘለቄታዊ መፍትኄ ለማስገኘት ሰፊ መሠረት ያለው እንቅስቃሴ ማካሄድ ስለሚያስፈልግ በዚህ እረገድ ኢዴኃኅ (ኅብረቱ) በማድረግ ላይ ያለውን የበኩሉን አስተዋጽዖ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያደርገው ጥረት ልዩ ልዩ እንቅፋቶች እንደሚገጥመው መጠበቅ አለበት። በተለይም የዚህን ዓይነት ስብስብ ለራሳቸው አጀንዳ ማሚያ ለማድረግ አንዳንድ “የውጭ” ክፍሎች ሽር ጉድ ማለታቸውና ከተቃዋሚው ውስጥም አንዳንዱ ይኸንን አጋጣሚ በመጠቀም የራሳቸውን ውሱን ዓላማ ለመገፋት ሌሎች ደግሞ የእነሱ ሥልጣን መያዝ የሕዝብ ድል የሚመስላቸውና ትግሉን አቅልለው የሚያዩ ክፍሎች የየሩቁ ሳይታያቸው በግብዝነት ተመርተው በነጣላው ኢሕአዴግን ለማውረድ በሚል ቀቢፀ-ተስፋ የጓዳ ድርድር መሞከራቸው መጠበቅ አለበት። የዚህ ዓይነት የጓዳና ሁሉንም ያልጨመረ የመሰባሰብ ጥረት ውጤቱ የታሰበውን ጠንካራ የጋራ መታገያ መድረክ አለማስገኘት ብቻ ሳይሆን ባልታየና ባልተጠበቀ መንገድ ትግሉን አመሰቃቅሎ ከአንዳንዶቹ ጋር ወደፊት የሚኖረውን አብሮ የመሥራት ዕድል ሊያበላሽ መቻሉ ሊያሳስብ ይገባል።

የተቃዋሚውን ኃይል በአዲስና በስፋት የማሰባሰቡ ጥረትና የሚደረገው እንቅስቃሴ በአራት እረድፍ ሊቃኝ ይገባዋል።

5.1.2.1) ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ፤

5.1.2.2) ከሲቪክና የሙያ ማኅበራት፤

5.1.2.3) የትጥቅ ትግል ከሚያካሂዱ ጋር፤
5.1.2.4) የሕዝብ ወገን የሆነ አጠቃይ ሰፊ ስብስብ፣

## 5.1.2.1 ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር፤

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ኢዴኃኀ የውስጥ ድርጅታዊ ይዞታውን የተሻለ እያጠናከረ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚያደርገውን የትብብር ጥረት ጥንቃቄ በተሞላበትና በየደረጃው ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል። ይኸ ኃይሎችን የማሰባሰብ እንቅስቃሴ ከነማን ጋር፥ እንዴትና መቸ ለሚሉት ጥያቄዎች ዝርዝርና በቂ ነው ማለት ባይቻልም መልስ ሰጥቷል። ለዚሁ መሰባሰብ ዓላማ ምክክር ለማድረግ እንዲቻል ለቅንጅትና ለኦነግ ጥሪ አቅርቦ በቅንጅት በኩል አመራሩ በእስር ላይ ስለሚገኝና ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል አካል ባለመኖሩ የሚጠበቀው መልስ ባይገኝም ከኦነግ ግን አዎንታዊ ምላሽ ተሰጥቷል። የመጀመሪያ ደረጃ ተከታታይ ውይይቶችም ተካሂደዋል። በኅብረቱ እምነት ከኅብረቱ፥ ከቅንጅቱና ከኦነግ የተውጣጣ አንድ የጋራ ጊዜአዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ የኃይል ማሰባሰቡን ጥረት ሥርዓት ባለው አካሄድ እነማንን?፥ መቸ?፥ እንዴት? የት?፥ ወዘተ... ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ እየሰጠ ጊዜ ያልፈጀ ዝግጅት መደረግ ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። የዚህ ዓይነት አካሄድ መጠላለፍንና መጠራጠርን አስወግዶ፥ መተማመንን እያዳበረ የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኝ እምነታችን ነው። በዚህ የረጋ አካሄድ የሚደረግ መሰባሰብ መሠረቱ የጠነከረና ለጋራ ችግሮቻችን ዘለቄታዊ መፍትኄ ለማስገኘት ለሚደረገው ጥረት አስተማማኝ ይሆናል።

ቀደም ሲል አንዳንድ የጋራ ሥራዎችን ከቅንጅቱ ጋር መሥራታችን ይታወቃል። በአሁኑ የፖለቲካ ሁኔታም ይኸ የጋራ ሥራ ጅማሮ ቀላል መሆን ቢገባውም እውነታው ሌላ ሆኖ የብቻ ጉዞ ሲቀነቀንና ኢሕአዴግን ብቻ በሚጠቅም መልኩ ከኅብረቱ ርቆ ለመገኘት የሚሰነዘሩ አባባሎችና አንዳንድ ተግባሮች መከሰታቸው ለኅብረቱ አግራሞትን ያተረፈ ጉዳይ ሆኖበታል። ሆኖም አሁንም ከቅንጅቱ ጋር ( ሙሉ ውክልናና ውሳኔ መስጠት የሚችል አካል በቅርቡ ሊኖረው ከቻለ፥ ካልተቻለም በውጭ ከሚገኙ የድጋፍ አካላትና አባላት ውስጥ በጋራ ሥራ ላይ አመኔታና ሰፋ ያለ አመለካከት ካላቸው አባላቱ ጋር) ለመሥራት የሚደረገው ጥረት መቀጠል ይኖርበታል። ኅብረቱ በሁለተኛ አስቸኳይ የሸንጎ ጉባዔው ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ሰፋ ያለ ስብስብ እንዲኖር ከቅንጅቱና ከኦነግ ጋር የሦስትዮሽ የሥራ ግንኙነት ሊኖረውና እነሱ በጋራ በተስማሙበት ሁኔታ ሌሎችን በጨመረ መንገድ የጋራ የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል አቋቁመው በውጭ የሚደረገውን ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ፥ ከአገር ውጭ የሚገኘው ኅብረተሰባችን የሚያደርገውን ትግል በአንድ-ወጥ በተቀናበረ መልክ እንዲያካሂድ በማደራጀት፥ በአገር ውስጥ የሚደረገውን ትግል በማስተሳሰሩና በማቀናበሩ፥ ወዘተ... ዙሪያ ውጤት ያለው ሥራ እንዲሠሩ ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። በእርግጥ ያለውን ሁኔታ በጠዛባ መልኩ ከመረዳት የመነጨ አጉል መኩራራትና ለብቻ የመሄድ ወይም ሁኔታውን ተጠቅሞ የራስን ጠባብ አጀንዳ ለማራመድ በአንዳንዶች ዘንድ ሙከራም ምኞትም ሊኖር ይችላል። ሆኖም በኅብረቱ በኩል መተክሉን ያልለቀቀና የነገውን ባየ መልኩ የድርጅቶች ትብብር እንዲኖር የሚቻለውን ሁሉ በትዕግሥትና በጥሞና ማድረግ ይኖርበታል። የዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡም የአቶ መለስ አገዛዝ የታሰሩን እንዲፈታ፥ በዜጎች ላይ እያደረሰ ያለውን የግፍ እርምጃ እንዲያቆም፥ እስካሁን በወሰዳቸው ሕገ-ወጥ የግፍ እርምጃዎች ምክንያት በዜጎች ላይ የደረሰውን ግድያ፥ እስራት፥ ግፍና መከራ፤ የሚያጣራ አንድ ዓለም-አቀፍ አጣሪ ኮሚቴ እንዲቋቋም፥ ያለውን ቀውስ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ይቻል ዘንድ ወደ ድርድር እንዲመጣ፥ ወዘተ.. ከመግለጫ የዘለለ ጫና እንዲደረግና አስገዳጅ እርምጃዎችም እንዲወሰዱ የተቀናበረ ዘመቻ በጋራ ማድረግ አንደኛው የጋራ ስብስቡ ተግባር ይሆናል። ከሁለቱ ድርጅቶች ጋር የሚኖረው የትግል ትብብር ሁሉም በተስማሙበትና ሌሎች ኃይሎችን በጨመረ መልኩ አገር-አቀፍ የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል አቋቁሞ የመሥራቱ ጉዳይ በኅብረቱ ፍላጎትና ግፊት ብቻ ሳይሆን የእነዚህን ወገኖች ተመሳሳይ ግፊት ስለሚጠይቅና ይኸም ምን ያህል

ጊዜ እንደሚፈጅ ስለማይታወቅ ይኸ እስከሚሆን በተናጠል በሚደረግ የጎንዮሽ ግንኙነት አንዳንድ በአገር ውስጥ የሚሰሩ የትግል ትብብሮችን መቃኘቱ መልካም ይሆናል።

## 5.1.2.2 ከሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ስብስቦች ጋር ፤

ለሥርዓት ለውጥ መምጣት የተመቻቸ ሁኔታን በአገራችን ለመፍጠር የምናደርገው ትግል በሕዝብ ታቅፎ የተሻለ ውጤት እንዲኖረው የፖለቲካ ድርጅቶች ከሲቪክና ከሙያ ማኅበራትና ስብስቦች ጋር የተቀራረበ ትስስር መኖር እንዳለበት በመርኅ ደረጃ በመቀበል ብቻ ሳይወሰን ምንም እንኳ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አርኪ ውጤት ባያስመዘግብም ይኸንን እውን ለማድረግ ኅብረቱ ከምሥረታው ጀምሮ ሙከራዎችን ከማድረግ እንዳልተቆጠበ ይታወቃል። ለዚህም የትግል ትስስር ከላይ እንደተጠቀሰው ለፖለቲካ ድርጅቶቹ እንደተፃፈው በተመሳሳይ ሁኔታ ኅብረቱ ቢያንስ ለሦስት ማኅበራትና ስብስቦች ማለትም ለአንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር (ኢመማ)፥ ለኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጠኞች ማኅበር (ኢነጋማ)፥ ለኢትዮጵያ አገራዊ ጉባዔ (ኢአጉ) ደብዳቤ በመጻፍ የትግል ትብብር እንዲደረግ ጠይቋል። አንድ የሕዝብ መነሳሳት ድርጅታዊ ይዞታ ከሌለው ውጤቱ ትርምስ ሊሆን ይችላል። ሕዝባዊ መነሳሳት የፖለቲካ ድርጅቶች ከልዩ ልዩ የሙያና የሲቪክ ማኅበራት ጋር በሚያደርጉት የተቀናጀ አካሄድ እንዲመራ ያስፈልጋል። የፖለቲካ ድርጅቶች ከሕዝቡ ጋር የሚኖራቸውን የትግል አጥር የሚማግሩት በነኝክ አማካይነት መሆኑ ለትግሉ ቀጣይነትና ሕዝባዊነት ዋስትና ነው። ስለሆነም ኅብረቱ አሁንም ከነኝህ የትግል አጋር ወገኖች ጋር የሚያደርገውን ጥረት ያለመታከት ሊቀጥልበት ይገባል። ከነሱ ጋር የሚደረገው የጎንዮሽ ግንኙነት በቶሎ ከፖለቲካ ድርርጅቶች ጋር ካለው ግንኙነት ጋር እንዲጣመር ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

እንደሚታወቀው የአቶ መለስ አገዛዝ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ አገር-አቀፍ የሲቪክና የሙያ ስብስቦች እንዳይኖሩ፥ ያሉትም ቢያንስ እንዲኮስሱ ስላደረገ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሌላ ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ቁጥጥር ውጭ የሆነ ለሕዝቡ ትግል ተአማኒነት ያለው ገለልተኛና ጠንካራ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ስብስብ ወይም ማኅበር በአገራችን እንዳይኖር ከፍተኛ ተጽዕኖ እየተደረገበት ያለ ሁኔታ ጎልቶ ይታያል። አሁን ባለው የአገሪቱ ሁኔታ እነኝህ የኅብረተሰባችን ክፍሎች ልክ እንደ ፖለቲካ ድርጅቶቹ እነሱም ላይ አገዛዙ በሚያደርሰው ጭካኔ የተሞላበት የአፈና ዘመቻ ተውጠው ድምፃቸውን ማሰማት ባይችሉም የመንግሥት ጫናና ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ቁጥጥር እየተደረገም ቢሆን በአለፉት ዓመታት በልዩ ልዩ ዓላማዎች ሥር ለልዩ ልዩ ጥቅሞችና አገልግሎቶች በርካታ ስብስቦች ከመቸውም ጊዜ የበለጠ እንደ አሸን ፈልተዋል። ከጥቂት ቀናት በፊት በጄኔቭ የወጣቶችንና የሕፃናትን መብት አስመልክቶ በተደረገ ጉባዔ ላይ በዚህ የልጆችና የወጣቶች መብትን በማስከበሩ ጉዳይ ላይ የሚሠሩ ወደ ስድሳ የሚደርሱ አገር-በቀል ስብስቦችን የያዘ መድረክ (ፎረም) ተወካይ አማካይነት የቀረበው ዘገባ ሁለት ቁም ነገሮችን ይጠቁማል። አንደኛ በድኅረ-ግንቦት የአገራችን ሁኔታ የኢሕአዴግ አገዛዝ በሕዝባችን ላይ ያወጀው የግፍና የሽብር ዘመቻ ገፈት ቀማሽ ታዳጊ ልጆችና ወጣቶች መሆናቸው፤ ሁለተኛ የእነዚህ ስብስቦች ተወካዮች ናዝሬት (አዳማ) ተሰብስበው ስለሚፈጸመው ግፍ ከተወያዩ በኋላ ይኸንኑ ክስተት በዘገባ መልክ በአገር ውስጥ ለማቅረብ ቢያስቡም የአገዛዙን የተጠበቀ አረመኔአዊ ምላሽ በማወቅ ዘገባውን ለውጭው ዓለም ለማሳወቅ በመወሰን አሁን እንዳቀረቡት አቶ ሳምሶን በተባሉ የጋራ መድረኩ (ፎረሙ) አስተባባሪ ተገልጿል። ይኸ ሚያሳየው የአቶ መለስ አገዛዝ እነኝህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ቅታቸው እንዲጠፉ ያላሰለሰ ጥረት ቢያደርግም በርካታ የልዩ ልዩ መብቶችና ጥቅሞች ሃቀኛ ተሟጋች ስብስቦች እንደሚኖሩና ሁኔታው ቢፈቅድ በቀላሉ ለማበብ ጊዜ እንደማይፈጅባቸው ነው።

በፖለቲካ ድርጅቶችና በሲቪክና የሙያ ድርጅቶችና ስብስቦች መኻል የቆየውን ተቀራርቦ የመሥራት ልማድ እጥረትንና የአለመተማመን አዝማሚያን አስወግዶ አሁን ካሉት ጋር በቅንነትና በቅርበት መሥራቱ ተገቢ ነው። ይኸ እርምጃ ሌሎችም እራሳቸውን

ችለው መንቀሳቀስ እንዲችሉ ሊያደፋፍራቸው ይችላል። የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በፖለቲካው እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ማድረጉ በፖለቲካ ድርጅቶች መኻል ያለውን አጉልና መሠረተ-ቢስ የርስ በርስ አለመተማመን በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ ያግዛል።

የፖለቲካ ድርጅቶችና የልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍል ተወካይ ማኅበራትና ስብስቦች ትብብር የሚያስፈልግበት ምክንያት ትግሉ አሁን ባለበት ደረጃ የፓርቲ ፖለቲካ የሚካሄድበት ብቻ ተደርጎ መታየት የሌለበትና በተወሰኑ የጋራ ነጥቦች ዙሪያ ሰፊ የጋራ እንቅስቃሴ የሚደረግበት ሰፊ የትብብር መስክ ስላለ ጭምር ነው። በእርግጥ በአንድ በኩል አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች አሁንም እንኳ በአለው የሁሉንም ትብብር የሚጠይቅ የአገሪቱ ሁኔታ ትግሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሃላፊነት ብቻ እንደሆነና የሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ስብስቦችን "ሲያስፈልግ" ብቻ እንዲተባበሩ ከማድረግ የዘለለ የትግልል ትስስር አስፈላጊ እንዳልሆነ፥ "እርባና" ያላቸው የሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ስብስቦችም እንደሌሉ ይከራከራሉ። በሌላ በኩል አንዳንድ የኅብረተሰብ ስብስቦች በአገር ጉዳይ ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር አብሮ መሥራት ፖለቲከኛ ያደርገናል ዓላማችን እሱ አይደለም እናንተው የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ በርቱ የሚሉ አሉ። እነኝህ ወገኖች፥ የሐይማኖት ይሁኑ የኅብረተሰብ አገልግሎት ሰጭ፥ ወዘተ… ሊገነዘቡት የሚገባ የሰብኣዊ መብት አይጣስ፥ ዜጎች (ሰው) ያለ ሕግ አይታሰር፥ አይሰቃይ፥ አይገደል፥ ያለጥፋታቸው የታሰሩ ይፈቱ፥ ዜጎች ሰላም ያግኙ፥ ችግር ይጥፋ፥ በሽታ ይጥፋ፥ ረሃብ ይጥፋ፥ እርቅና ሰላም ይውረድ፥ ወዘተ… ማለት የፖለቲካ ፕሮግራምን የሚጠይቅ ወይም ፖለቲከኛ የሚያሰኝ ሳይሆን ሰው ሆኖ መፈጠርን፥ ለፍትኅና ለበጎ ነገር መቆምን የሚያሳይ ተግባር መሆኑን ነው።

ከነኝህ ወገኖች ጋር የሚደረገው የመሰባሰብ ጥረት የጊዜ ገደብ ተሰጥቶት ያለ ብዙ መጓተት በአጭር ጊዜ ውስጥ መገኘት ከሚችሉት፥ ፈቃደኛ ከሆኑትና ሃላፊነት ከሚሰማቸው ጋር የጋራ ሥራ መጀመር እንዳለበት የኅብረቱ እምነት ነው።

### 5.1.2.3 የትጥቅ ትግል ከሚያካሂዱ ክፍሎች ጋር፤

የአቶ መለስ ቡድን ሳለመገዛት የቆረጠን ሕዝብ በኃይል ለማንበርከክ የሚያደርገውን የተስፋ መቁረጥ እርምጃ በገፋበት ቁጥር የባሰ ዋኝቶ ሊወጣበት በማይችል የወንጀል ባሕር ውስጥ እራሱን እየዘፈቀ የእርቅና የሰላሙን ሂደት ይበልጥ እያወሳሰበው ይገኛል። ይኸም ሁኔታ የሰላሙን አቅጣጫ ጭራሹን ዋጋ እንደሌለው በመቁጠር የመሣሪያ መፋለሙን ብቻ በነጠላው የሚገፉ ክፍሎች የሕዝቡን ብሶት በመጠቀም ለመሰብሰብ አዳጋች ወደሆነ በተበተነና በተሰበጣጠረ አቅጣጫ ሊወስዱት መሞከራቸው አይቀርም። ይኸ ሁኔታ የሶማሌን ዓይነት ጦረኛ አውራዎችን በየአቅጣጫው ሊሚፈጥር ይችላል። "የሚሰጥም ገለባ ይጨብጣል" ነውና በአስቸኳይ የጠራ የትግል አቅጣጫ የሚያስይዝና ታግሎ የሚያታግል ብሔራዊ አመራር ካልተሰጠው ሕዝባችን አሁን እየደረሰበት ባለው ግፍና መከራ ምክንያት ለዚህ አደጋ ሊጋለጥ ይችላል። ከአሁኑ በዚህ አቅጣጫ የሽሚያ ሩጫዎች እየታዩ ነው። ምንም ዓይነት በብሔራዊ አጀንዳነት ያልቀረበ የትግል መሥመር ግፋ ቢል አገዛዙን ከማቁሰል የማይዘልና ለቆምንለትና ለምንታገልለት የመልካም ሥርዓት ግንባታ ዋስትና እንደማይሆን ብቻ ሳይሆን ውሎ አድሮ ሕዝብንና አገርን ከመጉዳት እንደማይዘል ወይም ዘለቄታዊ ጠቀሜታ እንደሌለው ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ኅብረቱ ከምሥረታው ጀምሮ የትግል ዘዴው ሰላማዊ እንደሆነ አሳውቋል። አሁንም መሠረታዊ የእምነት ለውጥ አላደረገም። የራሱ ሠራዊትም የለውም። ሆኖም ሕዝባችን በኢሕአዴግ የሚደርስበት አረመኔአዊ ጭፍጨፋና ግፍ ማንም ሊሸከመው የማይገባና ማንም ቢሆን ባዶ እጁን የሚደበደብን ሕዝብ ዝም ብለህ ተደብደብ ብሎ ተፈጥሮአዊ የሆነን እራስን የመከላከል መብት መንፈግ ተገቢ አይደለምና የተዘጉት የሰላማዊና የሕጋዊ የትግል መድረኮች እስከሚከፈቱ ዜጎች ባመቻቸው መታገላቸውን መቃወም አይቻልም። በትጥቅ ትግል ላይ የተሰማሩ ወገኖቻችንም መርጠው ሳይሆን ተገደው ስለሆነ ኅብረቱ ትግሉ የጋራ

ነውና የተሻለ አካሄድ የሚመስለውን ከመጠቆምና አስፈላጊው ጥንቃቄ ካልተደረገ የዚህ ዓይነት ትግል ሊያስከትል የሚችለውን አደገኛ መዘዝ ከማሳሰብ ወደ ኋላ አይልም።

ኢዴኃኅ የፖለቲካ ድርጅቶችን መሰባሰብ አስፈላጊነት ተረድቶ ለዚሁ እውንነት የበኩሉን ጥረት እንደሚያደርግ ሁሉ በአብዛኛው አገዛዙ የሰላማዊውንና የሕጋዊውን የመታገያ መድረኮች ጥርቅም አድርጎ ዘግቶ የሚያደርሰውን ግፍ ለመቋቋምና መብትን ለማስከበር አማራጭ ከማጣት የትጥቅ ትግል ፍልሚያዎች በማድረግ ላይ ያሉ ወገኖች ትግላቸውን በአገር-አቀፍ ደረጃ እንዲያስተሳስሩ በተናጠል ከማነጋገር ጀምሮ ሁሉም የሚገኙበት አንድ አጠቃላይ ስብሰባ የመጠራቱን አስፈላጊነት ያምናል። ይኽ ስብስብ የጋራ አስተባባሪ አመራር እንዲፈጥርና በአንድ የተጣመረ ስልት ትግሉን እንዲገፋ ያስፈልጋል እንላለን። ይኽም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል የሚል እምነት አለን። ይኽ ተግባራዊ እንዲሆን ኅብረቱ የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ ይኖርበታል። የመሣሪያ ትግል የሚያደርጉ ወገኖችን በአንድ የጋራ ስብስብ ሥር የማስተሳሰሩ ጠቀሜታ ግልጽ የሆነውን በአገዛዙ ላይ ተፈላጊውን ጫና ማሳደር ብቻ ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያ የውጥረት ሁኔታ ውስጥ ያለፉ አገሮች ያጋጠማቸው የጦረኛ አባወራዎች (War Lords) ሁኔታ እንዳይፈጠር ለመከላከል ስለሚያስችል ነው። በአሁኑ ጊዜ ስማቸው የበዛና የተጣላለፈ የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱና እናካሂዳለን የሚሉ ቡድኖች በተለይ ከኤርትራው የሻዓቢያ መንግሥት ጋር የጠበቀ ቁርኝት እንዳላቸው ይታወቃል። አንዳንዶቹም ጠቅላላ ኅልውናቸው በዚሁ አካል ላይ ያረፈ ነው።

ስለሆነም ' ከበሽታው መድኃኒቱ ' እንዳይሆን ኅብረቱ ከነዚህ ቡድኖች ጋር የሚያደርገው የትግል ግንኙነት በተገቢ የተመዘነ መሆን ይኖርበታል። አበው "የአምሣ ሣንቲም ደሮዬ የአምስት ብር ገመዴን ይዛ ጠፋች" እንዲሉ ነውና።

### <u>5.1.2.4 የሕዝብ ወገን የሆነ አጠቃይ ሰፊ ስብስብ ፤</u>

በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው የአገራችን ውስብስብ ችግሮች እንኳን በተናጠል በተወሰኑ ድርጅቶች ጊዜኣዊ መተባበር ብቻ በሚደረግ ትግል ሊፈታ ከቶውኑ አይችልም። ስለሆነም የሕዝባችን ትግል አስተማማኝ አዎንታዊ ምላሽ ያገኝ ዘንድ ከፖለቲካ ድርጅቶች ውጭ ያሉ የሙያና የሲቪክ ማኅበራትንና ስብስቦችን ያካተተ ሰፊ መሠረት ያለው እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል። ኅብረቱ በዚህ ረገድ ከፖለቲካ ድርጅቶች በተጨማሪ የኅብረተሰባችንን ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚወክሉ ማኅበራትና ስብስቦች የተካተቱበት አገር - አቀፍ ጉባዔ እንዲጠራ በተደጋጋሚ ጥሪ ያቀረበውና አሁንም የሚጠይቀው የትግሉም መሠረት ለማስፋት ነው። ከዋና ዋና የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመመካከር ይኽ አገር-አቀፍ ጉባዔ ጊዜ ሳይፈጅ ተጠርቶ አሁን ባለው ትግል ተሳታፊ እንዲሆኑና በአገራችን ስለሚኖረው የሽግግር ጊዜ ምክክር እንዲደረግ ያስፈልጋል።

## <u>ክፍል ስድስት፡-</u>

## <u>አጣዳፊ ተግባራት፤</u>

የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረጉ ለትግሉ መልክ መያዝ ይጠቅማል የሚል እምነት ኅብረቱ አለው።

### <u>6.1 የዲፕሎማሲ ሥራ፤</u>

የዲፕሎማሲው ትግል ላይ ልዩ ትኩረት ተደርጎ እንቅስቃሴው ፋታ የማይሰጥ እንዲሆን አሁን የፖለቲካ ድርጅቶቹ እየሰሩባቸው ያሉ መሥመሮችን በአዲስ መንገድ በማደራጀትና አንድ ወጥና የጋራ አካል በማቋቋም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ክፍሎች ሁሉ የጋራ እንቅስቃሴ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከምርጫው ጋር በተያያዘ የታሰሩ ዜጎች ያለ

ምንም ቅድመ-ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ፥ ኢሕአዴግ በሕዝባችን ላይ ያወጀው የሽብር ጦርነት እንዲቆም፥ የተገደሉ ንፁኃን ዜጎቻችን፥ በብዙ ሽዎች የሚቆጠሩና መዳረሻቸው ያልታወቀ ታፍሰው የተወሰዱ ወገኖቻችን ጉዳይ እንዲጣራ፥ የተባበሩት መንግሥታት፥ የአውሮጳ ኅብረትና የታወቁ የዓለም-አቀፍ የሰው ልጅ መብት ተሟጋች ተቋማት ተወካዮች ያሉበት አጣሪ አካል (ኮሚሽን) እንዲቋቋም፥ ሕጋዊና ሰላማዊ እንቅስቃሴዎች እንዳይከለከሉ፥ ነፃው ፕረስ ላይ የሚደረገው አፈና እንዲነሳ፥ አገራችን መንግሥት አልባ እንደሆነችና ዜጎች ለሁለንተናዊ ስቃይ እንደተዳረጉ፥ አገራችን የትርምስ መድረክ እንድትሆን እየተደረገ መሆኑና ለአካባቢው አለመረጋጋት ጠንቅ የሚሆን ሁኔታ እየተፈጠረ እንደሆነ፥ እርዳታዎቻቸውን ለዚህ ጨቋኝ ቡድን እንዲነፍጉ፥ የአገዛዙ ቁንጮዎችና የወንጀል አራማጆች ወደ ውጭ እንዳይዎጡ የቪዛም ሆነ ሌላ ትብብር እንዲነፈጋቸው፥ ወዘተ… በሚሉት ዙሪያ እንቅስቃሴ ማድረግ። እነኝህ ጥያቄዎች ተደማጭነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው በአሜሪካ ምክር ቤት የሕዝብ ተወካይ በክቡር አቶ ክሪስ ስሚዝ የቀረበው HR 4423 እረቂቅ ሕግ እንዲፀድቅና ተግባራዊ እንዲሆን፥ የአውሮጳ ፓርላማ ያወጣው ውሳኔ ተግባራዊ እንዲሆን፥ ውሳኔዎች ገዥነት እንዲኖራቸው ተጨማሪ አስገዳጅ እርምጃዎች እንዲወሰዱና በሌሎችም አገሮች ተመሳሳይ አቋሞች እንዲወሰዱ እንቅስቃሴዎች ማድረግ። እነዚህን መሠረታዊ የዲፕሎማሲ ተግባራት ለማከናወን የጋራ አካሉ ውስጥ ችሎታው ያላቸውን ከድርጅት ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንን በማሳተፍ የተሻለ ውጤት ማግኘት ይቻላል። በዚህ ዘርፍ ሊያገለግሉ የሚችሉ እጅግ በርካታ ብቁና ፈቃደኛ ኢትዮጵያውያን ስላሉ ጉዳዬ-ፈጅ (ሎቢይስት) በሕዝብ የእርዳታ ገንዘብ የሚያስቀጥር ምንም ምክንያት የለም።

## 6.2 መረጃ ስብሰባና ልውውጥ፤

ተቃዋሚው የሚያስተላልፋቸው መልዕክቶች በመረጃ የተደገፉና ከታመኑ ምንጮች መሆን ይኖርባቸዋል። በጋራ ስብስብ ደረጃም ይሁን በተናጠል ድርጅቶች የሚደርሱ መረጃወችን በማዕከልነት የሚሰበስብና ለሁሉም ወገን የሚያስተላልፍ የጋራ አካል ሊኖር ይገባል። መረጃወችን ማጠናቀር ሊወሰዱ የሚችሉ ዝግጅቶችን በእርግጠኝነት ማከናወን ከማስቻሉም በላይ አጉል አሉባልታዎችንና ሆን ተብሎ በአገዛዙ የሚነዙ ወሬዎችን ለመቋቋም ያስችላል። በአብዛኛው በድርጅቶች በመኻልም ይሁን በኅብረተሰባችን ውስጥ ልዩነቶች የሚፈጠሩት ባልተረጋገጠና በፈጠራ ወሬ ነው። ራዲዮ ጣቢያዎች ይሁኑ ጋዜጦች፥ ድረ-ገጾች ይሁኑ በራሪ ጽሑፎች ማዕከላዊ አስተማማኝ የመረጃ ምንጭ ካለ የተሳሳተ ወይም የተዛባ መልዕክት እንዳያስተላልፉ ይረዳል።

ከዚህ ጋር በማያያዝ በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ትግል ለማኮላሸት ታስቦ በቅርቡ አገዛዙ ያወጣው ባለ ብዙ ጥራዝ ሰነድ እንደሚያስረዳው ውዥንብር ለመፍጠርና ተቃውሞን ለማክሰም አዳዲስ እረዳቶችን ለመመልመል ታጥቀው ተነስተዋል። ይኽንንኑ ውዥንብር ለመንዛት ብዙ ገንዘብ የማፍሰስ ችግር አይኖርባቸውም፥ አገር ውስጥ ቤት መሥራት ለሚፈልጉ መሬት የመስጠትም ሆነ ልዩ ልዩ የንግድ ጥቅሞችን በማባባያነት በማቅረብ ተላላ ወገኖችን ወደነሱ በመሳብ እንዲሁም በተቃዋሚው መኻል ልዩነቶች እንዲሰፉ በማድረግ አገር-ወዳዱ ክፍል አመኔታው እንዲቀንስ መጣራቸው የሚጠበቅ መሆን አለበት። ዞሮ ዞሮ ዓላማቸው በውጭው ዓለም ያለው ተቃውሞ ሲቻል እንዲከስም ቢያንስ ግን እንዲቀጭጭና ለተቃዋሚ ድርጅቶች የሚሰጠው ድጋፍ እንዲመናመን ለማድረግ ነው። ስለሆነም በዚህ እረገድ በአገር ውስጥ የሚደርሰው እመቃ አልበቃ ብሎ የጥፋትና የከፋፋይ እጃቸውን እውጭ ድረስ እንዲዘረጉ ጨርሶ መፈቀድ አይኖርበትምና ይኽንን እኩይ ዘመቻ አገር-ወዳዱንና ዴሞክራቱ ታጋይ ክፍል እንዲቋቋም ብቻ ሳይሆን የተቃውሞ ትግሉን እንዲያፋፍም በሚገባ ማደራጀትና ማዘጋጀት ያስፈልጋል። የፖለቲካ ድርጅቶቹ ከሲቪክና ከሙያ ማኅበራት፥ ከሐይማኖትና ከዜና ስርጭት ክፍሎች ጋር በመተባበር የመረጃ አሰባሰቡና ስርጭቱ ጉዳይ በጥናት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ እንዲካሄድ ያስፈልጋል። የኢሕአዴግ ቡድን ተለጣፊዎችና አፈ ቀላጤዎች በምንም መንገድ ፋታ አግኝተው በውጭ

ባለው ኅብረተሰባችን መኻል የመለያየትን መርዝ እንዲነዙ መፈቀድ የለበትም። በተመሳሳይ ሁኔታ ከኢሕአዴግ ጋር የተዛመዱና ለሱም ጥቅም የሚሰጡ የንግድ ተቋማት ተለይተው እንዲታወቁና ጨርሶ እንዲመክኑ የተቀናበረ ዘመቻ ማድረግ ያስፈልጋል።
ይኸ የመረጃ ስብሰባና ልውውጥ ተግባር በብቃትና በአስተማማኝ እንዲሠራ በሙያው ልምድና ፍላጎት ያላቸውን ወገኖች ያካተተ የጋራ አካል ሊኖር ይገባል።

## 6.3 የዜና ሥርጭት፤

በአለው አፈና ምክንያት ሕዝባችን እየደረሰበት ያለውን ትክክለኛ ዜናና መረጃ ማግኘት የአለመቻል ችግርን ለማቃለል ማዕከላዊነት ያለው የጋራ የቅስቀሳና ፕሮፖጋንዳ ክፍል ሊኖር ይገባል። ይኸ ክፍል ከመረጃ አሰባሳቢ አካል ጋር በቅርብ በመሥራት በድርጅቶች መኸል ስላለው በጎ የትብብር ጎን፥ የሕዝቡን የትግል ሞራል የሚጠብቁ፥ ለሠራዊቱና ለኢሕአዴግ ተባባሪዎች ከመጥፎ ተግባራቸው እንዲቆጠቡና ከሕዝብ ጎን እንዲሰለፉ ጥሪ የሚያቀርቡ፥ የዚህን የጥፋት ቡድን ቁንጮዎች ከሌሎች አባሎችና ተከታዮቻቸው የሚለይ፥ የወደፊቷ የሁሉም ዜጎቿ እኩልነት የተረጋገጠባት አገራችንን ብሩኅ ተስፋ የሚያመላክቱና ያሚያሳዩ፥ ወዘተ.. ቅስቀሳዎች መካሄድ ይኖርበታል። ለዚሁ ዓላማ በአዲስ መልክ የሚሠራና በሙያተኞች የሚካሄድ የራዲዮ፥ የፓልቶክ፥ ጋዜጣ/ ልሳን ወዘተ... ሥርጭት መጀመር ያስፈልጋል። እስከዚያው አሁን በሥራ ላይ ካሉ ዜና ማሰራጫዎች ጋር በቅርብ በመመካከር የተቀናበረ መልእክት ማስተላለፍ ያስፈልጋል። ቢያንስ ቢያንስ የተቃረኑ፥ አሉታዊና አፍራሽ ስርጭቶች እንዳይኖሩ ማድረግ አጣዳፊ ጉዳይ ነው። ይኸንንም ጉዳይ በቅርበትና በአስተማማኝ ሁኔታ በጋራ ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል የወል የሆነ የዜና ስርጭት አካል መቋቋም ይኖርበታል።

## 6.4 የወል እንቅስቃሴዎች ፥

እንደሚታወቀው በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ አገር ውስጥ ያለው ወገኑ ነፀብራቅ ነው። በውስጥ ያለው ትግል ሲፋፋም በውጭም ያው ይስተጋባል፥ ወዘተ... በአሁኑ ጊዜ ግን ነገሮች በዚህ መልክ እንደሚቀጥሉ ተደርጎ መታየት የለበትም። ሁኔታውን አዙረን ማስኬድ የግድ ይሆናል። ስለዚህ ውጭ ያለውን ዜጋ እስከዛሬ ከተደረጉ እንቅስቃሴዎች ለየት ባለ፥ ተከታታይነት ባለው፥ በተቀናበረ፥ በደመቀና ብዙ ፈርጅ ባለው መልክ በሙሉ ኃይል ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል። አንድ ነገር በኢትዮጵያ ሲከሰትም ይሁን በዓመታዊ ዝክሪያነት የሚደረጉ እንደ ሰላማዊ ሰልፎች፥ የሻማ ማብራት ተግባራት የመሳሰሉትን ለማከናወን በተፈለገ ጊዜ ሁሉ ያላስፈላጊና አሳፋሪ እስከሚሆን ድረስ የልዩነት ምክንያት እየሆኑ መምጣታቸው በአስቸኳይ መቆም ይኖርበታል። ስለዚህ በጋራ የሚገለጹ መልእክቶቻችንን ለማስተላለፍ የሚዘጋጁ ሰላማዊ ሰልፎችም ይሁኑ አንዳንድ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ልዩነትን ባስወገደ መልክ ለማካሄድ፥ መልእክቶቻችንም ሥርዓትና ድምቀት ባለው ሁኔታ ማስተላለፍ እንዲቻል ከሁሉም የተውጣጣ አንድ የጋራ ተግባራት ግብረ-ኃይል ማቋቋም ያስፈልጋል። በዓለም ዙሪያ የሚደረጉ ተመሳሳይ የጋራ ሥራዎችን በዚሁ አምሳያ በተቋቋሙ ቅርንጫፎች አማካይነት ተግባራዊ በማድረግ የሕዝባችንን አንድነትና የትግሉን ግለት ለማስጠበቅ ይረዳል።

# ክፍል ሰባት፦

## ተቃዋሚውና ኢሕአዴግ፤

የተቃዋሚው ክፍልና የኢሕአዴግ ግንኙነት በአብዛኛው ብዥታ የበዛበት ወይም ጨርሶ አንድ ጎንዮሽ ነው ማለት ይቻላል። ብዥታው በሕዝብ ትግል ያልታጀበና የድርድር መሠረታዊ ማጠየቂያ የሆነው የኃይል ሚዛን በተዛባበት ሁኔታ ለመደራደር ማሰብ ነው።

እንደማንኛውም አምባ-ገነን አገዛዝ ኢሕአዴግም ድርድርን ተገዶ እንጅ በፈቃዱ የማይሞክረው ጉዳይ ነው። ስለዚህ ይኽ ቡድን ወደ ድርድር እንዲመጣ ማስገደጃ መንገዱ ምንድን ነው? ለሚለው ተገቢ ጥያቄ መልስ መስጠት ያስፈልጋል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ምርጫ ፺፯ን ነፃና ፍትኃዊ ለማድረግ ኅብረቱ ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ተደራድሯል። የማይናቁ ውጤቶችንም አስመዝግቧል። ቅድመ-ምርጫም ሆነ ከምርጫው በኋላም በአብዛኛው ከቅንጅት ጋር በመሆን ከዚሁ ኃይል ጋር ድርድሮች ተካሂደዋል። ከዚህ ገዥ ፓርቲና መንግሥት ጋር በተደረገ ድርድር የተገኙ ጥቂት ውጤቶች ቢኖሩም እያንዳንዱ ግኝት በተለይ በሦስተኛ ክፍሎች ወይም በሁኔታዎች ታላቅ ግፊትና ጫና ብቻ ነው መገኘት የቻለው።

የአምባ-ገነኖች ወደ ድርድር አለመቅረብ ወይም አለመፈለግ ለሁሉም ጥያቄ እኛ የተሻለ መልስ አለን፥ ከሁሉም የበለጠ ችሎታ አለን ከሚል ግብዝ አስተሳሰብ ብቻ የመነጨ አይሆንም። አብዛኛው ግትርነት ካለመተማመንና ከስጋት የመነጨ ነው። ስጋቱም እጠፋለሁ የሚል ነው። ልዩነትን ማስተናገድ የማይችሉትም ለዚህ ነው። ከዚህም የተነሳ ታዲያ ከነዚህ ክፍሎች ጋር ውጤት ያለው ድርድር ለማድረግ ጫናው አስተማማኝና ሊሸከሙት የማይችሉት መሆን ይኖርበታል። በኅብረቱ በኩል ያለመታከት ትግሉ በሕዝብ የታጀበ መሆን አለበት የምንለው ትግሉ አስተማማኝ ውጤት እንዲኖረው ሲሆን ከገዥው ጋር ለሚደረገውም ድርድር አስገዳጅነቱ አጠያያቂ ስላልሆነ ነው። ሌላው ብዙም ያልተገፋበት መንገድ ያላቸውን ስጋት የሚያቃልል አቅርቦት ማሳየት ወይም ማረጋገጫ መስጠት ይሆናል። በዚህ እረገድ ኅብረቱ ከቅንጅቱ ጋር በጋራ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ምስረታን አሳብ ያቀረበው ምንም እንኳ ኢሕአዴግ በምርጫው እንደተቸነፈ ቅንጣት ጥርጥር ባይኖርም ሁሉን ያጣ ሆኖ እንዳይሰማውና የሽግግሩን ሂደት እንዳያደናቅፍ በማለት ነበር። አሁንም በኅብረቱ በኩል የሚገፋው የሰከነ ሽግግር ሂደትን የመከተል ዓላማ ከዚሁ እምነት የመነጨና ኢሕአዴግም በአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ላይ የጥፋት መልእክተኛና የውድመት አራማጅ ብቻ ሳይሆን በነገዋ ኢትዮጵያም የፖለቲካ ሕይዎት እንዲኖረው ዕድል ለመስጠት ነው። ይኽ የሚሆነው የሽንገላ ፖለቲካን ለማስተናገድ ሳይሆን የኅብረቱን የብሔራዊ እርቅ መተክላዊ አቋም በተከተለ መንገድ ትርምስን ባስወገደ መልክ የተረጋጋ ኅብረተሰብን ለማስገኘት በሚያስችል አካሄድ እንዲሆን ነው።

የገዥው ክፍል ቁንጮዎች ከግላቸው ጠባብ ዓላማ ይልቅ የአገርና የወገን ብሶት በልጠባቸው እኛን አምነው ወይም ጥሪያችንን በቀና ተቀብለው በቀላሉ ትብብር ያደርጋሉ ከሚል ቀቢፀ-ተስፋም አይደለም። ሆኖም ጥሪያችንና መልእክታችን ለሰፊው የኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎች፥ ለሠራዊቱ፥ ለፖሊሱና ለፀጥታ ኃይሎች፥ ወዘተ... ነው። አቶ መለስና የአገዛዙ ቁንጮዎች እንደ ኮሎኔል መንግሥቱና ኢሠፓ ሰፊውን አባላትና ደጋፊዎቻቸውን ገደል ይዘዋቸው እንዳይገቡ ያስፈልጋል። እነሱ ከሕዝብና ያለ አግባብ ከአገሪቱ ዘርፈው በውጭ ሃብት አከማችተው፥ ልጆቻቸውንና ወዳጅ ዘመዳቸውን ጥግ ጥግ አስይዘው፥ በውጭ መሸሻ ቤት ሰርተውና ንብረት አከማችተው፥ ነገ ነገር ባለበት መቀጠል ሳይችል ሲቀር ለነሱ ጥቅምና ሥልጣን ከሕዝብ አናክሰውት፥ በነሱ ሃጢኣት ከወገን አቀያይመውትና ተጠያቂ አድርገውት ባወጣ ያውጣህ ብለው አውላላ ሜዳ ላይ በትነውትና ከድተውት ሊፈረጥጡ ከሚችሉት ሳይሆን ከቀሪ ወገኑ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዲያብርና የነገዋን ኢትዮጵያ አብሮ እንዲገነባ ያስፈልጋል። ምንም ዓይነት ሰላማዊና የሰከነ ሽግግር ኢሕአዴግን ሳይጨምር ማድረግ አይቻልም። እንኳን በፖለቲካ ስሊት በተራ ኤኮኖሚያዊ ስሊት መንገዱ ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም። ሃብትና ንብረት አልባ ሆኖ በትግል ላይ ጊዜውን ያሳለፈና ባዶ እጁን ሥልጣን ላይ ወጥቶ አሁን ሃብት ያካበተ አዲስ ከበርቴ ሌላው ቢቀር ያለአግባብ ያካበተውን ንብረትና የለመደውን የድሎት ሕይወት ላለማጣት ይሟሟታል። የእኛ ጭንቀት እነሱ አዲስ የለመዱት ድሎት እንዳይጓደልባቸው ለመንከባከብ አይደለም። “እባብ ያዬ በልጥ በረየ” ነውና የአዲሶቹ ጌቶች ስጋት እነሱን የሚተካው ሁሉ እነሱ በተኩት ላይ የወሰዱትን የጅምላ ብያኔ የሚያደርስባቸው

ስለሚመስላቸው ነው። ሆኖም አፍአዊ ሳይሆን ተግባራዊ ሊሆን በሚችል መንገድ ሕጋዊ ዋስትና መኖሩን ማረጋገጫ መስጠት ተገቢ ይሆናል።
የሚገርመው አሁን በአገራችን በአለው የኃይል አሰላለፍ ምክንያት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር የማይገደው ኢሕአዴግ በተለይ መሪዎቹ ነገ ለኢትዮጵያ ሉአላዊነትና አንድነት ቆሜአለሁ ብሎ ሊያውጅና ተቃዋሚው መኻል ከፍተኛ ልዩነት ሊፈጥር የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር መቻሉ ነው። እንደሚታወቀው የአብዛኛው ዴሞክራሲያዊና አገር-ወዳድ ተቃዋሚ ክፍል ትግል በኤገራችን የመልካም ሥርዓት እውን የመሆን እንጅ ኢትዮጵያ የምትባለዋን አገር በአገር ደረጃ የመቀጠሏን ጥታቄ ውስጥ ያስገባ አይደለም። የአንዳንድ ክፍሎች አካሄድ ተቃራኒው ሊሆን ይችላል፤ 'እራሴን "ነፃ" ላውጣና ስለ አንድነቱ በኋላ አስብበት ይሆናል' የሚል።

ኢሕአደግ በሚወስደውና እየወሰደ ባለው አረመኔአዊ እርምጃ ከሕዝብ ጋር ዓይና አፈር ሆኗል። እንግዲህ ማጣጣም የሚያስፈልገው ይኽንን የሕዝብ ደመኛ የሆነ ኃይል እንዴት አድርጎ የሕዝብና የሽግግሩ አካል ማድረግ እንደሚቻል ነው። በአለው የኃይል አሰላለፍ ብቻ ሳይሆን እንዲሁም ኢሕአዴግን ከምድረ-ገፅ ጥፋ ማለት የሚቻል አይሆንም። ተመራጭም አይደለም። በእኛ እምነት ኢሕአዴግ አዎንታዊና ገንቢ ሚና መጫወት ይችላል። ይኽ መሆን የሚችለው አመራሩን መቀየር ሲችል ብቻ ነው። በአንድ እምነት ዙሪያ የሚንቀሳቀስን ኃይል፥ ያውም ከጅምሩ፥ እንዲለወጥ ከተፈለገ ወይም አዲስ አቅጣጫ እንዲይዝ ከተፈለገ አመራሩ መቀየር አለበት። በደቡብ አፍሪቃም ሆነ በቀድሞው ሶቪየት ኅብረት እንደተከሰተው ከነበሩበት ወጣ ባለ መልኩ አቅጣጫ መቀየር የተቻለው በአሮጌው ሳይሆን በአዲስ አመራር ነው። ይኽ ደግሞ የተሻለ የሚሆነው በተፈጥሮ በሚደርስ የአመራሩ ኅልፈት ወይም ከመድረኩ መወገድ ሳይሆን ለዚሁ ስሊት ለዚሁ ዓላማ ቢሆን በጣም ይመረጣል።

የኢሕአዴግ ቁንጮ መሪዎች በሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። ሆኖም ድርጅታቸውን ከሕዝብ ጎን ለማሰለፍና ኃይላቸውን ለጋራ አገር ጥቅም ለማዋል የሚችሉ አገር-ወዳዶች በንፁኃን ደም የተበከሉትን የወቅቱ መሪዎች አስወግደው ለእርቅና ሰላሙ አራማጅ መሆናቸው እጅጉን የተመረጠ ይሆናል። ስለሆነም በኢሕአዴግም ይሁን በአባል ድርጅቶቹ ውስጥ ያሉ አገር-ወዳድና የሕዝብ ስቃይ የተሰማቸው ወገኖች ይኽንን ታሪካዊ ተልዕኮ እንዲወጡ እነሆ ጥሪያችን ነው። ይኽ ከሆነ አገራችንን ከተደገሰላትና ማንም ተጠቃሚ ከማይሆንበት አደገኛ የትርምስ ሁኔታ አዳን፥ ሕዝባችንን ታደግን፥ በታሪክ ተወቃሽ አለመሆን ብቻ ሳይሆን ታሪክም ሰራን ማለት ነው።

## <u>ክፍል ስምንት፤</u>

## <u>መደምደሚያ ፤</u>

የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍላጎቱና በፈቃዱ የመረጠው፥ ተጠያቂነት ያለውና ሃላፊነት የሚሰማው መንግሥት ባለቤት ለመሆን እንዲችል በትግሉና በመስዋዕትነቱ በግንቦት ሰባት ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ያስመዘገበው ድል በኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነኖች እየተሰናከለበት ይገኛል። ኢሕአዴግ የሕዝብን መብት አፍኖ ያለ ሕዝብ ፈቃድ በመሣሪያ ኃይል ብቻ የአገዛዝ ዕድሜውን ለማራዘም ሲል ያወጀበትን አፈናና እመቃ ተቋቁሞ ለመብቱ መረጋገጥ በመታገል ላይ ነው። የተቃዋሚው ክፍል በአንጻሩ የተነሳሳውን የሕዝብ መንፈስ፥ ስሜትና ፍላጎት በሚመጥን ደረጃ አሚሚቱንና መስዋዕትነቱን የሚያካክስ በሳልና ወቅታዊ አመራር ሰጥቶ ወደ ተረጋገጠና አይቀሬ ድል ማብቃት እየተሳነው እንደሆነ በግልጽ የሚታይ ጉዳይ ነው።

አገራችን በእርግጥም መንታ መንገድ ላይ ትገኛለች፡፡ አማራጩ ግልጽ ነው፤ የሕዝብ ሙሉ መብት ተከብሮና የጋራ ኅልውናችን ተረጋግጦ፥ የሰላምና የብልጽግና አቅጣጫ የሚያዝበት ወይም አርቆ ማየት ከመሳን በመነጩ በፀፀት ወደማይመለስ፥ በታሪክ ወደሚያስጠይቅና ይቅርታ ወደማይደረግለት፥ ማንም ተጠቃሚ ወደማይሆንበት ትርምስና የጥፋት አቅጣጫ መያዝ ነው፡፡

ሕዝቡ የሚያደርገውን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የመብት ማስከበር ትግል ማስተናደገድ ያልቻለውና የማይችለው የአቶ መለስ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ቡድን በሥልጣን መቆየትን የሞት የሽረት ጉዳይ አድርጎ ከራሱ ሕዝብ ጋ እየተፋለመ ይገኛል፡፡ የአፈና መረቡንም ከአገር አልፎ በውጭው ዓለም ሳይቀር ለማስፋትና የጥፋት እጁን ለመዘርጋት የሚያደርገው መራወጥ ጣራ ላይ ደርሷል፤ ይኽ ይዞታ ቀጣይነት ሊኖረው ግን አይችልም፡፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ከውጭው ዓለም የሚያገኘውን ብድር ከሕዝብ ጉሮሮ እየነጠቀ በዚህ የሕዝብ እመቃ ዘመቻው ላይ የማባከን ጥረቱ የባሰ ከሕዝብ የሚያርቀውና በቀጣይነት ለረዥም ጊዜ ሊያዋጣውም የማይችል የተስፋ መቁረጥ ከንቱ አካሄድ ነው፡፡ ሕዝባችን ይኽ ሁሉ ግፍና መከራ እየወረደበት አሁንም ይኽን ተፍቶ የጣለውን አገዛዝ እስከ ሌላ ኢሕአዴግ ለሚያዘጋጀው ምርጫ ዙር ድረስ ላለመሸከምና መብቱን ለማስከበር ቁርጠኝነቱ እንዳለና ልቡ እንደሸፈተ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ የመብትና የኅልውና ማስከበር መራር ትግል ኢትዮጵያውያን በሁሉም ዘርፍና በየትኛውም ቦታ አኩሪ መረባረብ እያደረጉ ነው፡፡ ምናልባትም በስድሳዎቹ ዓመታት ከነበረው የተማሪ እንቅስቃሴ ወዲህ ታይቶ በማይታወቅ የጋለ ስሜት በውጭው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በተለይም ወጣቱ አገር-ወዳድ ክፍል ከድርጅቶች ጋር በመሆንም ሆነ በራሱ አነሳሽነት የአቶ መለስ አሸባሪ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈጽመውን ግፍ በማጋለጥና ስቃይ ላይ ለሚገኙ ወገኖቹ የእርዳታ እጁን በመዘርጋት የሚደነቅ ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴ እያደረገና እጅግ የሚያኮራ ተግባር እየፈጸመ ይገኛል፡፡

ጥንታዊቷ አገራችን ኢትዮጵያ በውስጧ ያልተወለዱ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በውስጣቸው የወለዱ፥ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወልደው ኢትዮጵያ ልታሳድጋቸው ባትችልም ኢትዮጵያን ሊያሳድጉ የሚፈልጉና የሚመኙ፥ ኢትዮጵያ አድገው አምባ-ገነን አገዛዞች አገራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ሊያኖሯቸው ያልቻሉ በየሄዱበት ኢትዮጵያን በልባቸው ቋጥረው ያኖሩ፥ ውድ አገራቸው ኢትዮጵያ ላይ በክብር አርጅተው በአገራቸው ውስጥ የተፈጥሮ ሞት የመሞት እንኳ ዕድሉ የተነፈጋቸው፥ ለዚች ብርቅ አገራቸው ለመሞት ወደኋላ የማይሉና የቆረጡ ዜጎች ያሏት አገር መሆኗ በገሃድ እየተመሰከረ ነው፡፡

የኢዴኃኅ (ኅብረት) መመሥረት ለአገራችን በጎ አሳቢ ሁሉ ታላቅ ደስታ የመሆኑን ያህል ገዥው ክፍል ለመጀመሪያ ጊዜ መለስተኛም ይሁን እንጂ ተቃዋሚውን ወገን አክብሮ ወደ ድርድር ለመምጣት አስችሏል፡፡ ምንም እንኳ ኅብረቱን ለመመሥረት ከሁለት ዓመት በላይ ጊዜ መፍጀቱ ድርጅቶች በተለይ ከመጀመሪያው ጀምሮ በዚህ ሂደት የነበሩት በመኻላቸው የነበረውን የተለመደ አለመተማመን ለማስወገድ እንደረዳ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ግን ኅብረቱ ከተመሠረተ ማግስት ጀምሮ በዝግጅቱ ወደ መጨረሻ ከገቡት ውስጥ ኅብረቱን የበለጠ ያጎለብታሉ ተብለው የተጠበቁት ሁለት ድርጅቶች- መኢአድና ኢዴፓ (በኋላ ኢዴአፓ)- ከኅብረቱ ጋር አብሮ መጓዝ አለመቻልና ልዩነት መፈጠር ሳቢያ ተቃዋሚው በጋራ ትግሉ በአንድ አሰላለፍ እንዳይሔድ እክል ሆኗል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ከዚያ መናጋት በኋላ ኅብረቱ ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚው ትግል አንክሶ ነው የቀጠለው፡፡ የዚህ አባዜም አሁንም እንኳ ድርጅቶች ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ኃይላቸውን አስተባብረው ተግባራዊ የጋራ እንቅስቃሴ ማድረግ በሚጠበቅባቸውና በሚገባቸው በዚህ የቀውጢ ወቅት በሚያሳዝን መልክ ተለያይቶ የመሔድ አባዜ ሲንፀባረቅ ይታያል፡፡ ይኽንን ለመፍታት ኅብረቱ ከፍተኛ የማያቋርጥ ጥረት ከማድረግ አልተቆጠበም፡፡

የአቶ መለስ አምባ-ገነን አገዛዝ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አመፅ እየፈጸመ የአገዛዝ ዕድሜውን ለማራዘም በሚያደርገው የሽብር ጦርነት ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኗል፡፡ በምንም መሥፈርት በዚህ ፀረ-ሕዝብና አረመኔአዊ አድራጎት የተጠመደና ይኸን መሰል ሽብርተኛ አቋም ላለው ማንኛውም ኃይል ሕዝብን የማስተዳደር ብቃትና መብት ሊኖረውም ሆነ ሊሰጠው አይችልም፥ አይገባም፡፡ በእኛ እምነት በግንቦት ምርጫ አቸናፊ ሆኖ መታየት ያለበት አንድ ድርጅት ወይም ሁለት ሦስት ድርጅቶች ሳይሆን (ሳይሆኑ) ያቸነፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፤ አቸናፊው ዴሞክራሲ ነው፡፡ ያ የዴሞክራሲ ችግኝ፥ ያ የብሩህ ተስፋ ጅማሮ ግን ተኮትኩቶ እንዲድግ፥ እንዲያብብና እንዲያፈራ መረባረብ ሲገባ ዕድል ተነፍጎት እንዲጠወልግና እንዲከስም እየተደረገ ነው፡፡

እንደምንምና በማናቸውም መንገድ ሥልጣንን የሙጥኝ ማለት የአምባገነኖች ዘይቤ ነውና ኢሕአዴግም ይኸንን የሰኔ ሰባት አኩሪ ብሔራዊ ኩነት ያየውና የተቀበለው በደስታ ሳይሆን በድንጋጤና በደም ፍላት ነው፡፡ በመሆኑም የምርጫው ውጤት በፈለገውና እንደፈለገው አለመሆኑን ከተረዳበት ግንቦት ሰባት ምሽት አንስቶ በሕዝብ ድምፅ ላለመገዛት ሕገወጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በአዲስ አበባ ከማወጅ ጀምሮ የሕዝብን የመገናኛ ብዙሃን ለተቃዋሚው ጨርሶ በመከልከል፥ የተሳሳቱ ወሬዎችንና አሉባልታዎችን በማሰራጨት፥ ተቃዋሚውን በማጥላላት፥ አንድን የሕዝብ ወገን በተለይም የትግራይን ሕዝብ ከቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ለማናከስ የተለመደ ደካማና አሳፋሪ መሰሪ ተግባር ላይ በመሰማራት፥ እሱን ያልመረጡት ዜጎች ላይ በቀል የተሞላበት ማንገላታት፥ ማሳደድ፥ በየእስር ቤቱና በየማጎሪያ ጣቢያዎች ማሰርና ማሰቃየት፥ ንፁኃን ዜጎችን መግደል፥ ወዘተ.... ወንጀል ላይ ተሰማርቷል፡፡

በዚህ ቀውጢና ፈታኝ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ የድርጅቶች ኃላፊነት በቅድመ-ግንቦት አስተሳሰብ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን የሚያስተጋቡበትና የሚወዳደሩበት ሳይሆን የጋራ እንቅስቃሴዎች የሚደረግበት የትብብር ጊዜ መሆኑን ተረድተው በዚህ ረገድ ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ ነው፡፡ መተማመንን ኮትኩቶ፥ በብሔራዊ እርቅ ላይ የተመሠረተ ብሔራዊ መግባባት የሚያስገኘው የጋራ የወደፊት ዕድል መተለሚያ ረጅም ጉዞአችንን መያያዝ ያለብን ጊዜ አሁን ነው፡፡ የተናጠል ትግል ትርፍ የለውም፤ ውጤቱም ዞሮ ዞሮ ሁሉም እንዲለወጥ የሚፈልገውን አገዛዝ ዕድሜ ማራዘም ብቻ ይሆናል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ሕዝባችን አይከፍሉ መስዋዕትነት እየከፈለ ባለበት ሁኔታ የሕዝቡን ትግል በአገር-አቀፍ ደረጃ የሚመራ ማዕከላዊ አመራር እጥረት በገሃድ መታየቱ እጅግ ሊያሳስብም ሊቆጭም ይገባል፡፡ ይኽ ሁኔታ ባስቸኳይ አመርቂ ምላሽ ካልተሰጠው የሕዝባችን ትግል እየኮሰመነ እንዲሄድና አጠቃላይ ሁኔታውም አቅጣጫውን ቀይሮ ማቃናት ወደማንችልበት ደረጃ እንዲደርስ መፍቀድ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የሕዝባችን ቀጣይ ሰቆቃ እንዲያከትምና የጥፋት ድግሱ እንዲከሽፍ ጊዜ ሳይሰጥ ትግሉ በተቀናበረ መልክ ሊመራ ይገባዋል፡፡ በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው ለአገራችን የተወሳሰበ ሁኔታ ኅብረቱም ይሁን ቅንጅቱ እንኳን አሁን ባሉበት ደረጃ በፊትም ቢሆን በተናጠል ምላሽ ሊሰጡ አይቻላቸውም፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
ድል በኅብረት!
ኅብረት ለአስተማማኝ የሕዝብ ድል!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም